ባሕረ - ሐሳብ

ወ

ሥነ-ፍጥረት

ወልደአብ ወልደማርያም

ዛቲ ይእቲ ደብረ-ጉንደወይን ምስለ እምየ ቆጋ ኪዳነ-ምህረት

በመንፈስቅዱስ ስከበረ



አዘጋጅ ፡- እሱባለው ዘጎንቻ(ወልደ-ሚካኤል)

ባሕረ ሐሳብ

ወሥነ-ፍጥረት

ከወልደ ሚካኤል

እምየ ጉንደወይን

የመጀመሪያ ዕትም ታኅሣሥ ©19/2012 ዓ.ም

©የአዘጋጁ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

መታሰቢያነቱ

“በፍቅረ እግዚአብሔር ፀንተው፤ ቅኔ ተምረው ፤ትርጓሜ ተርጉመው፤ ተምረው ፤አስተምረው ትምህርትን ከትህትና፤ እውቀንት ከእምነት፤ አስተባብረው ይዘው ለሃይማኖታቸው ሲሉ ግርማ ሌሊቱን፣ፀበ አጋንንቱን ታግሰው በአንብእከ በጸሎት ሃይማኖታቸውን ይዘው ለአቆዩን ለቅዱሳን መሲሐዊያን አባቶቼ ይሁንልኝ። በተለይም ለምስባከ ቅዱሳን ቆጋ ኪዳነ ምሕረት አፀደ ኤምስጣቴዎስ አንድነት ገዳም መነኮሳት ገዳማዊያን ርቱዓ ሃይማኖት መሲሐዊያን ይሁነልኝ።”

የሽፋን መግለጫ

- ደብረ-ጉንወይን ምስለ ቆጋ ኪዳነ - ምህረት ቤተ ክርስቲያንን ያመለክታል።
- እንዲሁም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ብሒልን ይገልፃል ማለት ነው።
- የመጽሐፉን ስም እንዲሁ የሚገልፅ ሽፋን ነው (ባሕረ ሐሳብ ወሥነ-ፍጥረት)።

አስተያየት መልእክት፤ወንድማዊ ምክር ፤ ማስተካካያና ማስረጃዎች ካለዎት:-

- ✓ Bereketdesssie647@gmail.com(0919473584)

ምስጋና

“ከሁሉ አስቀድሞ አነሳስቶ ላስጀመረኝ አስጀምሮም ላስፈፀመኝ ፤ ለልዑል እግዚአብሔር ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ስሙ የተመሰገነ ይሁን። በመቀጠል እግዚአብሔር በፀጋ መንፈስ ቅዱስ ያከበራቸው ነቢያት፤ሐዋርያት፤ፃድቃን ሰማዕታት ፤ደናግል መነኮሳት እንደየክብራቸው መጠን ስማቸው ከፍ ከፍ ያለ ይሁን።”አሜን!!!



መስቀል ኃይልነ

መክሥተ አርእስት

አርዕስት ገጽ

የመክፈቻ ጸሎት.....፭

መቅደም.....፱

የቅዱስ ዲሜጥሮስ ታሪክ.....፲

የአጽዋማትና በዓላት ሥርዓት.....፲፪

የቅዱስ ዲሜጥሮስ ታሪክ.....፲፪

፩. ምዕራፍ አንድ፡- ባሕረ ሐሳብ.....፲፫

፩.፩. ባሕረ-ሐሳብ ምንድን ነው.....፲፫

፩.፪. ስለምን ባሕር ተባለ.....፲፩

፩.፪.፩. መርሐ ዕውር.....፲፭

፩.፪.፪. ሐሳበ አቡሻሃር.....፲፭

፩.፪.፫. ሐሳበ ፈለክ.....፲፭

፩.፫. ባሕረ ሐሳብ እንዴት ተገኘ.....፲፭

፩.፬. መጥቅዕ.....፲፮

፩.፭. አበቅቴ.....፲፰

፩.፮. ዘመነ ወንጌላዊያን.....፲፱

፩.፯. የዘመን መለወጫ.....፳

፩.፯.፩. ጥንተ ቀመር.....፳

፩.፯.፪. ጥንተ ዖን.....፳፩

፩.፯.፫. ጥንተ ዕለት.....፳፩

፩.፯. ፈተና አንድ.....፳፪

፪. ምዕራፍ ሁለት፡- አዕዋዳት.....፳፫

፪.፩. ዐውደ ዕለት.....፳፫

፪.፩.፩. የዕለት መጀመሪያ(ጥንተ ዕለት)……..፳፬
፪.፪. ዐውደ ወርኀ……..፳፬
፪.፫. ዐውደ ዓመት……..፳፬
፪.፬. ዐውደ አበቅቴ……..፳፭
፪.፭. ዐውደ ፀሐይ……..፳፭
፪.፮. ዐውደ ማዕከላዊ……..፳፭
፪.፯. ዐውደ አብይ ቀመር……..፳፭
፪.፰. ፈተና ሁለት……..፳፯
፫. ምዕራፍ ሦስት፡- ወንበር……..፳፰
፫.፩. ፈተና ሦስት……..፳፱
፬. ምዕራፍ አራት፡- አበቅቴ……..፴
፬.፩. ሕፀፅ……..፴፩
፬.፪. የሌሊት አወጣጥ……..፴፪
፬.፫. ሠርቀ ወርኀ……..፴፫
፬.፬. ፈተና አራት……..፴፬
፭. ምዕራፍ አምስት፡- መጥቅዕ……..፴፭
፭.፩. የዕለታት ተውሳክ……..፴፯
፭.፩.፩. የቅዳሜ ተውሳክ……..፴፯
፭.፩.፪. የእሑድ ተውሳክ……..፴፯
፭.፩.፫. የሰኞ ተውሳክ……..፴፯
፭.፩.፬. የማስክኞ ተውሳክ……..፴፯
፭.፩.፭. የረቡዕ ተውሳክ……..፴፯
፭.፩.፮. የኀሙስ ተውሳክ……..፴፯
፭.፩.፯. የዓርብ ተውሳክ……..፴፰
፭.፩.፰. ፈተና አምስት……..፴፰

፮. ምዕራፍ ስድስት፡- መባጃ ሐመር.....፵፱
፮.፩. የአጽዋማት ተውሳክ.....፵
፮.፩.፩. የጾመ ነነዌ ተውሳክ.....፵
፮.፩.፪. የዐብይ ጾም ተውሳክ.....፵፩
፮.፩.፫. የደብረ ዘይት ተውሳክ.....፵፩
፮.፩.፬. የሆሣዕና ተውሳክ.....፵፪
፮.፩.፭. የስቅለት ተውሳክ.....፵፪
፮.፩.፮. የትንሳኤ ተውሳክ.....፵፪
፮.፩.፯. የርክበ ካህናት ተውሳክ.....፵፪
፮.፩.፰. የዕርገት ተውሳክ.....፵፪
፮.፩.፱. የጰራቅሊጦስ ተውሳክ.....፵፫
፮.፩.፲. የጾመ ድኅነት ተውሳክ.....፵፫
፮.፩.፲፩. የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ.....፵፫
፮.፩.፲፪. ፈተና ስድስት.....፵፬
፯. ምዕራፍ ሰባት፡- የአጽዋማት ገደብ.....፵፭
፯.፩. የአጽዋማት ኢየዐርግና ኢይወርድ.....፵፭
፯.፩.፩. የጾመ ነነዌ ገደብ.....፵፮
፯.፩.፪. የዐብይ ጾም ገደብ.....፵፰
፯.፩.፫. የደብረ ዘይት ገደብ.....፶
፯.፩.፬. የሆሣዕና ገደብ.....፶፩
፯.፩.፭. የስቅለት ገደብ.....፶፫
፯.፩.፮. የትንሳኤ ገደብ.....፶፬
፯.፩.፯. የርክበ ካህናት ገደብ.....፶፮
፯.፩.፰. የዕርገት ገደብ.....፶፯
፯.፩.፱. የጰራቅሊጦስ ገደብ.....፶፱

፮.፩.፲. የጾመ ድኅነት ገደብ.....፰
፮.፩.፲፩. የጾመ ሐዋርያት ገደብ.....፰፪
፮.፩.፲፪. ፈተና ሠባት.....፰፬
፰. ምዕራፍ ስምንት፡- በእንተ ጳጉሜ.....፰፰
፰.፩. ጳጉሜ.....፰፰
፰.፪. የጳጉሜ አመጣጥ.....፰፯
፰.፫. የጳጉሜ ስድስት የመሆን ምሥጢር.....፰፯
፰.፬. የጳጉሜ ሠባት የመሆን ምሥጢር.....፰፱
፱. ምዕራፍ ዘጠኝ፡- የኢትዮጵያዊያንና የምዕራባዊያን የቀናትና የወራት ስያሜ.....፱፩
፱.፩. የዕለታት ስያሜ ልዩነት.....፱፩
፱.፩.፩. የኢትዮጵያዊያን.....፱፩
፱.፩.፪. በምዕራባዊያን.....፱፬
፱.፪. የወራት ስያሜ ልዩነት.....፱፯
፱.፪.፩. በኢትዮጵያዊያን.....፱፯
፱.፪.፪. በምዕራባዊያን.....፲
፲. ምዕራፍ አሥር፡- ሥነ-ፍጥረት.....፲፬
፲.፩. መግቢያ.....፲፬
፲.፪. የእሑድፍጥረታት.....፲፭
፲.፫. የሰኞ ፍጥረታት.....፲፭
፲.፬. የማግሰኞ ፍጥረታት.....፲፮
፲.፭. የረቡዕ ፍጥረታት.....፲፯
፲.፮. የኀሙስ ፍጥረታት.....፲፰
፲.፯. የዓርብ ፍጥረታት.....፲፱
፲.፯.፩. የአዳምና የሔዋን ተፈጥሮ.....፯
ምስጋና ለሥላሴ.....፻፩

የመክፈቻ ጸሎት

“በስመ እግዚአብሔር አብ መስተሣህል ወመሐሪ በቃሉ ወበመንፈሱ ኩሎ ዓለም ሣራሪ፤”፤

“ወበስመ እግዚአብሔር ወልድ ቃለ አብ ነባቢ፤ ወቃለ መንፈስ ቅዱስ ተናጋሪ ኩሎ ፍጥረተ በአሐቲ ምክር ገባሪ”፤

“ወበስመ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፤ መንፈሰ አብ ወወልድ ኃጢአተነ ዘይሰሪ”፤

“ሳዱዓ ወክሡተ በአሐቲ ሥምረተ ፈጠረ እንዘ አስምከ በዝንተ ጉንደ ሃይማኖት አስካለ በረከት ዘይፈሪ”፤

- *እጽሕፍ ለክሙ አበው እስመ አእምርክምዎ ለቀዳማዊ፤*
- *እጽሕፍ ለክሙ ወራዙት እስመ ሞእክምዎ ለእኩይ፤*
- *ጸሐፍኩ ለክሙ ደቂቅየ እስመ አእመርክምዎ ለአብ፤(፩ኛ.ዮሐ ፪፤፲፫)*

ትርጉም

“በቃሉና በመንፈሱ ዓለምን ሁሉ ስለመሠረተ፤ መሐሪና ይቅር ባይ ስለሆነው ስለ እግዚአብሔር አብ ስም ፤ የአብ ቃል ነባቢ ፤ የመንፈስ ቅዱስ ቃል ተናጋሪ፤ ስለሆነው፤ ፍጥረትን ሁሉ በአንዲት ክብር ስለፈጠረ ስለ እግዚአብሔር ወልድ ስም ፤ አንዲት የፈጣሪ ፈቃድ ሥውርና ግልፅ የሆነውን ኃጢአት ይቅር ስለሚል የአብና የወልድ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ፤ ስለ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስም የበረከት ፍሬን በሚያፈራ በዚህ ሃይማኖት ግንድ አምኜ፤”

“አባቶች እፅፍላችኋለሁ ቅድመ ዓለም የነበረ እርሱን ዐውቃችኋልና፤ ጎልማሶች እጽፍላችኋለሁ ክፉውን ድል ነስታችኋልና፤ ልጆቼ ጻፍኩላችሁ አብን ዐውቃችሁታልና። (1ኛ.ዮሐ 2፤13)”

መቅድም

መቅድም ፦ ማለት ወደ ቤት ለመግባት በሩን መክፈት እንደሚያስፈልግ ሁሉ ከፅሁፍ ፍሬ ነገር አስቀድሞ የሚገኝ ገለፃ ማለት ነው ። "ይደልዎ ለዘያነብብ ቅድመ ይዝክር ስሞ ለበዓለ መጽሓፍ ወእምዝ ያንብብ ወይምህር ።" እንዳለ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለዚህ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ትውልድ ያውቀው፣ይማረውና ያስተምረው ዘንድ የእምየ ኢትዮጵያ ታላቅ ሀብት የሆነውን ባሕረ ሐሳብ በቀላል አቀራረብና ግልፅ በሆነ መልኩ ለትምህርቱ አዲስ የሆነ ሰው እንዲገነዘበው አድርጌ ለማቅረብ ሞክሬአለሁ።

ባሕረ ሐሳብ ሰፊና ጥልቅ በመሆኑ ማንም ጽፎና አስተምሮ ሊጨርሰው እንደማይችል የታወቀ ነው።እናም በዚህ አነስተኛ ጽሁፍ የቀረበው ባሕረ ሐሳብ ከብዙ በጥቂቱ፣ከረጅሙ በአጭሩ፣ከሰፊው በጠባቡ፣የቀረበ እንጅ ከጫፍ እስከ ጫፍ ተጽፎ የተጨረሰ አይደለም ። ይልቁንም ወጣቱ ትውልድ አጽዋማትንና በዓላትን ራሱ ማውጣት ሲችልና መማር ሲችል በቅርቡ ቀላል መገልገያ ባለማግኘቱ እየተቸገረ በመናፍቅ ሥርዓት ተውጦ ቆይቶአል። በተለይ የቤተ ክርስቲያንን ዶግማና ቅኖና በመጣስ የምንፍቅና መረባቸውን የዘረጉ መናፍቃን እነርሱ ስተው ፍጥረተ እግዚአብሔርን ሲያስቱና ሲያጠፉ ይስተዋላሉ፤ በተለይም በልደትና በአጽዋማት ላይ ትልቅና አስነዋሪ ስራ ሲሰሩ ይስተዋላሉ፤ እናም ይህ አነስተኛ ጽሑፍ ለዚህ መልስ የሚሆን ሃይማኖታዊ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎችን ይዟል የመዘጋጀቱ ዋናው አላማውም ይህ ነውና ። ሲቀጥል ከባሕረ ሐሳብ ትምህርቶች ውስጥ በቅድሚያ የአጽዋማትና የበዓላት ጉዳይ ሊታወቅ እና ሊረዳ ስለሚገባ ይህን ቀለል ያለ ፅሁፍ እቅርቤአለሁ።

የቅዱስ ዲሜጥሮስ ታሪክ

ቅዱስ ዲሜጥሮስ ጌታችን በአረገ በመቶ ሰማንያ ዘመን በእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ተሾመ ። በተሾመም በ27 ዘመን መንፈስ ቅዱስ ባሕረ ሐሳብ የተባለ የቁጥር መጽሐፍት ገለጸለት።

ታሪኩም እንዲህ ነው፡-

አርማስቆ ; ደማስቆ የሚባሉ ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ፤ በርኃብ ምክንያት ብሔረ ሞዓብ ተሠደው ይኖሩ ነበር። ሚጠታቸው ሳይደርስ (ከመመለሻቸው በፊት) የልዕልተ ወይን አባት በድንገት ሞተ። ከዚህ በኋላ ልዕልተ ወይን ከዲሜጥሮስ ጋር በአንድ በአጎቷ ቤት አደጉ። አካለ መጠን ሁለቱም ሲደርሱ አሕዛብ የበዙበት ምዕመናን ያነሱበት ዘመን ነበርና ንጹሐ ነፍስ ከሚፈርስ ንጹሐ ሥጋ ይፍረስ ብለው ዲሜጥሮስንና ልዕልተ ወይንን አጋቧቸው። ከዚህም በኋላ ስርዓተ መረዓዊ ወመርዓት(የሙሽሮች ስርዓት) ያድርጉ ብለው መጋረጃ ጥለውባቸው ወጡ። ልዕልተ ወይንም ወንድሜ ይህን ነገር ያሰብከው እኔን ንቀህ ነው ወይስ ተዘምዶውን ነው አለችው። እኔስ አንችንም ተዘምዶውን ንቄ አይደለም የእናትና የአባቴን ፈቃድ እፈጽማለሁ ብየ ነው እንጅ አላት። ፈቃድሽማ ከሆነ በድንግልና እንኑር አላት እርሷም መልካም ይሁን አለችው። እንኪያውስ የተፋታን እንደሆን አንችን ለሌላ እኔንም ለሌላ ያጋቡናልና በአንድ እንኑር አላት። እሽ አለችው ፤ ከዚህ በኋላ በአንድ አልጋ ተኝተው በአንድ ምንጣፍ አንጥፈው አንድ ልብስ ለብሰው ለ48 ዘመን ኑረዋል።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ቀኝ ክንፉን ለእርሱ ግራ ክንፉን ለእርሷ አልብሷቸው አድሮ ጧት በአምሳለ ርግብ በመስኮት ወጥቶ ሲሔድ ያዩት ነበር።

“ንሕነሰ ንሬኢ ዘከመ ገጸ መልአከ እግዚአብሔር ንስረ ወይጼልል ክንፎ ዘየማን ላዕሌየ ወክንፎ ዘጸጋም ላዕሌሃ እምጊዜ ንነውም እስከ ጊዜ ጽባሕ ወውእቱ ጊዜ ይትባእ” እንዲል።

ከዚህ በኋላ ዩልያኖስ የሚባል የማርቆስ 11ኛ ሊቀ ጳጳስ ነበር ህዝቡ ተሰብስበው በመምጣት አባታችን አንተ አፈጀህ ከአንተ ቀጥሎ የሚሾመውን ሊቀ ጳጳስ ንገረን አሉት። እናንተም ጸልዩ እኔም እጸልያለሁኝ ብሎ ሱባኤ ገባ። ከዚህም በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ መጥቶ ያለ ግዜው የደረሰ ሦስት የወይን ዘለላ ይዞ የሚመጣ ሰው አለ፤ከአንተ ቀጥሎ የሚሾመው እሱ ነው ብሎ ነግሮታል ። እርሱም ሱባዔውን ሲፈጽም ሰዎቹን አገኛችሁ አላቸው፤እኛስ አላገኘንም አሉት። እኔ ግን አግኝቻለሁኝ

አላቸው፤ያለ ጊዜው የደረሰ ሦስት የወይን ዘለላን ይዞ የመጣ ሰው አለ፤ ከእኔ ቀጥሎ የሚሾመው እርሱ ነው አላቸው።

ይህም ድሜጥሮስ ድኮ ታጣቂ፤ሞፈር አራቂ፤ወይን አዕዳቂ ነበር። ከዕለታት በአንድ ቀን ወይን ለማቅናት ወደ ወይን ቦታ ቢገባ ያለ ጊዜው የደረሰ ሦስ የወይን ዘለላ አገኘ።ወስዶ ለሚስቱ ሰጣት፤እርሷም ይህ ለእኛ አይገባም ወስደህ ለሊቀ ጳጳሱ አበርክተህ አቡነ ዘበሰማያት ተቀብለህበትና አለችው። እርሱም ለጳጳሱ አበርክቶ አቡነ ዘበሰማያት ተቀብሎበት ሲመለስ ከእን ቀጥሎ የሚሾመው ይህ ነው ብሏቸዋል። አንድም ሊቀ ጳጳሱ አልዋለም አላደረም ዕለቱን ሞቷል። ቀብረው ሲመለሱ ደረሰ፤ እርሱንም ተሾምልን አሉት? እርሱም እን ደንቆሮ በሊቁ ወንበር ፤እን ባሕጉ በባለ ንጽሑ ወንበር እንደምን አድርጎ ይኾንልኛል አላቸው። አባታችን ነግሮናልና ተሾምልን አሉት።በሀገራችሁ ሊቀ ጳጳስ ሲሾም ምን ሠርቶ ይሾማል አላቸው። እነርሱም አንቀፀ ብፁዓንን፤አንቀፀ አባግዕንን አንብቦ ተርጉሞ ይሾማል አሉት። እርሱም አንቀፀ ብፁዓንን፤አንቀፀ አባግዕንን አንብቦ ተርጉሞ ተሹሟል። ወዲያው 81 መጻሕፍት ለገልፀውለታል።

ከዚህ በኋላ የሕዝቡ ኃጢአት ተገልጾለት አንተ በቅተሃል ቁረብ፤ አንተ አላበቃህም አትቁረብ እያለ ይከለክላቸው ገሥመር። እጩጌነት ከሚስት እንዲሉ፤ እርሱ በማይገባው በንጹሑ በማርቆስ ወንበር ተቀምጦ እኛን አንተ በቅተሃል፤ አንተ አልበቃህም አትቀበል እያለ ይከለክለን ገሥመር ብለው አሙት። አምተውትም አልቀሩ የሐሰት ምስክር ዋጅተው ፤ ከሳሽ አስነስተው ለንጉሡ ሰደዱለት። እርሱም በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾለት በአገልግል አድርጎ በውሃው ላይ ዳመጦ፤በዳመጠው ላይ እሳትን አድርጎ ለንጉሱ ላከለት። ንጉሡም ዳመጦውን እሳቱ ሳያቃጥለው፤እሳቱን ውሃው ሳይጠፋው አይቶ ሰዋቹን አስጠርቶ ይህ ሰው ደግ ሰው ነው በእኔ የንግስና ዘመን አይከሰስም አይወቀስም ብሏቸዋል።የእነርሱም መልእክተኞች በፊት ቀን ተነስተው በሠላሳ ቀን ደርሰዋል፤የእርሱ መልእክተኞች በኋላ ተነስተው በሰባት ቀን ደርሰዋል።የእነሱ መልእክተኞች በፊት ተነስተው በሠላሳ ቀን መድረሳቸው በሠላሳ የመደገፍ ምሳሌ ነው።የእርሱ መልእክተኞች በኋላ ተነስተው መሰባት ቀን መድረሳቸው በሰባት የመደገፍ ምሳሌ ነው።

ከዚህ በኋላ መልአኩ ተገላጾ ሕዝቡ አንተን እያመሙ የሚጎዱ ኹኖአልና በአንተና በሚስትህ መካከል ያለውን ምስጢር ለሕዝቡ ግለጽላቸው አለው።**"ክሥት ዘሀሉ ማእከሌከ ወማእከለ ብእሲትከ"** እንዲል እርሱም የመልአኩን ትእዛዝ በመቀበል ሕዝቡን እንጨት እየያዛችሁ ተሰብሰቡ ብሎ አዋጅ አስነገረ።ሕዝቡም ዕንጨት እየያዙ ተሰበሰቡ። ያንን የሕዝብ ዕንጨት እንደ ደመራ ደምሮ ሊቀ ዲያቆኑን ስወጣ በእሳት እንድታቃጥለው ብሎ ቅዳሴ ገባ።ከቅዳሴ ከወጣ በኋላ ሒዶ ከፍሕመ መካከል ይጸልይ ገሥመር፤"**ሕዝቡም በምን ይሞታል ስንል ዛሬስ በገንዛ እጁ ከእሳት ገብቶ ሊሞትልን ነው አሉት"**። ሚስቱም "**ከቤተ ደናግል**" ነበረችና ልዕልተ ወይን ልዕልተ ወይን ብሎ ጠርቶ "**ስፍሒ ዐጽፍኪ/ነጠላሽን ዘርጊ/ አላት**። የእሳቱን ፍሕም በእጁ እያፈሰ ከልብሷ ላይ አደረገላት። እርሷም ወንዱን ሴቱን እጅ ነስታ ብታደርገው ልብሷ "**ከዘሐው ከማኁ**" አንድስ እንኳን ሳይቀነብር ነገኝቷል። እርሱም እንዲህ አለ፤ ከተጋባን 48 ዘመናችን ነው፤ከአንድ አልጋ ተኝተን፤ ከአንድ ምንጣፍ አንጥፈን፤ አንድ ልብስ ለብሰን ስንኖር በግብረ ሥጋ አላተዋወቅንም አላቸው።ሕዝቡም "**ጎድግ ለነ ስረይ ለነ**" ...ኃጢአታችንን ተውልን ፤ይቅርም በለን ብለው ለጫማው ወደቁ።እርሱም "**ይፍታህ ወይጎድግ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ**" **"ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ይቅር ይበላችሁ ለኃጢአታችሁ የተፈታችሁ ሁኑ" ብሎ ናዝዟቸዋል፤ ኑዛዜም ያን ጊዜ ተዘምሯል።**

የአጽዋማትና በዓላት ሥርዓት

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ድሜጥሮስ እንዲህ አለ፤ እንስ የጌታዬ ፈቃድ ቢሆን ጾመ ነነዌ፤ዐቢይ ጾም፤ ጾመ ሐዋርያት **ከሰኞ**፣ደብረ ዘይት ፤ሆሣዕና፤ትንሳኤ፤ጰራቅሊጦስ **ከእሑድ**፣ ረክበ ካህናት፤ጾመ ድኅነት **ከረቡዕ**፣ ዕርገት **ከሐሙስ**፣ ስቅለት **ከአርብ** ባይወጣ መልካም ነበር ብሎ ተመኘ፡፡

ከዚህም በኋላ መላአኩ መጥቶ ሁልጊዜ በተምኔት ይፈጸማል ከቀኑ 7 ሱባዔ፤ከሌሊቱ 23 ሱባዔ ገብተህ እየው አለው፡፡ ስለምን የቀኑን አሳንሶ የሌሊቱን አበዛው ቢሉ ቀን ሲፈርድ ሲተች፤የተጣላ ሲያሰታርቅ ፤የተበደለ ሲያስክስ ፤ የተቀማ ሲያስመልስ ይውላል፡፡ሌሊት ግን ይህ ሁሉ የለበትምና ስለዚህ ነው፡፡ የመዓልቱን 7 ሱባኤ ሲበዛ 49 ይሆናል፡፡ለዚህ 30 ሲቀነስ 19 ይተርፋል፡፡ ይህን መጥቅዕ ብለህ ከዕለታት ተውሳክ ጋር ደምረህ የአጽዋማትና የበዓላት ማውጫ ይሁንህ ብሎታል፡፡ የሌሊቱን 23 ሱባዔ ሲበዛ 161 ይሆናል፡፡ ይህ በ30 ሲቀመር 5 ሱባዔ ሆኖ 11 ይተርፋል፡፡ ይህን አበቅቴ ብለህ ከሕፀፅና ከዕለት ጋር ደምረህ የሌሊት ማውጫ ይሁንህ ብሎታል፡፡

የቅዱስ ድሜጥሮስ መልእክት

ቅዱስ ድሜጥሮስ የአጽዋማትና የበዓላት ኢየዐርጋቸውንና ኢይወርዳቸውን በአንድ አብይ ቀመር ቀምሮ ለሦስቱ ሊቃነ ጳጳሳት አራተኛም በኢየሩሳሌም ላለው ኤጲስቆጶስ ሰደደላቸው፡፡ እነርሱም ተቀብለው ሐዋርያት በዲድስቅልያ ካስተማሩት ጋር አንድ ሆኖ ቢያገኙት ደስ ብሏቸው አስተምረውታል፡፡ ከሁሉ ደርሷል፤ ሠለስቱ ምዕትም ጉባኤ ሰርተው አስተምረውበታል፡፡

“ወአስተላጸቅዋ ለጾመ አርብዓ ቅድስት ምስለ ስሙነ ሕማማት ወሠርዑ አበቅቴ ውስተ አብያተ ክርስቲያን(አርባ ጾምን ከሰሙነ ህማማት ጋር አዛመዱት)” እንዲል፡፡ቁጥርም ቢሳሳት የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ይመስክር ብለዋል፤**ወአዘዙ ኩሉ ዘስሕት አበቅቴ ወሐሳበ ይትመራሕ በሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ) እንዲል፡፡**

ምዕራፍአንድ(፩)

፩.ባሕረ-ሐሳብ

፩.፩ ባሕረ-ሐሳብ ምንድን ነው?



ስለዚህ፡-

- ባሕር ማለት ዘመን ማለት ነው።
- ሐሳብ ማለት ደግሞ ቁጥር ማለት ነው።

ቃሉ የተወሰደው ከግዕዝ ቋንቋ ሲሆን ይህም ሓሰበ ፤ቆጠረ ከሚለው ግስ የወጣ ነው ። የእነዚህ የሁለቱ ቃላት ጥምረት (ባሐረ ሐሳብ) ትርጉሙም "ቁጥር ዘመን ወይም ቁጥር ያለው ዘመን" ማለት ነው። ዘመን ይቆጠራል ፤ ዘመን ይለካል ፤ ይሰፈራል ፤ይሀን የመለካት የመስፈር እና የመቆተር ባህሪ ለማሳየት ባሕረ ሐሳብ ተብሏል።

፩.፪. ስለምን ባሕር ተባለ

1ኛ. ባሕር መባሉ "ባሕር" እስኪለምዱት ድረስ ያስፈራል ከለመዱት በኋላ ግን እንደልብ እንደሆነ ሁሉ ይህ የዘመን አቆጣጠር ከለመዱት በኋላ ትምህርትን፤ ምስጢርን ያሳውቃልና።

2ኛ.አንድም ባሕር ከለመዱት በኋላ ከመሠረቱ ወርደው አሸዋ ይዘው ይወጣሉ ይህን መጽሐፍም ከለመዱት ብዙ ምስጢራትን ያስመረምራል፤ያሳውቃልና።

ምሳሌ፡-

- ምህዋረ ፀሐይን
- ምሳክወ ፀሐይን
- ምእዛረ ፀሐይን
- ወራትን
- ኬክሮስን
- ኬንትሮስን
- እለታትን
- ዓመታትን

እሊህንና የመሳሰሉትን ምስጢራትን በማሳወቁ ባሕር ሊሉት ችለዋል።

3ኛ. አንድም የባሕር አዝዋሪቱ ብዙ ነው የዚህም የዘመን አቆጣጠር ትምህርት መንገዱ፤ስልቱ ብዙ ነውና አባቶቻችን በባሕር መስለው ባሕረ ሐሳብ ብለውታል።

4ኛ. አንድም በባሕር ያለውን ሁሉኑ ነገር ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ሰው እንደማያውቀው በዘመን የሚደረገውን ሁሉ እግዚአብሔር እንጅ ሰው አይውቀውምና ቅዱሳን አባቶቻችን ባሕረ ሐሳብ ሊሉት ችለዋል።



፩.፪.፩. መርሐ ዕውር (የዕውር መምሪያ)

መርሐ ዕውር አላዋቂዎችን ከድንቁርና ጨለማ ወደ ዕውቀት ብርሃን ደረጃ መርቶ ከብልዕግና የሚያደረስ መጽሐፍ ሲሆን በውስጡም የአጽዋማትንና የበዓላትን አወጣጥ መንገድ ፤ ኢያዓርጋቸውንና ኢይወርዳቸውን(ከፍተኛውን ገደብና ዝቅተናውን ገደብ)አጠቃሎ የያዘ ነው።

፩.፪.፪. ሐሳበ አቡሸህር

ሐሳበ አቡሸህር የሚለው መጠሪያ ተሰጠው በደራሲው ስም ሲሆን በውስጡም የፀሐይን፤ጨረቃንና የከዋክብትን እንዲሁም የስነ ፈለክን ነገር በጠቅላላ የሚናገር ቅዱስ መጽሐፍ ነው።

፩.፪.፫. ሐሳበ ፈለክ

ሐሳበ ፈለክ ማለት ደግሞ የብርሃናቱን ማለትም የፀሐይን፤የጨረቃን፤የከዋክብትን መመላለስ ወይም አዘዋወርን እና ሐሳበ ነፍሳትን የሚመለከት ክፍል ነው።

- እነዚህ ሦስት ክፍሎች በተናጥል ለማየት እጅግ ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን አባቶቻችን አንድ መጽሐፍ አድረገው ሰይመውታል ይህም ባሕረ ሐሳብ ነው።

፩.፫.ባሕረ ሐሳብ እንዴት ተገኘ?

ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ባሕረ ሐሳብን ለማወቅ ይመኙ እንደነበረ የተለያዩ የታሪክ መጽሐፍት ይዘክራሉ። ሆኖም ግን የተገለፀው በእስክንድርያ 11ኛ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ ከተሾመው ከዮልያየስ በኋላ 12ኛ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ ለተሾመው ለቅዱስ ድሜጥሮስ ነው። ይህ ቅዱስ ድሜጥሮስ ለዚህ ከመብቃቱ በፊት ምንም አይነት የቤተ ክርስቲያን ትምህርት እና ዕውቀት ያልነበረውና ገበሬ የነበረ ሰው ነበር። በኋላ ግን መንፈሳዊ የዕውቀት ፀጋ ተገልያለት በማርቆስ ወንበር ላይ በመቀመጥ 12ኛው የእስክንድርያ ታላቅ ጳጳስ ለመባል በቅቷል።



ባይወጡ እያለ ይህ ቅዱስ አባት ምኞት ተመኘ። ለምኞቱ ምክንያቱ ደግሞ ቀናቶቹ የበዓላቱና የአጽዋማቱ ጥንተ ዕለታት (በዓላቱና አጽዋማቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የዋሉባቸው ዕለታት)መሆናቸው ነው። በዚህ ምኞት ላይ እያለ መልአክ ወደ እርሱ መጥቶ ፤ ነገር በምኞት እንደማይገኝና ሱባኤ መግባት እንዳለበት ነገረው ። ሱባዔውም ከቀኑ ሰባት ሱባዔ፤ከሌሊቱ ደግሞ ሃያ ሦስት ሱባዔ እንዲሆን አዘዘው። አያይዞም ፤ ከቀኑ ሰባት ሱባዔ ..መጥቅዕ ፤ከሌሊቱ ሃያ ሦስት ሱባዔ ደግሞ አበቅቴ ይሆን ዘንድ ነገረው።ይህንን የነገረው የተመኘው ምኞት ይሳካ ዘንድ መጥቅዕና አበቅቴ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ዐብይ ነገሮች በመሆናቸው ነው።

፩.፬. መጥቅዕ

መጥቅዕ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፤የአይሁድ አዲስ አመት መባቻ ፣ነጋሪት፣ደወል ማለት ነው ። አንድም መጥቅዕ ማለት የመጀመሪያው የፀሐይ ዓመታዊ ጉዞ አልቆ ሁለተኛውን ዐውደ አበቅቴ ለመሙላት የሚያስፈልግ የቀን መጠን መጥቅዕ ይባላል ።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉሙም መጥቅዕ ማለት ፦

፩. ደወል መቀስቀሻ ይባላል ፤ የተጀመረውም በኖህ ዘመን ነው (ዘፍ ምዕ ፮ ቁ ፳-፳፩)

፪. የእስራኤላውያን የበዓል ስም ነው (ዘሌ ምዕ ፳፫ ቁ ፳፬-፳፭ ፤ ዘኁል ምዕ ፳፱ ቁ ፩-፮)

፫. መለከት ማለት ነው (ዘኁል ምዕ ፲ቁ ፩-፲)

መጥቅዕ ከዕለታት ተውሳክ ጋር ሲደመር ለአጽዋማትና ለበዓላት ማውጫ ያለግላል። ተውሳክን ወደ ፊት የምናየው ይሆናል። ስለዚህ ወደ ነገራችን እንመለስና ከላይ በታዘዘው መሰርት ከቀኑ ሰባት ሱባዔ መጥቅዕ እንዴት እንደሚገኝ እንመለከታለን።

አንድ ሱባዔ ከስባት ቀናት ጋር እኩል ነው ወይም ሰባት ሱባዔ ነው ማለት ነው ስለዚህ የቀኑን ሰባት ሱባዔ ወደ ቀን እንቀይራለን። ማለትም....

1 ሱባዔ = 7 ቀናት

7 ሱባዔ = X ቀን ይሆናል

$$\mathbf{X} = \frac{\textbf{7 ሱባኤ}\times\textbf{7 ቀን}}{\textbf{ለ1 ሱባኤ}}$$

X = ፵፱(49) ቀናት ይሆናል።

ቀናቱ 49 መሆናቸውን ካወቅን በኋላ ወደ መጥቅዕ እንቀይራቸዋለን። ይህም የራሱ የሆነ ህግ አለው ፤ አባዝተን ያገኘነው ቁጥር ከሰላሳ ከበለጠ ለሰላሳ በማካፈል ቀሪውን እንወስዳለን ማለት ነው። ምክንያቱም በባሕረ ሐሳብ ትምህርት ቁጥሮችን ስናካፈል(ስንገድፍ) ብዙን ጊዜ ድርሻውን ጥለን ቀሪውን እንይዛለን።

የሚፈለጉት ቁጥሮች አብዛኛውን ጊዜ የሚያርፉት ቀሪው ላይ ነው። ስለዚህ ያገኘነው ቀን ከሰላሳ ስለበለጠ ለሰላሳ በማካፈል(በመደገፍ) ጥንተ መጥቅዕን እናገኛለን ማለት ነው ።

ስለዚህ፡-

መጥቅዕ $= \frac{\text{፵፱}(49)}{(\text{፴})30} =$ ፩(1) ቀሪ ፲፱(19) ስለዚህ ጥንተ መጥቅዕ ፲፱(19) ነው ማለት ነው።

- ፵፱ (49).....ተካፋይ
- ፴ (30).....አካፋይ
- ፩ (1).....መጠነ ራቢት (ድርሻ)..የዘመን መለወጫን ለማወቅ ይረዳናል።
- ፲፱ (19).....ቀሪ

ስለዚህ ቀሪው ፲፱ (19) ስለሆነ ጥንተ መጥቅዕ ነው ማለት ነው።

አራቱ ስሌቶች በጥንተ ስሌትና በዓለማዊ ስሌት



፩.፫. አበቅቴ

_____አበቅቴ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ ተረፈ ዓመት ወይም ተረፈ ጨርቃ ማለት ነው ። ማለትም አበቅቴ ማለት በፀሐይ ዓመትና በጨርቃ ዓመት መካከል ያለ የቀናት ልዩነት ማለት ነው። ስለዚህ በጨረቃ አቆጣጠር በዓመት ውስጥ ያሉት ቀናት ተደምረው በፀሐይ አቆጣጠር ካሉት ዓመታት ቀናት ጋር ተነጻጽሮ የሚገኝ ልዩነት ነው። አንድም አበቅቴ ከሕፀፅና ከዕለት ጋር ተደምሮ የሌሊት ማውጫ ያገለግል ዘንድ ለቅዱስ ድሜጥሮስ ተነግሮታል።

ከላይ እንዳየነው አበቅቴ የሚገኘው ከሌሊቱ 23 ሱባዔ ነው ስለዚህ ወደ ቀን እንቀይራለን ማለት ነው።

፩ (1) ሱባዔ = ፯ (7) ቀናት

፳፫ (23) ሱባዔ =ስንት ይሆናል X

"X"ን ለማግኘት፡-

$$X = \frac{\text{ጽፐ}(23)\ \text{ሱባዔ}\ X(\text{ሲሰበሰብ})\ \text{፯}(7)\ \text{ቀናት}}{\text{ለ፩}(1)\ \text{ሱባዔ}} = \text{፻፷፩}\ (161)\ \text{ቀናት ይሆናል።}$$

እነዚህ ወደ አበቅቴ ሲቀየሩ፡,-

$$\text{አበቅቴ} = \frac{\text{፻፷፩}(161)\ \text{ቀናት}}{\text{ለ፴}(30)}$$

አበቅቴ = ፭ (5) ቀሪ ፲፩ (11)

ቀሪው 11 ስለሆነ አበቅቴውም 11 ይሆናል ማለት ነው ። ድሜጥሮስ በመልአኩ በተነገረው መሠረት እንዲህ በማድረግ መጥቅዕን 19 ፣ አበቅቴን ደግሞ 11 አድርጎ አውጥቶታል።እነዚህ ለመጀመሪያ ጊዜ የወጡ ቁጥሮች ሁለት መጠሪያዎች ተሰጥቶአቸዋል። 19 ጥንተ መጥቅዕ ተብሎ ሲጠራ ፣11 ደግሞ ጥንተ አበቅቴ ይባላል።

- ጥንተ መጥቅዕና ጥንተ አበቅቴ ሲደመሩ ከሰላሳ መብለጥም ማነስም የለባቸውም ሰላሳ ቢሆኑ እንጅ።
- ጥንተ መጥቅዕ……19
- ጥንተ አበቅቴ……..11

ስለዚህ 11 +(ሲገጠም) 19 = 30 ይሆናል ማለት ነው።

፩.፮. ዘመነ-ወንጌላዊያን

የዘመኑን ወንጌላዊይ ለማወቅ የምንጠቀመው ወይም የምናገኘው እንዴት ነው ቢሉ፡- ዓመተ ፍዳንና ዓመተ ምህረትን መሠረት ያደረገ ነው።

- ዓመተ-ፍዳ(ኩነኔ)……ከመሲሑ ክርስቶስ ልደት በፊት….5500 ዘመን
- ዓመተ-ምህረት(ዘመነ-ደስታ)..የምህረት ዓመት…….ከመሲሑ ክርስቶስ ልደት በኋላ ያለው ዘመን ነው። ሲቀጥል ዓ.ዓን ማግኘት አለብን ዓመተ ዓለምን ካወቅን በአራት(በመደገፍ)በማካፈል ትርፉን እየያዝን የዘመኑን ወንጌላዊ በቀላሉ ማወቅ ይቻላል ማለት ነው።

ስለዚህ፡-

ዓ.ዓ = ዓ.ፍ + ዓ.ም……..ወንጌላዊ ለማወቅ …ዓ.ዓ ሲካፈል ለአራት እናደርገዋል ስለዚህ በባሕረ ሐሳብ ትምህርት ቀሪው ይወሰዳል ብለናልና ቀሪውን እንወስዳለን ማለት ነው።

ትርፉ(ቀሪው)

- ቀሪው 1 ከሆነ ማቴዎስ

- ቀሪው 2 ከሆነ ማርቆስ
- ቀሪው 3 ከሆነ ሉቃስ
- ቀሪው 0(አልቦ) ከሆነ ዮሐንስ ነው በማለት የዘመኑን ወንጌላዊ ማወቅ እንችላለን ማለት ነው።

ምሳሌ. የ2008 ዓ.ም ወንጌላዊን ስንፈልግ ፡-

ዓ.ዓ = ዓ.ፍ + ዓ.ም

ዓ.ዓ = 5500 + 2008

ዓ.ዓ = 7508 ዓ.ዓ

ወንጌላዊ = $\frac{\text{ዓ.ዓ}}{4} = \frac{7508}{4}$ = 1877 ቀሪ 0 ይሆናል ማለት ነው።

- 1877.....መጠነ ራብዒት (ድርሻ)
- ስለዚህ ፡- ቀሪው 0(አልቦ) ስለመጣ የ2008 ዓ፣ም ወንጌላዊው ዮሐንስ ነበር ማለት ነው።

፩.፯ የዘመን መለወጫ

የዘመን መለወጫን ማለትም መስከረም 1 ቀን የባተበትን ቀን ለማወቅ ወይም ለመፈለግ ሦስት ጥንታትን መሠረት አድርገን ዘመን መለወጫውን እናገኛለን ማለት ነው።

- ጥንተ ቀመር.....ማክሰኞ
- ጥንተ ያን.....ረቡዕ(ፀሐይና ጨረቃ የተፈጠሩበት ዕለት)
- ጥንተ ዕለት.....እሑድ....ዓለም የተፈጠረችነት ዕለት

ስለዚህ በእነዚህ በሦስቱ ጥንታት የዘመን መለወጫን መፈለግ እንችላለን።

፩.፯.፩.ጥንተ ቀመር

በጥንተ ቀመር መስከረም አንድ ቀን መቼ እንደዋለ ለማወቅ ፤ ከላይ ያገኘነውን መጠነ ራብዒት ከዓመተ ዓለም ጋር ገጥመን(ደምረን) ለሰባት በመገደፍ(በማካፈል) ትርፉን ወይንም ቀሪውን በመያዝ እና ከማስከኞ ጀምረን በመቁጠር ዕለቱን መወቅ እንችላለን። ወይም

- ቀሪው 1 ከሆነ መስከረም አንድ ቀን የሚውለው .....ማክሰኞ ነው
- ቀሪው 2 ከሆነ መስከረም አንድ ቀን የሚውለው .....ረቡዕ ነው
- ቀሪው 3 ከሆነ መስከረም አንድ ቀን የሚውለው .....ሐሙስ ነው
- ቀሪው 4 ከሆነ መስከረም አንድ ቀን የሚውለው .....አርብ ነው
- ቀሪው 5 ከሆነ መስከረም አንድ ቀን የሚውለው .....ቅዳሜ ነው
- ቀሪው 6 ከሆነ መስከረም አንድ ቀን የሚውለው .....እሑድ ነው
- ቀሪው 7(አልቦ) ከሆነ መስከረም አንድ ቀን የሚውለው ..... ሰኞ ነው ማለት ነው።

$$\text{ጥንተ ቀመር} = \frac{\text{ዓ.ዓ} + \text{መጠነ ራብዒት}}{\text{ለ7}}$$

ምሳሌ፡- የ2008 የዘመን መለወጫ በጥንተ ቀመር ስንፈልግ፡-

ዓ.ዓ ማለት ዓመተ ምህረት(ዘመነ ስጋዌ) ከዓመተ ፍዳ(ኩነኔ) ጋር ሲገጠም ማለት ነው። ስለዚህ መጠነ ራብዒቱንም ማግኘት ስላለብን ለአራት እናካፍላለን ማለት ነው።ስለዚህ ለአራት በማካፈል ድርሻውን መጠነ ራብዒት ብለን እንጠረዋለን ማለት ነው።

$$\text{ዓ.ዓ} = \frac{\text{ዓ.ም} + \text{ዓ.ፍ}}{\text{ለወንጌላዊያን}} = \frac{2008 + 5500}{4} = \frac{7508\ \text{ዓ.ዓ}}{4} = 1877\ \text{ቀሪ}\ 0$$

$$\text{ስለዚህ የዘመን መለወጫ} = \frac{\text{ዓ.ዓ} + \text{መጠነ ራብዒት}}{7} = 1340\ \text{ቀሪ}\ 5$$

ስለዚህ ከማክሰኞ ጀምረን ስንቆጥር 5 ቅዳሜ ላይ ታበቃለች ስለዚህ የ2008 የዘመን መለወጫ (መስከ...1 ቀን) ቅዳሜ ነበር ማለት ነው። ነገር ግን ቀሪያችን 7(አልቦ) ከመጣብን መስከረም አንድ የሚውለው ሠኑይ (ሰኞ) ነው ማለት ነው።ምክንያቱም ቀሪው አልቦ ነው ማለት የሳምነቱ መጨረሻ ሱባዔ የሞላበት ቀን ማለት ነው።

፩.፯.፪.ጥንተ ዖን

ጥንተ ዖን = ዓመተ አለም ሲደመር(ሲገጠም)መጠነ ራብዒት ሲካፈል ለሠባት በማድረግ ከቀሪው ላይ አንድ በመቀነስ መስከረም አንድ ቀን የባተበትን ዕለት ማወቅ እንችላለን ማለት ነው።ለምን አንድ እቀንሳለን ቢሉ ፀሐይ፣ጨረቃና ከዋክብት በአንድ ቀን ዘግይተው ተፈጥረዋልና(ዘፍ ፩)። ስለዚህ ያገኘነውን የቀሪ ቁጥር ከረቡዕ ጀምረን በመቁጠር ዕለቱን መወቅ እንችላለን ማለት ነው።

$$\text{ጥንተ ዖን} = \frac{\text{ዓ.ዓ} + \text{መጠነ ራብዒት}}{\text{ለሠባት}} - \text{አንድ}$$

ምሳሌ፡-የ2008ን የዘመን መለወጫ በጥንተ ዖን ስንፈልግ፡-

$$= \frac{7508 + 1877}{7} - 1 = 1340\ \text{ቀሪ}\ 5 - 1$$

= 4 ስለዚህ ከረቡዕ ጀምረን ስንቆጥር የዘመን መለወጫው ቅዳሜ ይሆናል ማለት ነው።

፩.፯.፫.ጥንተ ዕለት

በጥንተ ዕለት የዘመን መለወጫን ወይም መስከረም አንድ ቀን መቼ ቀን እንደዋለ እናውቃለን ቢሉ ከላይ እናደየነው ዓ.ዓን ከመጠነ ራብዒት ጋር ደምረን (ገጥመን) ለሰባት በማካፈል(በመገደፍ)ያገኘነውን ቀሪ ሁለት በመደመር(በመግጠም) ፣ከእሁድ ጀምረን በመቁጠር የዘመን መለወጫውን ዕለት ማወቅ እንችላለን ማለት ነው።

$$\text{ጥንተ ዕለት} = \frac{\text{ዓ.ዓ} + \text{መጠነ ራብዒት}}{\text{ለሰባት}} + \text{ሁለት}$$

ምሳሌ፡-የ2008ን የዘመን መለወጫ በጥንተ አን ስንፈልግ፡-

$$= \frac{7508 + 1877}{7} + 2$$

= 1340 ቀሪ 5 + 2 = 7 ይሆናል ማለት ነው ። ስለዚህ ከእሁድ ጀመረን በመቁጠር የዘመን መለወጫውን ማወቅ እንችላለን ማለት ነው።



1) 23 ሱባዔ
2) አበቅቴ
3) መጥቅዕ
4) 7 ሱባዔ
5) ጥንተ መጥቅዕ
6) ድሜጥሮስ
7) ጾመ ነነዌ፣ዐብይ ጾምና ጾመ ሐዋርያት
8) ጥንተ አበቅቴ
9) ዕርገት
10) ርክበ ካህናትና ጾመ ድኅነት

ሀ) ረቡዕ
ለ) 161 ቀናት
ሐ) 49 ቀናት
መ) 19
ሠ) 11
ረ) ሰኞ
ሰ) ኀሙስ
ሸ) ደወል
ቀ) የእስክንድርያ 12ኛ ሊቀ ጳጳስ
በ) ከሕፀፅና ከዕለታ ጋር ተደምሮየሌሊት ማውጫ ይሆናል



ምዕራፍ ሁለት(፪)

፪.አዕዋዳት

አዕዋዳት የሚለው ቃል “ዖደ” ከሚለው የግዕዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙም “ዞረ” ማለት ሲሆን ፣ ዐውድ ማለት ደግሞ ዙሪያ ወይም ክበብ ማለት ነው ። ይህም ቃል የብዙ ቁጥር አመልካች ሲሆን ይህም አዕዋዳት ይባላል።ስለዚህ አዕዋዳት ማለት ለዓመተ ዓለም መስፈሪያና መቁጠሪያ የሚያገለግሉና ዖደታቸውን ጠብቀው የሚመላለሱ መለኪያዎች ማለት ነው።

ለዓመተ ዓለም መሥፈሪያ የሚሆኑ ሰባት አዕዋዳት አሉ። እነርሱም ፡-

- ዐውደ ዕለት
- አውደ ወርኀ
- ዐውደ ዓመት
- ዐውደ አበቅቴ(ዐውደ ንዑስ ቀመር)
- ዐውደ ፀሐይ
- ዐውደ ማኅተም(ማእከላዊ ቀመር)
- ዐውደ አብይ ቀመር

፪.፩ ዐውደ ዕለት

ዐውደ ዕለት ማለት ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ያሉት የሰባት ዕለታት ዑደት (መመላለስ) ማት ነው። እሀዚህ ሰባት ቀናት ወርን ለማስገኘት በየተራ ይመላለሳሉ። አንድ ዐውደ ዕለት ሠባት ዕለታት ማት ሲሆን በሰባት ዕለታት ጎብረት አንድ ዐውደ ዕለት ይገኛል ። በአንድ ዐውደ ዕለታ አቃፊነት ሰባት ኾርለታት ይገኛሉ፤ ሰባቱ ዕለታት ተራቸውን ጠብቀው የመመላለሳቸው ሒደት ዐውደ ዕለት ተብሎ ይጠራል።

፪.፩.፩ የዕለት መጀመሪያ(ጥንተ ዕለት)

እንደ አጀማመራቸውና መነሻነታቸው ዕለታት የሚታወቁባቸው ጥንታት ወይም ስያሜ አላቸው።

እነርሱም፡-

- ✓ እሑድ ...ጥንተ ዕለት ይባላል ምክንያቱም ዓለም ተፈጥሮበታልና፡፡
- ✓ ማክሰኞ ...ጥንተ ቀመር(የቁጥር መጀመሪያ) ይባላል ምክንያቱም መዕለተ ሠሉስ ዕፅዋትና አዝርዕት የተፈጠሩበትና ቁጥር የተጀመረበት ዕለት መሆኑ ነው፡፡
- ✓ ረቡዕ.... ጥንተ ያን ይባላል ምክንያቱም ፀሐይ፣ጨረቃና ከዋክብት የጠፈጠሩበት ዕለት ነውና ። ያን ማለትም ፀሐይ ማለት ነው፡፡
- ✓ ሰኞ..... የቁጥር ወይም የቀመር መጨረሻ ያባላል፡፡
- ✓ ሐሙስ ..... ጥንተ ወር
- ✓ አርብ .....ጥንተ አዳም
- ✓ ቅዳሜ .....ጥንተ ዕረፍት ይባላሉ፡፡

፪.፪ <u>ዐውደ ወርኀ</u>

ዕለታት በዐውዳቸው መሠረት እየተመላለሱ ወርን ያስገኛሉ፡፡ አንድ ወር በፀሐይ 30 ዕለታትን ያጠቃልላል፣ በጨረቃ ደግሞ አንድ ጊዜ 29፣ አንድ ጊዜ 30 ነው፡፡በዚህ መሠረት ዐውደ ውርኀ ማለት የወራት መመላለስ ማለት ነው፡፡

፪.፫ <u>ዐውደ ዓመት</u>

ዐወደ ዕለት ማለት በፀሐይ 365 ዕለት፣ከ15 ኬክሮስ፣ከ6 ካልዒት(365 ቀን፣ከ6 ሰዓት፣ከ2 ደቂቃ) ሲሆን ፣ በጨረቃ ደግሞ 354 ዕለት ከ22 ኬክሮስ፣ከ1 ካልኢት፣ከ37 ሳልሲት፣ከ52 ራብኢት፣ከ48 ሐምሲት(354 ቀን፣ከ48 ደቂቃ፣ከ39 ሰከንድ) ነው ። ስለዚህ ዐውደ ዓመት ማለት በየዓመቱ እየዞረ የምናገኘው ነው ማለት ነው ።

እንዴት ስድስት ሰዓት ሊመጣ ቻለ???

1 ቀን = 60 ኬክሮስ

1 ኬክሮስ = 60 ካልዒት

1ካልዒት = 60 ሣልዒት ነው፡፡

ስለዚህ፡- 1 ቀን = 24 ሰዓት = 60 ኬክሮስ

24 ሰዓት = 60 ኬክሮስ ከሆነ

ሀ = 15 ኬክሮስ ስንት ሰዓት ይሆናል

$ሀ$ = 24 ስዓት X 15 ኬክሮስ ? = 60 ኬክሮስ..... = $\frac{360 \text{ ስዓት}}{60}$

ሀ = 6 ስዓት

ስለዚህ 6 ስዓት = 15 ኬክሮስ ፤ በመሆኑም ዐውደ ዓመት በፀሐይ 365 ዕለት ከ6 ስዓት ነው ማለት ነው ። ወገን ልብ ልናደርገው የሚገባ 6 ስዓቷ በአንድ ዓመት ነው ወይም የአንዱ ወንጌላዊ ናት ለአራቱ ወንጌላዊ ስድስት ስድስት ስዓት ነው እናም አራተኛ ዓመት ላይ አንድ ቀን ወይም 24 ስዓት ሆና **በሉቃስ ትፈፀማች** ማለት ነው።

፪.፩ ዓውደ አበቅቴ(ንዑስ ቀመር)

ዓውደ አበቅቴ በየ 19 ዓመቱ ዞሮ የሚመጣ ነው። ይህ ማለት ዓመት አንድ ተብሎተቆጥሮ አስራ ዘጠኝ ሲሞላ አንድ ዐውደ አበቅቴ ይባላል። አንድ ዐውደ አበቅቴ 19 ዓመታትን በውስጡ ይይዛል ፤ 19 ዓመታት ደግሞ በአንድ አበቅቴ ሥር ይጠቃለላሉ።19 ዓመት አንድ ዐውደ አበቅቴ የተባለበት የራሱ የሆነ ምክንያት አለው ፤ እርሱም፡-በ19 ዓመት አንድ ጊዜ ፀሐይና ጨረቃ በተፈጠሩበት መስኮት ግንኙነት ያደርጋሉ። ያ ማለት የራሳቸውን ዙረት ሲዞሩ ኖረው ልክ በ19 ዓመታቸው አንድ የጋራ ነጥብ ላይ ይገናኛሉ ማለት ነው። በዚህ ጊዜ አበቅቴና መጥቅዕ ዜሮ ይሆናሉ።በ19 ዓመታቸው የተገናኙ ፀሐይና ጨረቃም ዓውደ ዓመታቸውን አንድ ላይ እኩል ይጀምራሉ። ስለዚህ ዓውደ አበቅቴ ማለት በየ 19 ዓመቱ ዞሮ የምናገኘው ነው ማለት ነው።

፪.፪ ዓውደ ፀሐይ

በዓውደ አበቅቴ ላይ እንዳየነው ፀሐይና ጨረቃ ይገናኛሉ ብለን ነበር ። ስለዚህ በዓውደ ፀሐይ ደግሞ በየ28 ዓመቱ ረቡዕና ማቴዎስ ይገናኛሉ።ረቡዕ ፀሐይ የጠፈጠረችነት ቀን ሲሆን፤ ማቴዎስ ደግሞ የወንጌላዊያን መጀመሪያ ነው ። እነዚህ ሁለት ነገሮች በሃያ ስምንት ዓመቱ ይገናኛሉ ማለት ነው።

፪.፫ ዓውደ ማእከላዊ ቀመር(ማኑተም)

በ76 ዓመት አንድ ጊዜ አበቅቴና ወንጌላዊ ይገናኛሉ። አበቅቴው 18 ሲሆን ወንጌላዊው ደግሞ ዮሐንስ ነው።18 አበቅቴ ለአበቅቴ የመጨረሻ ሲሆን ፤ ዮሐንስ ደግሞ በወንጌላዊያን የመጨረሻ ነው ። ስለዚህ እነዚህ ሁለት የመጨረሻ ነገሮች ሁሌም በየ76 ዓመቱ ይገናኛሉ ማለት ነው።ስለዚህ ዓውደ ማእከላዊ ቀመር 76 ዓመት ነው ማለት ነው ።

፪.፭ ዓውደ አብይ ቀመር

በ532 ዓመት ሦስት ነገሮች ይገናኛሉ። እነርሱም፡-

- ዕለት
- አበቅቴና
- ወንጌላዊ ናቸው

ዕለቱ ሰኞ ምክንያቱም የቀመር ወይም የቁጥር መጨረሻ ሰኞ ነውና፤ ከማስከኞ ጀምረን ስንቆጥር የመጨሻው ሰኞ ነው፤አበቅቱው 18 ፤የአበቅቴ መጨረሻ 18 ነውና፣ወንጌላዊውም የወንጌላዊያን መጨረሻ ዮሐንስ ነው።በመሆኑም እነዚህ የመጨረሻ ሦስት ነገሮች በ532 ዓመት አንድ ጊዜ ስለሚገናኙ ዓውደ ዐብይ ቀመር 532 ዓመት ነው ማለት ነው ። ዓውደ ቀመርም ተብሎ ይጠራል።

በአጠቃላይ፣

- ✓ 1 ዐውደ ዕለት = 7 ዕለታት
- ✓ 1 ዐውደ ወርኀ = 30 ዕለታት
- ✓ 1 ዐውደ ዓመት = 365 ቀን ከ15 ኬክሮስ በፀሐይ፣ ወይም 354 ቀን ከ22 ኬክሮስ መጨረቃ
- ✓ 1 ዐውደ አበቅቴ = 19 ዓመት
- ➢ 1 ዐውደ ፀሐይ = 28 ዓመት
- ➢ 1 ዐውደ ፀሐይ = 1 ዐውደ አበቅቴ ከ9 ዓመት
- ➢ 28 ዓመት = 1 ዐውደ አበቅቴ ከ9 ዓመት
- ❖ 1 ዐውደ ማኅተም = 76 ዓመት
- ❖ 76 ዓመት = 2 ዐውደ ፀሐይ ከ20 ዓመት
- ❖ 2 ዐውደ ፀሐይ ከ20 ዓመት = 4 ዐውደ አበቅቴ
- ✓ 1 ዐውደ ማኅተም = 4 ዐውደ አበቅቴ
- ✓ 1 ዐውደ ቀመር = 532 ዓመት
- ✓ 532 ዓመት = 7 ዐውደ ማኅተም
- ➢ 7 ዐውደ ማኅተም = 19 ዐውደ ፀሐይ
- ➢ 19 ዐውደ ፀሐይ = 28 ዐውደ አበቅቴ
- ➢ 1 ዐውደ ቀመር = 7 ዐውደ ማኅተም
- ❖ 1 ዐውደ ቀመር = 19 ዐውደ ፀሐይ
- ❖ 1 ዐውደ ቀመር = 28 ዐውደ አበቅቴ



1).....ማለት ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ያሉት የሰባት ዕለታት ዑደት ነው።

2).....በ76 ዓመት ዞሮ የሚመጣ ነው።

3. በዐውደ ቀመር (በ532 ዓመት) አንድ ጊዜ ዕለት ፣አበቅቴና ወንጌላዊ ይገናኛሉ።
ዕለቱ.....፣አበቅቴው.....፣ወንጌላዊው.....ነው።

4).....በፀሐይ በ365 ዕለት ከ15 ኬክሮስ እንዲሁም በጨረቃ ነ354 ዕለት ከ22 ኬክሮስ የሞመላለስ የዓመተ ዓለም መስፈሪያ ነው።

5).....በፀሐይ ሠላሳ ዕለታትን ፣ በጨረቃ ደግሞ አንዴ 29 አንዴ ሠላሳ ሆኖ የሚመላለስ ነው፡፡

6) አበቅቴና መጥቅዕ ዜሮ የሚሆኑት በየትኛው ዓውድ ነው? በዚህ ጊዜ በተፈጠሩበት መስኮት ግንኙነት የሚያደርጉት አካላት ማንና ማን ናቸው?

7).ረቡዕና ማቴዎስ የሚገናኙበት ዓውድ ማን ነው?

8).በ76 ዓመት አንድ ጊዜ አበቅቴና ወንጌላዊ ይገናኛሉ፡፡ አበቅቴው ስንት ነው ? ወንጌላዊውስ ማን ነው?

ቀ
ጣ
ይ



ምዕራፍ ሦስት(፫)



፫. ወንበር

ወንበር ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፤ተረፈ ንኡስ ቀመር ማለት ነው፡፡ይህ ተረፈ ንኡስ ቀመር ዋናው አገልግሎቱ አበቅቴንና መጥቅዕን ለማግኘት ነው ፡፡ በመሆኑም አበቅቴንና መጥቅዕን ለማግኘት ወንበርን በቅድሚያ ማግኘት ግድ ይላል፡፡ወንበርን ለማግኘት የተለያዩ ደረጃዎችን እንከተላለን እነርሱም፡-

1ኛ...

ደረጃ1. ቅድመ ልደተ ክርስቶስንና እና ድኅረ ልደተ ክርስቶስን ያለውን ዘመን ማወቅ፤

ደረጃ 2. ቅድመ ልደተ ክርስቶስንና እና ድኅረ ልደተ ክርስቶስን ያለውን ዓመት በሙሉ መደመር፤

ደረጃ 3. በደረጃ ሁለት የተገኘውን ውጤት በዐሥር ቤት፣በመቶ ቤትና በሺሕ ቤት የቁጥር መደብ መክፈል ፤

ደረጃ 4. የሽሕ ቤቱን ለዐቢይ ቀመር ማካፈል፤

ደረጃ 5. በደረጃ አራት የተገኘውን ቀሪ ከመቶ ቤቱ ጋር መደመር፤

ደረጃ 6. በደረጃ አምስት የተገኘውን ውጤት ለማእከላዊ ቀመር ማካፈል፤

ደረጃ 7. ለማእከላዊ ተካፍሎ የተገኘውን ትርፍ ከዐሥር ቤቱ ጋር መደመር(የአሥር ቤትና የአንድ ቤቱ አንድ ላይ ይነበባሉ)። የዐሥር ቤቱ ዜሮ ከሆነ የአንድ ቤቱ ብቻ ይያዛል፤ሁለቱም ከዜሮ የተለዩ ከሆኑ ባንድ ላይ ይነበባሉ።

ደረጃ 8. በደረጃ ሰባት የተገኘውን ውጤት ለንኡስ ቀመር ማካፈል፤

ደረጃ 9. ለንኡስ ቀመር ተካፍሎ የተገኘው ቀሪ ላይ አንድን በመቀነስ ወንበርን ማግኘት ይቻላል።

2ኛ...ዓ.ዓምን በቀጥታ ለንዑስ ቀመር በማካፈል ቀሪውን ቀንሰን ወንበርን ማግኘት እንችላለን።

3ኛ.... ዓመተ ዓለምን በቀጥታ ለማዕከላዊ ቀመር በማካፈል ያገኘነውን ቀሪ ለንዑስ ቀመር በማካፈል የዓመቱን ተረፈ ዘመን እናገኛለን ። ስለዚህ ተረፈ ዘመን ሲቀነስ አንድ በማድረግ ወንበሩን ማግኘት ይቻላል።

ምሳሌ

የ2008ን ወንበር ፈልጉ፡-

1) ቅድመ ልደተ ክርስቶስ....5500 እና ድኅረ ልደተ ክርስቶስ...2008፤
2) ቅልክ(ቅድመ)+ድልክ(ድኅረ)....5500 ሲደመር 2008.....7508፤
3) የዐሥር ቤት...8፣የመቶ ቤት 500፣የሽሕ ቤት 7000፤
4) የሽሕ ቤት 7000 ሲካፈል ለዐቢይ ቀመር 532.....13 ቀሪ 84፤
5) የደረጃ 4 ቀሪ(84) ሲደመር ከመቶ ቤቱ(500).....584
6) 584 ሲካፈል ለማእከላዊ ቀመር(76).....7 ቀሪ 52
7) 52 ሲደመር ከአስር ቤቱ(8).....60
8) 60 ሲካፈል ለንኡስ ቀመር(19)...3 ቀሪ 3 ⟹ ተረፈ ዘመን ትባላለች።
9) ስለዚህ ወንበር= ተረፈ ዘመን-1.....2
   ወንበር 2008.....2 ነው ማለት ነው።

ይ.ይ.ፈተና ሦስት

1ኛ. ወንበር ማለት ምን ማለት ነው፤ ለምንስ ይጠቅመናል?
2ኛ. ወንበርን ለማግኘት የምንጠቀማቸውን ደረጃዎች አሳዩ?



ምዕራፍአራት(፬)

፬. አበቅቴ

አበቅቴ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ"ትርፍ ዘመን"፣የሌሊት ቁጥር ወይም የሌሊት ስፍር ማለት ነው። ማለትም በፀሐይና በጨረቃ መካከል ያለውን ልዩነት መሰረት ያደረገ ነው። ይህም ሲባል አንድ ዓመት በፀሐይ 365 ከ15 ኬክሮስ ሲሆን በጨረቃ ደግሞ 354 ቀን ከ22 ኬክሮስ ነው ። ስለዚህ በዚህ መሰረት በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ማወቅ እንችላለን። ስለዚህ 365 ሲቀነስ 354....11 ቀን እናገኛለን ይህችን 11 ቀን ተረፈ ዘመን ትባላለች። ይህ ተረፈ ዘመን ደግሞ ጥንተ አበቅቴ ይባላል።

ጥንተ አበቅቴ የተባለበት ምክንያት ምንድር ነው ቢሉ፡-ፀሐይና ጨረቃ በተፈጠሩበት ዕለት የዓመቱን ጉዞ እኩል ጀመሩ።የዓመት ጉዟቸውን ሲጠጥሉ ጨረቃ ልክ 354 ቀን እንደተጓዘች ዓመቷን ስትጨርስ፣ፀሐይ 365 ቀን ተጉዛ ዓመቷን ጨርሳለች። በሌላ አባባል ፀሐይ ጉዞዋን የጨረሰችው ከጨቀራ 11ቀን ዘግይታ ነው ማለት ነው። ስለዚህ ይህ በፀሐይና በጨረቃ ዓመት ያለው የ11 ቀን ልዩነት ጥንተ አበቅቴ ይባላል። ስለዚህ ዓለም በተፈጠረችበት በመጀመሪያው አመት አበቅቴው 11 ነበር ማለት ነው።

1ኛ. **አበቅቴ= ወንበር X ጥንተ አበቅቴ**

ጥንተ አበቅቴ ሁሌም 11 ነው።

ለምሳሌ የ2008ን አበቅቴ ፈልጉ፡-

ወንበር= ዓ.ዓ ሲካፈል ለንዑስ ቀመር....7508 ሲካፈል ለ19...395 ቀሪ 3 **ተረፈ ዘመን**

ወንበር=ተረፈ ዘመን - 1 = 2....ወንበር አፍ 2008 ስለዚህ አበቅቴውን ስንፈልግ፡-

አበቅቴ= ወንበር X ጥንተ አበቅቴ= 2X11= 22

ስለዚህ የ2008 አበቅቴ 22 ነው ማለት ነው።

2ኛ..

አበቅቴ = ያለፈው ዘመን አበቅቴ + ጥንተ አበቅቴ

ምሳሌ

የ2008ን አበቅቴ ስንፈልግ፡-

አበቅቴ = **ያለፈው ዘመን አበቅቴ + ጥንተ አበቅቴ**

አበቅቴ = የ2007 አበቅቴ + 11

=የ2007 አበቅቴ..11 ነው

= ስለዚህ 11+11= 22 ...የ2008 አበቅቴ 22 ነው ማለት ነው። ነገር ግን የምናገኘው ከሰላሳ ከበለጠ ለሠላሳ ማካፈላችንን እንዳንረሳ።

፬.፭. <u>ሕፀፅ</u>

ሕፀፅ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ በፀሐይና በጨረቃ ዙሪያ የሚገኝ ልዩነት ማት ነው። ይህም ማለት ፀሐይ በወር 30 ቀን ትዞራለች፤ጨረቃ ግን አንድ ወር 30 አንድ ወር29 ቀን ተዞራለች ስለዚህ የዚህ ልዩነት ማለት ነው።ስለዚህ ሕፀፅ በፀሐይና በጨረቃ መካከል የተከሰተው የሃያ ዘጠኝና የሰላሳ ልዩነት ነው። ሕፀፅ ማለት ይህ ነው ።ይህ ሕፀፅ በእያንዳንዱ ወር ይገኛል ፤ ከመጀመሪያው ወር መስከረም ጀምሮ ያሉት ሁለት ሁለት ተከታታይ ወራት ተመሳሳይ ሕፀፅ አላቸው።

$$\text{ሕፀፅ} = \frac{\text{ሁለተኛው የወራት ቁጥር(ሙሉው የወራት ቁጥር)}}{\text{ለሁለት}}$$

ስለዚህ፡-

ሕፀፅ አውርን = ሙሉው የወራት ቁጥር ሲካፈል ለ2

ለምሳሌ፡- የመስከረምና የጥቅምት ሕፀፅ = ሙሉው የወራት ቁጥር ÷ ለሁለት

= 2 ÷ 2 = 1

ስለዚህ የመስከረምና የጥቅምት ሕፀፅ አንድ(1) ነው ማለት ነው።

በአጠቃላይ፡-

- የመስከረምና የጥቅምት ሕፀፅ = 1(፩)
- የኅዳርና የታኅሣሥ ሕፀፅ = 2(፪)
- የጥርና የየካቲት ሕፀፅ = 3(፫)
- የመጋቢትና የሚያዚያ ሕፀፅ = 4(፬)
- የግንቦትና የሠኔ ሕፀፅ = 5(፭)
- የሐምሌና የነሐሴ ሕፀፅ =6(፮) ነው ማለት ነው።

የጳጉሜን ወር አምስት ወይም ስድስት ቀን ስለሆነ ሕፀፁ ከሐምሌና ከነሐሴ ጋር ተመሳሳይ ነው።

፬.፪. የሌሊት አወጣጥ

ቀን ውሎ ሌሊት እንደሚተካ ነገሩ ግልጥ ነው። ሌሊትም ቆይታውን ከጨረሰ በኋላ ወረፋውን ለቀን ያስረክባል ። የእነዚህ ቀንና ሌሊት ግን አቆጣጠራቸው የተለያ ነው ። ይህም ሲባል ቀን የሚቆጠረው በፀሐይ ዙሪት አማካኝነት ሲሆን ሌሊት የሚቆጠረው ግን በአበቅቴ፣በሕፀፅና በዕለት አማካኝነት ነው። ስለዚህ፡-

ሌሊት = አበቅቴ + ሕፀፅ + ዕለት

ዕለት ማለት በወሩ ቀኑ የሚውልበት ቁጥር ማለት ነው።ወይም የምንፈልገው ሌሊት ቀን ቁጥር ማለት ነው። ለምሳሌ የምንፈልገው 2002 መስከረም 5 ከሆነ ዕለቱ አምስት ነው ማለት ነው።

ምሳሌ፡- የ2005 ዓ፣ም መስከረም አምስት ቀን ሌሊቱ ስንት እንዳደረ ለማወቅ፡-

Given(የተሰጠ)

ወር...መስከረም

ዓመት....2005

ሕፀፅ.... የመስከረም

አበቅቴ....የ2005

ዕለት....መስከረም 5

ሌሊት....??? So,

ሌሊት = አበቅቴ + ሕፀፅ + ዕለት

የ2005 አበቅቴ = 18 የላይኛውን ቀመር መሰረት በማድረግ

የመስከረም ሕፀፅ = 1 ››››››››››››››››››››››››››››››

የመስከረም ዕለት = 5

ስለዚህ ፡-

ሌሊት = (፲፰)18 + (፩)1 + (፭)5

= (፳፬)24

ስለዚህ የመስከረም አምስት (፳፪፭)2005 ዓ፣ም ያደረው ሌሊት (፳፬)24 ነው ማለት ነው።

፬.፫. ሠርቀ ወርኀ

ሠርቀ ወርኀ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ "የጨረቃ ውጣት፣የጨረቃ ልደት ወይም ጨረቃ የወጣችበት ዕለት" ማለት ነው። ይህም አንድ ካህን በአገልግሎት ጊዜ ጸሎቱን ለማሳረግ ያሠርቃል ። ለማሥረቅ ደግሞ ሠርቀ ዕለትን፣ሠርቀ ሌሊትንና ሠርቀ ወርኀንም ማወቅ ያስፈልጋል። ሠርቀ ወርኀ ወይም የጨረቃን ልደት ለማወቅ ፡-

ሠርቀ ወርኀ = ሌሊት + የጨረቃ ተውሳክ

የጨረቃ ተውሳክ ግን አራት ነው።

ሌሊት = አበቅቴ + ሕፀፅ + ዕለት

ሠርቀ ወርን = አበቅቴ + ሕፀፅ + ዕለት + የጨረቃ ተውሳክ

....ስለዚህ ይህንን ቀመር በመጥቀም ሠርቀ ወርኀን ማወቅ ይቻላል ማለት ነው ::



1ኛ. አበቅቴ ማለት ምን ማለት ነው፣ አበቅቴን ማወቃችን ለምን ይጠቅመናል?

2ኛ. የ1988 ወንበሩን ፣አበቅቴውን በቀመሩ መሰረት አሳዩ?

3ኛ. የ1988 ዓ.ም የካቲት 22 ቀን ሌሊቱን አስሉ?

4ኛ. የሕፀፅን ቀመር በመጠቀም የዓመቱን ሕፀፅ አውጡ?

5ኛ. ዕለት ማለት ምን ማለት ነው?

6ኛ. ሠርቀ ወርኀ እንዴት ይገኛል?



ምዕራፍ አምስት(፭)

፭. መጥቅዕ

መጥቅዕ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፣ ቢሉ፤የአይሁድ አዲስ አመት መባቻ ፣ነጋሪት፣ደወል ማለት ነው ። ነጋሪት ሲመታ ወይም ሲደወል አንድም መልእክት ያስተላልፋል፤አንድም ሕዝብን ይሰበስባል። በዓላትና አጽዋማት በመጥቅዕ ስለሚሰበሰቡ ነው በማት ቅዱሳን አባቶቻችን በአባትነት አንደተበታቸው ይነግሩናል ያስተምሩናል ማለት ነው። አንድም መጥቅዕ ማለት የመጀመሪያው የፀሐይ ዓመታዊ ጉዞ አልቆ ሁለተኛውን ዐውደ አበቅቴ ለመሙላት የሚያስፈልግ የቀን መጠን መጥቅዕ ይባላል ። አንድም መጥቅዕ ከዕለታ ተውሳክ ጋር ተደምሮ መባጃ ሐመርን ያስገኛል።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉሙም መጥቅዕ ማለት ፦

፩. ደወል መቀስቀሻ ይባላል ፤ የተጀመረውም በኖህ ዘመን ነው (ዘፍ ምዕ 6 ቁ 20-21)

፪. የእስራኤላውያን የበዓል ስም ነው (ዘሌ ምዕ ፳፫ ቁ ፳፬-፳፭ ፤ ዘኁል ምዕ 29 ቁ 1-7)

፫. መለከት ማለት ነው (ዘኁል ምዕ 10 ቁ 1-10)

ስለዚህ፡-

መጥቅዕ = ወንበር X ጥንተ መጥቅዕ

….. ያገኘነው ውጤት ግን ከሠላሳ ከበለጠ ለሠላሳ በማካፈል ቀሪውን መጥቅዕ ብለን እንወስዳለን ማለት ነው።

ወይም፡-

መጥቅዕ = ያለፈው ዓመት መጥቅዕ + ጥንተ መጥቅዕ

ምሳሌ፡-

የ2008ን ዓ.ም መጥቅዕ ስንፈልግ፡-

1ኛ. መጥቅዕ = ወንበር X ጥንተ መጥቅዕ

ወንበር = ተረፈ ዘመን - 1

የ2008 ወንበር....2 ስለዚህ

መጥቅዕ = ወንበር X ጥንተ መጥቅዕ

= 2 X 19 = 38

ወጤቱ ከ30 የበለጠ ስለሆነ ለሠላሳ እናካፍለዋለን

38 ሲካፈል ለ30 = 1 ቀሪ 8

ስለዚህ የ2008 ዓ.ም መጥቅዕ 8 ነበር ማለት ነው።

2ኛ. መጥቅዕ = ያለፈው ዓመት መጥቅዕ + ጥንተ መጥቅዕ

= የ2007 ዐ.ም መጥቅዕ + 19

የ2007 ዓ፣ም መጥቅዕ ...19 ነው ስለዚህ

መጥቅዕ = 19 +19 =38

መጥቅዕ = 38 ሲካፈል ለ30 = 1ቀሪ 8 ስለዚህ

የ2008 መጥቅዕ 8 ነበር ማለት ነው።

- **ያገኘነው የመጥቅዕና የአበቅቴ ውጤት ድምሩ ሠላሳ መሆን አለበት ከበለተና ካነሰ ግን ስራችን ትክክል አይደለም ማለት ነው።**
- **የ2008 ዓ፣ም መጥቅዕ = 8**
- **የ2008 ዓ፣ም አበቅቴ = 22**
- **ስለዚህ 8 + 22 = 30 ይመጣል ስለዚህ ስራችን ትክክል ነው ማለት ነው።**

፭.፩. የዕለታት ተውሳክ

ተውሳክ ማለት ጭማሪ ፣ ተጨማሪ ማለት ሲሆን ለበዓትና ለአጽዋማት ማውጫ ያገለግላል። ተውሳክ /ተጨማሪ/ የሚወከለው በቁጥር ነው። ስለዚህ የዕለታት ተውሳክ ማለት ከሰኞ እስከ እሑድ ያለ ለበዓትና ለአጽዋማት ማውጫ የሚያገለግል ቁጥር ማለት ነው። በሌላ አባባል ተውሳክ ማለት መለያ ቁጥር ፣ ኮድ ፣ ታርጋ ቁጥር እንደማለት ነው። በመሆኑም እያንዳንዱ ዕለት የራሱ የሆነ ተውሳክ አለው ማለት ነው። ይኸውም ከመጥቅዕ እስከ ያመ ነነዌ ያለው የቀን ብዛት በማሰብ ነው።

ስንቀምረውም፡-

፮.፭.፩. የቅዳሜ ተውሳክ

በዓለ መጥቅዕ ቅዳሜ ቢውል ከቅዳሜ ማግስት እስከ ጾመ ነነዌ ያሉት ቀናት ፻፳፰/128/ ናቸው።

= ፻፳፰/128/ ሲካፈል ለ30 = 4 ቀሪ 8 ስለዚህ

የቅዳሜ ተውሳክ 8 ይሆናል ማለት ነው።

፮.፭.፪. የእሑድ ተውሳክ

በዓለ መጥቅዕ እሑድ ቢውል ከእሑድ ማግስት እስከ ጾመ ነነዌ ያሉት ቀናት ፻፳፯/127/ናቸው።

= ፻፳፯/127/ ሲካፈል ለ30 = 4ቀሪ 7 ስለዚህ የእሑድ ተውሳክ ይሆናል ማለት ነው።

፮.፭.፫. የሰኞ ተውሳክ

በዓለ መጥቅዕ ሰኞ ቢውል ከሰኞ ማግስት እስከ ጾመ ነነዌ ያሉት ቀናት ፻፳፮/126/ ናቸው።

= 126 ሲካፈል ለ30 = 4 ቀሪ 6 ስለዚህ

የሰኞ ተውሳክ 6 ነው ማለት ነው።

፮.፭.፬. የማክሰኞ ተውሳክ

በዓለ መጥቅዕ ማክሰኞ ቢውል ከማክሰኞ ማግስት እስከ ጾመ ነነዌ ያሉት ቀናት ፻፳፭/125/ ናቸው።

= ፻፳፭/125 ሲካፈል ለ30 = 4 ቀሪ 5 ስለዚህ

የማክሰኞ ተውሳክ 6 ነው ማለት ነው፡

፮.፭.፭. የረቡዕ ተውሳክ

በዓለ መጥቅዕ ረቡዕ ቢውል ከረቡዕ ማግስት እስከ ጾመ ነነዌ ያሉት ቀናት ፻፳፬/124/ ናቸው።

= ፻፳፬/124/ ሲካፈል ለ30 = 4 ቀሪ 4 ስለዚህ

የረቢዕ ተውሳክ 4 ነው ማለት ነው።

፮.፭.፮. የሐሙስ ተውሳክ

በዓለ መጥቅዕ ሐሙስ ቢውል ከሐሙስ ማግስት እስከ ጾመ ነነዌ ያሉት ቀናት ፻፳፫/123/ ናቸው።

= ፻፳፫/123/ ሲካፈል ለ30 = 4 ቀሪ 3 ስለዚህ

የሐሙስ ተውሳክ 3 ነው ማለት ነው።

፭.፩.፯. ዓርብ ተውሳክ

በዓለ መጥቅዕ ዓርብ ቢውል ከዓርብ ማግስት እስከ ጾመ ነነዌ ያሉት ቀናት ፻፳፪/122/ ናቸው።

= ፻፳፪/122/ ሲካፈል ለ30 = 4 ቀሪ 2 ስለዚህ

የዓርብ ተውሳክ 2 ነው ማለት ነው።

በአጠቃላይ፦

መነሻ ዕለተ መጥቅዕ	እርዝማኔ እስከ ነነዌ	በ፴ ሲገደፍ	የተውሳክ ዕለት
ቅዳሜ	፻፸፭ =	፴ + ፴ + ፴ +፴ + ፭	፭
እሑድ	፻፸፮ =	፴ + ፴ + ፴ + ፴ + ፮	፮
ሰኞ	፻፸፯ =	፴ + ፴ + ፴ + ፴ + ፯	፯
ማክሰኞ	፻፸፰ =	፴ + ፴ + ፴ + ፴ + ፰	፰
ረቡዕ	፻፸፱ =	፴ + ፴ + ፴ + ፴ + ፱	፱
ኃሙስ	፻፹ =	፴ + ፴ + ፴ + ፴ + ፲	፲
ዓርብ	፻፹፩ =	፴ + ፴ + ፴ + ፴ + ፩	፩

፭.፪. ፈተና አምስት

1ኛ. ተውሳክ ማለት ምን ማለት ነው ?

2ኛ. መጥቅዕ ማለት ምን ማለት ነው?

3ኛ. የዕለታትን ተውሳክ አሳዩ?

4ኛ. የእለታትን ተውሳክ ማወቃችን ለምን ይጠቅመናል?

ቀጣይ

ምዕራፍ ስድስት(፮)

፮.መባጃ ሐመር

መባጃ ሐመር ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፣መባጃ ሐመር “መባጊያ” ሐመር በመባል ይጠራል።ይህም ማለት የበጋ መመላለሻ የሚል ትርጉምን ይሰጣል። በሌላ በኩል መባጃ በራሱ ማቆያ፣ማክረሚያ ተብሎ ይተረጎማል።መባጃ ሐመር የመጥቅዕና የዕለታት ተውሳክ ድምር ሆኖ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበትን ያመለክታል።በሐመር የተመሰለውም አጽዋማትና በዓላት ወደላይና ወደ ታች የሚመላለስበት ሥርዓት ስለሆነ ነው። በአጠቃላይ መባጃ ሐመር ማለት የአጽዋማትና የበዓላት ማስገኛ ልዩ ቁጥር ነው።

መባጃ ሐመር ማለት የአጽዋማትና የበዓላት ማስገኛ ልዩ ቁጥር ነው ካልን እንዴት እንደሚገኝ ማወቅ ያስፈልጋል፡-

መባጃ ሐመር = መጥቅዕ + በዓለ መጥቅዕ የዋለበት ዕለት ተውሳክ

መጥቅዕ እንዴት እንደሚገኝ ከዚህ ቀደም ብለን በደንብ አይተናል። አሁን ደግሞ በዓለ መጥቅዕ እንዴት እንደሚገኝ እንመለከታለን፡-

“መጥቅዕ ሲበዛ ከመስከረም ንዛ፤መጥቅዕ ሲያንስ ጥቅምትን ዳስ” እንዳሉ ቅዱሳን አባቶቻችን...መጥቅዕ በዛ የሚባለው ከዐሥራ አራት በላይ ሲሆን ፤ አነሰ የሚባለው ደግሞ ከዐሥራ አራት በታች ሲሆን ነው።በዚህም መሰረት መጥቅዕ ከአሥራ አራት በላይ ከሆነ በዓለ መጥቅዕ በመስከረም ይውላል ፤ መጥቅዕ ከዐሥራ አራት በታች ከሆነ ደግሞ በዓለ መጥቅዕ በጥቅምት ይውላል ማለት ነው።ለዚህ ነው ቅዱሳን አበው **“መጥቅዕ ሲበዛ ከመስከረም ንዛ፤መጥቅዕ ሲያንስ ጥቅምትን ዳስ”** በማለት በዚያ እንደ ማር በሚጣፍጥ አንደበታቸው የተናገሩት።

ምሳሌ፦ የ፳፻(2000ን) መባጃ ሐመር እንፈልጋለን፦

መባጃ ሐመር = መጥቅዕ + በዓለ መጥቅዕ የዋለበት ዕለት ተውሳክ

መጥቅዕ = ፯(7)

ስለዚህ በዓለ መጥቅዕን ለማግኘት መጥቅዓችን ከዐሥራ አራት በታች ስለሆነ ጥቅምት ላይ ይውላል። ስለዚህ ጥቅምት ሰባት ሀሙስ በዓለ መጥቅዕ ሲሆን ፤ ይህ መዓለ መጥቅዕ የዋለበት ዕለት ተውሳኩ ሦስት ነው ማለት ነው።ምክንያቱም ተውሳክ እንዴት እንደሚገኝ ከዚህ ቀደም አይተናል።

ስለዚህ፦

መባጃ ሐመር = መጥቅዕ + በዓለ መጥቅዕ የዋለበት ዕለት ተውሳክ

መጥቅዕ = ፯(7)

በዓለ መጥቅዕ የዋለበት ዕለት = ሐሙስ

የሐሙስ ዕለት ተውሳክ = ፫(3)

መባጃ ሐመር = ፯(7)+ ፫(3)

= ፲ (10)

ስለዚህ የ፳፻ (2000) ዓ.ም መባጃ ሐመር 10(፲) ስለሆነ መዚህ መሰረት የ፳፻ (2000)ን በዓላትና አጽዋማት ማውጣት ይቻላል።

ነገር ግን፦ መጥቅዕ አልቦ (0) እና ፩(1) ከሆነ መስከረም ፴(30) የዋለበት ቀን ተውሳክ መባጃ ሐመር ይሆናል ማለት ነው።

የዚህ መባጃ ሀመር ዋና አገልግሎቱ ከአጽዋማት ተውሳክ ጋር እየተደመረ በዓላትንና አጽዋማትን ማስገኘት ነው። ስለዚህ የእያንዳንዱን አጽዋማት ተውሳክ ማውቅ ይጠበቅብናል ማለት ነው።

፮.፩. የአጽዋማት ተውሳክ

፮.፩.፩.የጾመ ነነዌ ተውሳክ

ጾመ ነነዌ የሆነ ተውሳክ የለውም የሚወጣውም ያለ ተውሳክ በመባጃ ሐመር ብቻ ነው።

- በዓለ መጥቅዕ በመስከረም በሚውልበት ጊዜ ጾመ ነነዌ በጥር ይውላል።
- በዓለ መጥቅዕ በጥቅምት በሚውልበት ጊዜ ጾመ ነነዌ በየካቲት ይውላል።
- መጥቅዕ ከ14 በላይ ሆኖ ከዕለት ተውሳክ ጋር ሰንደምረው ከ30 ከበለጠ ጾመ ነነዌ በየካቲት ይውላል።
- መጥቅዕ ዜሮ በሚሆንበት ጊዜ ጾመ ነነዌ በየካቲት ይውላል።

ምሳሌ፡- ከላይ የተመለከትነውን የ2000 ዓ.ምን ጾመ ነነዌን ስናውጣ ፡-

መጥቅዕ 7 ሲሆን መዓለ መጥቅዕ ጥቅምት ሐሙስ ነው ብለናል። መባጃ ሐመሩ ደግሞ 10 ነው ብለናል፤ስለዚህ በዓለ መጥቅዕ በጥቅምት በሚሆንበት ጊዜ ጾመ ነነዌ በየካቲት ይውላል ብለናል። በለጨማሪም ጾመ ነነዌ ተውሳክ ስለሌላት በመባጃ ሐመር ብቻ ነው የምትወጣ ብለናል። ስለዚህ መባጃ ሐመሩ 10 ስለሆነ የካቲት 10 ጾመ ነነዌ ገብታ ነበር ማለት ነው።

፮.፩.፪.የዐቢይ ጾም ተውሳክ

የጾመ ዐቢይን ተውሳክ ለማግኘት ከጾመ ነነዌ ማግስት ጀምሮ እስከ ዐቢይ ጾም ያሉትን ቀናት በመቁጠር ነው።እሊህም ቀናት 14 ናቸው። ስለዚህ የዐቢይ ጾም ተውሳክ 14 ነው ማለት ነው።

ስለዚህ፡-

የዐቢይ ጾም መግቢያ = መባጃ ሐመር + የዐቢይ ጾም

፮.፩.፫.የደብረ ዘይት ተውሳክ

የደብረ ዘይትን ተውሳክ ለማግኘት ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ደብረ ዘይት ያሉትን ቀናት ስንቆጥር 41 ቀናትን እናገኛለን። ስለዚህ ይህንን ለ30 ስናካፍለው ቀሪ አንድ እናገኛለን። ሰለዚህ የደብረ ዘይት ተውሳክ 1 ነው ማለት ነው።

የደብረ ዘይት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የደብረ ዘይት ተውሳክ

፮.፩.፬.የሆሣዕና ተውሳክ

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ሆሣዕና ያሉት ቀናት 62 ናቸው። ስለዚህ ለ30 ስናካፍለው ቀሪ 2 እናገኛለን።እናም የሆሣዕና ተውሳክ 2 ነው ማለት ነው።

የሆሣዕና መግቢያ = መባጃ ሐመር + የሆሣዕና ተውሳክ

፮.፩.፭.የስቅለት ተውሳክ

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ስቅለት ያሉት ቀናት ሥልሳ ሰባት ናቸው።ለሠላሳ ስናካፍለው ቀሪ 7ን እናገኛለን። ስለዚህ የስቅለት ተውሳክ ሰባት ነው ማለት ነው።

የስቅለት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የስቅለት

፮.፩.፮.የትንሣኤ ተውሳክ

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ትንሣኤ ያሉት ቀናት ሥልሳ ዘጠኝ ናቸው። ለሠላሳ ስናካፍለው ቀሪ 9ን እናገኛለን። ሰለዚህ የትንሣኤ ተውሳክ 9 ነው ማለት ነው።

የትንሣኤ መግቢያ = መባጃ ሐመር + የትንሣኤ

፮.፩.፯.የርክበ ካህናት ተውሳክ

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ርክበ ካህናት ያሉት ቀናት ዘጠና ሦስት ናቸው። ለሠላሳ ስናካፍለው ቀሪ 3 እናገኛለን። በመሆኑም የርክበ ካህናት ተውሳክ 3 ነው ማለት ነው።

የርክበ ካህናት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የርክበ ካህናት ተውሳክ

፮.፩.፰.የዕርገት ተውሳክ

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ዕርገት ያሉት ቀናት አንድ መቶ ስምንት(፻፰) ቀናት ናቸው። ስለዚህ ለሠላሳ ስናካፍለው ቀሪ ፲፰ ይሆናል። በመሆኑም የዕርገት ተውሳክ ፲፰ ነው ማለት

የዕርገት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የዕርገት ተውሳክ

፮.፩.፱.የጰራቅሊጦስ ተውሳክ

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ጰራቅሊጦስ ያሉት ቀናት አንድ መቶ አሥራ ስምንት(፻፲፰) ቀናት ናቸው። ስለዚህ ለሠላሳ ስናካፍለው ቀሪ ፹፰ እናገኛለን።ስለዚህ ፹፰ የጰራቅሊጦስ

የጰራቅሊጦስ መግቢያ = መባጃ ሐመር + የጰራቅሊጦስ ተውሳክ

፮.፩.፲.የጾመ ድኅነት ተውሳክ

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ጾመ ድኅነት ያሉት ቀናት አንድ መቶ ሀያ አንድ(፻፳፩) ቀናት ናቸው። ስለዚህ ለሠላሳ ስናካፍለው ቀሪ አንድ(፩)ይሆናል ማለት ነው። ሆኖም የጾመ ድኅነት ተውሳክ አንድ ነው ማለት ነው።

የጾመ ድኅነት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የጾመ ድኅነት ተውሳክ

፮.፩.፲፩. የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ

ከጾመ ነነዌ ማግስት እስከ ጾመ ሐዋርያት ያሉት ቀናት አንድ መቶ ሀያ ስድስት(፻፳፮) ቀናት ናቸው። ስለዚህ ለሠላሳ ስናካፍለው ቀሪ ስድስት(፮) ይሆናል በመሆኑም የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ ስድስት ነው ማለት ነው።

የጾመ ሐዋርያት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የጾመ ሐዋርያት

በአጠቃላይ የአጽዋማት ተውሳክ እንደሚከተለው ነው።

መነሻ	መድረሻ	የቀን ብዛት	ተውሳክ
ጾመ ነነዌ	ዓብይ ጾም	፲፬	፲፬
ጾመ ነነዌ	ደብረ ዘይት	፳፩ = ፴ + ፲፩	፲፩
ጾመ ነነዌ	ሆሣዕና	፷፪ = ፴ + ፴ + ፪	፪
ጾመ ነነዌ	ስቅለት	፷፭ = ፴ + ፴ + ፭	፭
ጾመ ነነዌ	ትንሣኤ	፷፱ = ፴ + ፴ + ፱	፱
ጾመ ነነዌ	ርክበ ካህናት	፻፲ = ፴ + ፴ + ፴ + ፲	፲
ጾመ ነነዌ	ዕርገት	፲፭ = ፴ + ፴ + ፴ + ፲፭	፲፭
ጾመ ነነዌ	ጰራቅሊጦስ	፲፭፲፭ = ፴ + ፴ + ፴ + ፭፭	፭፭
ጾመ ነነዌ	ጾመ ድኅነት	፲፭፭ = ፴ + ፴ + ፴ + ፴ + ፭	፭
ጾመ ነነዌ	ጾመ ሐዋርያት	፲፭፯ = ፴ + ፴ + ፴ + ፴ + ፯	፯

፯.፪. ፈተና ስድስት

1ኛ. መባጃ ሐመር ማለት ምን ማለት ነው?

2ኛ. የጾመ ነነዌን ተውሳክ አብራሩ?



ምዕራፍ ሰባት(፯)

፯. የአጽዋማት ገደብ(ኢየዐርግና ኢይወርድ)

አጽዋማት ምንም እንኳን በባሕረ ሐሳብ እየተሰሩ ቢወጡም መነሻቸውና መድረሻቸው ይታወቃል። ከመስከረም አንድ ጅምሮ እስከ ጳጉሜ አምስት አይወጡም፤ የእየራሳቸው መነሻና መድረሻ ክልል አላቸው ማለት ነው።

“እንዘ ይብል እከሥት በምሳሌ አፉየ ወእነግር አምሳለ ዘእምትካት” “አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ፤ ከጥንት የተነገረውንም ምሳሌ እናገራለሁ”(ማቴ 13፤35) እንዳለ ። ስለዚህ ነገር በምሳሌ ይነገራልና ምሳሌን እንመለከታለን።

ለምሳሌ፡-

ሃይማኖትና ምግባሩ የሚባሉ ሁለት ነጋዴዎች ነበሩ እንበል፤ሃይማኖት እየተንቀሳቀሰ የሚነግደው ከቀበሌ እስከ ዞን ነው፤ ነጋዴ ምግባሩ ደግሞ የሚነግደው ከዞን እስከ ክልል ነው። ስለዚህ የሃይማኖት ገደብ ከቀበሌ እስከ ዞን ሲሆን ኢይወርዱ ቀበሌ ኢየዐርጉ ደግሞ ዞን ነው ማለት ነው። ማለትም ከዞን አይወጣም ከቀበሌ አይወርድም ። የምግባሩ ገደብ ደግሞ ከዞን እስከ ክልል ነው ማለትም ከዞን አይወርድም ከክልል አይወጣም ማለት ነው።

እንደዚህም ሁሉ አጽዋማትም የእየራሳቸው ገደብ አላቸው።

- ✓ ዝቅተኛው ገደብ ....ኢይወርድ
- ✓ ከፍተኛው ገደብ.....ኢየዐርግ ይባላል ማለት ነው።

ስለዚህ በዚህ መሰረት የአጽዋማትን ኢየዐርግና ኢይወርድ እንመለከታለን ማለት ነው።

፯.፩ የጾመ ነነዌ ገደብ

ኢይወርድ

መጥቅዕ ከአስራ አራት በላይ ሲሆን በዐለ መጥቅዕ መስከረም ይውላል ብለናል፤ ከአስራ አራት በላይ ዝቅተኛው ቁጥር አስራ አምስት ነው፤ ስለዚህ በዓለ መጥቅዕ መስከረም አስራ አምስት

ቢውል ብለን እናስባለን፡፡ መስከረም 15 ከሰባቱ እለታት በአንዱ መዋሉ የማይቀር ነው፤ስለዚህ ከሰባቱ ዕለታት ዝቅተኛ ተውሳክ ያለውን እንወስዳለን እርሱም አርብ ነው ተውሳኩም ሁለት ነው፡፡ ጸመ ነነዌ በመባጃ ሐመር ብቻ ስለምትወጣ አበቅቴውንና ተውሳኩን ካወቅን መባጃ ሐመሩን እንፈልጋለን፡፡

መባጃ ሐመር = መጥቅዕ + በዓለ መጥቅዕ የዋለበት ዕለት ተውሰክ

ስለዚህ ከላይ እንዳየነው ፡- ዝቅተኛውን አበቅቴ 15ን ይዘናል

በዓለ መጥቅዕ ዝቅተኛ ተውሳክ ካለበት ዓርብ ላይ ቢውል ብለን 2 ተውሳክ ይዘናል፡፡ ስለዚህ፡-

መባጃ ሐመር = 15 + 2

= 17

መስከረም ላይ በዓለ መጥቅዕ ቢውል ነነዌ በጥር እንደምትውልና በመባጃ ሐመር ብቻ እንደምትወጣ ተመልክተናል፡፡ በሰራነው መሰሠረት መባጃ ሐመሩ 17 ነው፡፡ ማለትም ዝቅተኛው አበቅቴ ሲደገፍ ዝቅተኛው ተውሳክ መባጃ ሐመሩና ነነዌ ተገንተዋል፤ ስለዚህ ጥር 17 ለጸመ ነነዌ መግቢያ ዝቅተኛው ገደብ ኢይወርድ ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ጸመ ነነዌ በየትኛውም ዓመት ፈጥና ገባች ቢባል በጥር 17 ቀን ትገባለች እንጅ ከጥር አስራ ሰባት ቀድማ አትገባም፡፡

ስለዚህ የጸመ ነነዌ ኢይወርድ ጥር አሰራ ሰባት ነው ማለት ነው፡፡

ኢየዐርግ

መጥቅዕ ከዐሥራ አራት በታች ሲሆን መዐለ መጠቅዕ በጥቅምት ይውላል ብለን አይተናል፡፡ ከዐሥራ አራት በታች ከፍተኛው አበቅቴ ዐሥራ ሦስት ነው፤ስለዚህ ጥቅምት 13 በዐለ መጥቅዕ ቢውል ብለን እናስባለን፡፡ ጥቅምት 13 ደግሞ ከሰባቱ ዕለታት በአንዱ መዋሉ የማይቀር ነው፤ስለዚህ ከሰባቱ ዕለታት ትልቅ ተውሳክ ያለውን እለት እንወስዳልን ዕለቱም ቅዳሜ ነው፤ተውሳኩም ስምንት ነው፡፡ ስለዚህ ከላይ እዳየነው መባጃ ሐመሩን እነፈልጋለን ምክንያቱም ነነዌ በመባጃ ሐመር ብቻ ነውና የምትወጣው፡፡

መባጃ ሐመር = መጥቅዕ + በዓለ መጥቅዕ የዋለበት ዕለት ተውሰክ

- ከአስራ ሦስት በታች ከፍተኛ መጥቅዕ 13ን ይዘናል፤
- ይህ 13 ከፍተኛ ተውሳክ ካለው ቀን ቢውል ብለን 8ን ይዘናል፡፡

ስለዚህ፡-

መባጃ ሐመር = 13 + 8

= 21

ጥቅምት ላይ በዐለ መጥቅዕ ሲውል የካቲት ላይ ጾመ ነነዌ ተገባለች ብለናል፤ሲቀጥል ነነዌ ተውሳክ ስለሌላት በመባጃ ሐመር ብቻ ትወጣለች ብለናል። ስለዚህ መባጃ ሐመሩን 21 አግኝተናል፤ በዐለ መጥቅዕ በየካቲት ስለሆነ የካቲት 21 ቀን ጾመ ነነዌ ትገባለች ማለት ነው። ስለዚህ ይህ የተገኘው በከፍተኛው አበቅቴና በከፍተኛው የዕለት ተውሳክ ነው፤እናም የካቲት ሃይ አንድ ለጾመ ነነዌ ከፍተኛ ገደብ ኢየዐርግ ነው ማለት ነው። ነገር ግን ከየካቲት ሃያ አንድ ውጭ የሚገባ ጾመ ነነዌ በዝቅተኛ አበቅቴና የዕለት ተውሳክ ይገኛል። ስለዚህ መቼም ቢሆን ጾመ ነነዌ የፈለገውን ወደ ላይ ብትወጣ ከየካቲት ሃያ አንድ አታልፍም ማለት ነው።

“ነነዌ እም፲፯ ለጥር ኢይወርድ ታሕተ ወእም፳፩ ለየካቲት ኢይዓርግ” ላዕለ እንዳለ መርሐ ዕውር ።



፯.፪ የዐቢይ ጾም ገደብ

ኢይወርድ

የጾመ ነነዌን ገደብ ካወቅን የቀሪዎችን አጽዋማት ገደብ ማወቅ ቀላል ነው። ስለዚህ የዐቢይ ጾምን ገደብ ለማወቅ መጀመሪያ ዐቢይ ጾምን ስናወጣ የተጠቀምንበትን ቀመር እንጠቀማለን።

ይህም፡-

የዐቢይ ጾም መግቢያ = መባጃ ሐመር + የዐቢይ ጾም ተውሳክ የሚል ነበር።

ስለዚህ ዝቅተኛውን ገደብ(ኢይወርድ) ለማወቅ የጾመ ነነዌን ዝቅተኛ ገደብ ስንፈልግ የተጠቀምንበትን 17 መባጃ ሐመር እንወስዳለን። የዐቢይ ጾም ተውሳክ ደግሞ 14 ነው። ስለዚህ እንዚህን በቀመሩ መሠረት አስገብተን መደመር ይሆናል ስራችን ማለት ነው።

የዐቢይ ጾም መግቢያ = መባጃ ሐመር + የዐቢይ ጾም ተውሳክ

የዐቢይ ጾም መግቢያ = 17 + 14

= 31

ስለዚህ ይህን ለሠላሳ ስናካፍለው ሠላሳ ደርሶ ቀሪ አንድ ይሆናል በባሕረ ሐሳብ ደግሞ ቀሪውን እንጠቀማለን ብለናል። እናም የጾመ ነነዌ ኢይወርድ ጥር 17 ነበር ስለዚህ የዐቢይ ፆም ለሠላሳ ስላካፈልነው ከጥር አንድ ወር እንጨምርና የካቲት ውስጥ እንገባለን ማለት ነው።

ስለዚህ የካቲት አንድ የዐቢይ ጾም ኢይወርድ(ዝቅተኛ ገደብ) ነው ማለት ነው።

ኢየዐርግ

የዐቢይ ጾምን ኢየዐርግ ለማኘት የምጠቀመው መባጃ ሐመር የጾመ ነነዌን ኢየዐርግ ለማውጣት የተጠቀምንበትን መባጃ ሐመር ነው። መባጃ ሐመሩም ሃያ አንድ ነው።

ስለዚህ፡-

የዐቢይ ጾም መግቢያ = መባጃ ሐመር + የዐቢይ ጾም ተውሳክ

የዐቢይ ጾም መግቢያ = 21 + 14

= 35 ይሆናል።

ስለዚህ ይህንን ለሠላሳ ስናካፍለው አምስት ይቀራል፤እንጠቀመዋለንም።

የጾመ ነነዌ ኢየዐርግ የካቲት ሃያ አንድ ነበር፤ የዐቢይ ጾምን ስንሠራ ለሠላሳ ስላካፈልነው ከየካቲት ወደ መጋቢት እንሄዳለን ማለት ነው። በመሆኑም መጋቢት አምስት የዐቢይ ጾም ኢየዐርግ ነው ማለት ነው።

በአጠቃላይ ዐቢይ ጾም ፈጥኖ ቢገባ የካቲት አንድ እንጅ ከየካቲት አንድ ቀድሞ አይገባም፤እንዲሁም በጣም ዘገየ ቢባልም መጋቢት አምስት ይገባል እንጂ ከመጋቢት አምስት በላይ አያልፍም ማለት ነው።



፯.፫ የደብረ-ዘይት ገደብ

ኢይወርድ

የደብረ ዘይትን ኢይወርድ ለማወቅ የጾመ ነነዌን ኢይወርድ ለመፈለግ የተጠቀምንበትን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን ማለት ነው። ማለትም፡-

- የጾመ ነነዌ ኢይወርድ መባጃ ሐመር ዐሥራ ሰባት ነው ብለናል።
- የደብረ ዘይት ተውሳክ ደግሞ ዐሥራ አንድ እንደሆነ አይተናል ስለዚህ

  የደብረ ዘይት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የደብረ ዘይት ተውሳክ

  = 17+ 11

  = 28 ይሆናል

  ስለዚህ፡- የዐቢይ ጾም ኢይወርድ የካቲት አንድ ነው ብለናል።የደብረ ዘይትንም ለሠላሳ ሳናካፍል 28ን አግኝተናል።ስለዚህ ወሩ በዚያው በየካቲት ይሆናል። እናም የደብረ ዘይት ኢይወርድ የካቲት 28 ነው ማለት ነው።

ኢየዐርግ

ኢየዐርጉንም ለመፈልግ በተመሳሳይ መልኩ የጾመ ነነዌን ኢየዐርግ ስንፈልግ የተጠቀምንውን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን ማለት ነው። እናም መባጃ ሐመሩ 21 ነው የደብረ ዘይት ተውሳክም ከላይ እንዳየነው 11 ነው ስለዚህ ሁለቱን በመገደፍ የደብረ ዘይትን ኢየዐርግ እናገኛለን ማለት ነው።

የደብረ ዘይት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የደብረ ዘይት ተውሳክ

= 21 + 11

= 32 ድምሩ ለሰላሳ ስለበለጠ ለሠላሳ እናካፍላለን ማለት ነው።

= 1 ቀሪ 2 ይሆናል

ስለዚህ የዐቢይ ጾም ኢየዐርግ መጋቢት አምስት ነው ብለን ነበር። የደብረ ዘይት ኢየዐርግ ግን ሚያዝያ 2 ነው ። ምክንያቱም 2ን ያገኘናት በሠላሳ አካፍለን ስለሆነ ከመጋቢት ወደ ሚያዝያ እንሸጋገራለን ማለት ነው።

በአጠቃላይ፡- ደብረ ዘይት ከየካቲት 28 አይወርድም ከሚያዝያ 2 አይወጣም ማለት ነው። ስለዚህ ከየካቲት 28-ሚያዝያ 2 ባሉት ሠላሳ አምስት ቀናት ውስጥ ይመላለሳል።



፯.፩ የሆሣዕና ገደብ

ኢይወርድ

የሆሣዕናን ኢይወርድ ለመስራት የጾመ ነነዌን ኢይወርድ ለማግኘት የተጠቀምነውን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን፤ እናም መባጃ ሐመሩ 17 ነው፤የሆሣዕና ተውሳክ ደግሞ 2 ነው ስለዚህ እነዚህን በመደገፍ ኢይወርዱን መስራት እንችላለን ማለት ነው።

የሆሣዕና መግቢያ = መባጃ ሐመር + የሆሣዕና ተውሳክ

= 17 + 2

= 19ን እናገኛለን፤

ሰለዚህ፡- የደብረ ዘይት ኢይወርድ የካቲት 28 ነው ብለን ነበር እናም የሆሣዕና ኢይወርድ መጋቢት 19 ቀን ይሆናል ማለት ነው። ለምን ቢሉ ከየካቲት 28 ቀን ቀጥሎ የምናገኘው 19 የመጋቢ እንጂ የየካቲት አይደልምና፤ ስለዚህ የሆሣዕና ኢይወርድ መጋቢት 19 ነው ማለት ነው።

ኢየዐርግ

የሆሣዕናን ኢየዐርግ ለማግኘት የጾመ ነነዌን ኢየዐርግ ስንፈልግ የተጠቀምነውን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን ማለት ነው፤እናም መባጃ ሐመሩም 21 ነው፤የሆሣዕና ተውሳክ ደግሞ 2 ነው ብለናል ስለዚህ ሁለቱን በመደገፍ የሆሣዕናን ኢየዐርግ ማወቅ እንችላለን፡፡

የሆሣዕና መግቢያ = መባጃ ሐመር + የሆሣዕና ተውሳክ

= 21 + 2

= 23ን እናገኛለን

ስለዚህ፡-የደብረ ዘይት ኢየዐርግ ሚያዚያ 2 ቀን ነው ብለን ነበር፡፡ እናም የሆሣዕናን ስንሰራ ለሠላሳ ስላላካፈልነው ከሚያዝያ ሁለት ቀጥሎ ያለው 23 ደግሞ የሚያዝያ ስለሆነ ኢየዐርጉ ሚያዝያ 23 ቀን ነው ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ፡- ሆሣዕና ከመጋቢት 19 አይወርድም ፤ ከሚያዝያ 23 አይወጣም ፤ ከመጋቢት 19-ሚያዝያ 28 ባሉት ሠላሳ አምስት ቀናቶች ይመላለሳል እንጅ፡፡



ኢይወርድ

የስቅለትን ኢይወርድ ለማግኘት የጾመ ነነዌን ኢይወርድ ለመስራት የተጠቀምንበትን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን ማለት ነው። መባጃ ሐመሩም 17 ነው፤የስቅለት ተውሳክ ደግሞ 7 ነው።

የስቅለት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የስቅለት ተውሳክ

= 17 + 7

= 24

ስለዚህ የሆሳዕና ኢይወርድ መጋቢት 19 ቀን ነው ብለን ነበር። ለሰላሳ ስላላካፈልነውና ከመጋቢት 19 ቀጥሎ ያለው መጋቢት 24 ነውና መጋቢት 24 የስቅለት ኢይወርድ ነው። ስለዚህ ስቅለት ከመጋቢት 24 ኢይወርድም ማለት ነው።

ኢየዐርግ

በተመሳሳይ መልኩ የስቅለትን ኢየዐርግ ለመፈለግ የጾመ ነነዌን ኢየዐርግ ለመፈልግ የተጠቀምነውን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን። መባጃ ሐመሩም 21 ነው፤የስቅለት ተውሳክም 7 ነው ስለዚህ፡-

የስቅለት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የስቅለት ተውሳክ

= 21 + 7

= 28

ስለዚህ የሆሳዕና ኢየዐርግ ሚያዝያ 23 ቀን ነው ብለን ነበር። እናም የስቅለትን ኢየዐርግ ያገኘነው ለሠላሳ ሳናካፍል ነው። ስለዚህ ከሚያዝያ 23 ቀጥሎ ያለው 28 ደግሞ የራሱ የሚያዝያ ነውና ሚያዝያ 28 ቀን የስቅለት ኢየዐርግ ነው ማለት ነው። ስለዚህ ስቅለት ቢበዛ ከሚያዝያ 28 አልፎ አይሔድም ማለት ነው።

በአጠቃላይ፡- ስቅለት ከመጋቢት 24 እስከ ሚያዝያ 28 ባሉት ሠላሳ አምስተ ቀናት ሊመላለስ ይኖራል ማለት ነው።



፯.፮ የትንሳኤ ገደብ

ኢይወርድ

የትንሳኤን ኢይወርድ ለመስራት የጸመ ነነዌን ኢይወርድ ስንፈልግ የተጠቀምንበትን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን፤ መባጃ ሐመሩም 17 ነው ፤ የትንሳኤ ተውሳክ ደግሞ 9 ነው። ስለዚህ ሁለቱን በመደገፍ የስቅለትን ኢይወርድ ማግኘት እንችላለን።

የትንሳኤ መግቢያ = መባጃ ሐመር + የስቅለት ተውሳክ

= 17 + 9

= 26 ይሆናል ማለት ነው።

ስለዚህ የስቅለት ኢይወርድ መጋቢት 24 ቀን ነው ብለን ነበር። እናም የትንሳኤን ስንፈልግ ለሠላሳ አላካፈልንም ከመጋቢት 24 ቀጥሎ ያለው 26 ደግሞ የእራሱ የመጋቢት ነው። ስለዚህ የትንሳኤ ኢይወርድ መጋቢት 26 ቀን ነው ማለት ነው።

ኢየዐርግ

የትንሳኤ ኢየዐርግ ለመስራት የጾመ ነነዌን ኢየዐርግ ስንፈልግ የተጠቀምንበትን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን ፤ መባጃ ሐመሩም 21 ነው፤ የትንሳኤ ተውሳክ ደግሞ 9 ነው ስለዚህ ሁለቱን በመደገፍ ኢየዐርጉን መስራት እንችላለን፡፡

የትንሳኤ መግቢያ = መባጃ ሐመር + ትንሳኤ ተውሳክ

= 21 + 9

= 30ን እናገኛለን፡፡

ስለዚህ የስቅለት ኢየዐርግ ሚያዝያ 28 ቀን ነው ብለን ነበር፡፡ የትንሳኤን ስንሰራ ለሠላሳ ስላላካፈልነው እራሱን ሚያዝያ 30 ቀንን እንወስዳለን ፡፡ ስለዚህ የትንሳኤ ኢየዐርግ ሚያዝያ 30 ቀን ነው ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ፡- ትንሳኤ ከመጋቢት 26 እስከ ሚያዝያ 30 ቀን ባሉት ሠላሳ አምስት ቀናት ሲመላለስ ይኖራል ማለት ነው፡፡



፯.፯ የርክበ ካህናት ገደብ

ኢይወርድ

የርክበ ካህናትን ኢይወርድ ለመስራት የጾመ ነነዌን ኢይወርድ ለመፈለግ የተጠቀምንበትን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን፤ መባጃ ሐመሩም 17 ነው፤ የርክበ ካህናት ተውሳክ ደግሞ 3 ነው ስለዚህ ሁለቱን በመደገፍ ኢይወርዱን መስራት እንችላለን ማለት ነው።

የርክበ ካህናት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የርክበ ካህናት ተውሳክ

= 17 + 3

= 20ን እናገኛለን።

ስለዚህ የትንሳኤ ኢይወርድ መጋቢት 26 ቀን ነው ብለን ነበር። ከመጋቢት 26 ቀን ቀጥሎ ያለው 20 ደግሞ የሚያዝያ እንጂ የመጋቢት ስላልሆነ የርክበ ካህናት ኢይወርድ ሚያዝያ 20 ቀን ነው ማለት ነው።

ኢየዐርግ

የርክበ ካህናት ለማግኘት የጾመ ነነዌን ኢየዐርግ ለንፈልግ የተጠቀምነውን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን ማለት ነው፤ መባጃ ሐመሩም 21 ነው፤የርክበ ካህናት ተውሳክ ደግሞ 3 ነው ብለን ነበር ስለዚህ ሁለቱን በመደገፍ የርክበ ካህናትን ኢየዐርግ ማግኘት እንችላለን።

የርክበ ካህናት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የርክበ ካህናት ተውሳክ

= 21 + 3

= 24

ስለዚህ የትንሳኤ ኢየዐርግ ሚያዝያ 30 ቀን ነው ብለን ነበር። ከሚያዝያ 30 ቀጥሎ ያለው 24 ደግሞ የግንቦት ነው፤ በመሆኑም ግንቦት 24 የርክበ ካህናት ኢየዐርግ ቀን ነው ማለት ነው።

በአጠቃለይ፡ -ርክበ ካህናት ከሚያዝያ 20 እስከ ግንቦት 24 ባሉት ሠላሳ አምስት ቀናት ሲመላለስ ይኖራል ማለት ነው።



ኢይወርድ

የዕርገትን ኢይወርድ ለመስራት በተመሳሳይ መልኩ የጾመ ነነዌን ኢይወርድ ስንሰራ የተጠቀምነውን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን፤መባጃ ሐመሩም 17 ነው፤እንዲሁም የዕርገት ተውሳክ ደግሞ 18 ነው፤ ስለዚህ ሁለቱን በመደገፍ የዕርገትን ኢይወርድ ማግኘት ይቻላል፡፡

የዕርገት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የዕርገት ተውሳክ

= 17 + 18

= 35

ሠላሳ አምስትን ለሠላሳ ስናካፍለው አንድ ቀሪ 5 ይሆናል በባሕረ ሐሳብ ደግሞ ቀሪውን እንወስዳለን ስለዚህ 5ን እንወስዳለን ማለት ነው፡፡

ስለዚህ የርክበ ካህናት ኢይወርድ ሚያዝያ 20 ቀን ነው ብለን ነበር፤የዕርገትን ስንሰራ ደግሞ ለሠላሳ ስላካፈልነው ከሚያዝያ ቀጥሎ ወዳለው ወር እንራመዳለን ፤ከሚያዝያ ቀጥሎ ያለው ወር ደግሞ ግንቦት ነው ስለዚህ የዕርገት ኢይወርድ ግንቦት 5 ነው ማለት ነው፡፡

ኢየዐርግ

የዕርገትን ኢየዐርግ ለመስራት የጾመ ነነዌን ኢየዐርግ ስንፈልግ የተጠቀምንበትን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን ስለዚህ መባጃ ሐመሩም 21 ነው፤ የዕርገት ተውሳክ ደግሞ 18 ነው ብለን ነበር፤ ስለዚህ ሁለቱን በመደገፍ የዕርገትን ኢየዐርግ መስራት ይቻላል።

የዕርገት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የዕርገት ተውሳክ

= 21 + 18

= 39

ስለዚህ ሠላሳ ዘጠኝን ለሠላሳ ስናካፍል ቀሪ 9ን እናገኛለን በባሕረ ሀሳብ ስልት ደግሞ የሚያገለግለው ድርሻ ሳይሆን ቀሪ ነውና ቀሪውን እንወስዳለን ማለት ነው።

ስለዚህ የርክበ ካህናት ኢየዐርግ ግንቦት 24 ቀን ነው ብለን ነበር፤እናም የዕርገትን ኢየዐርግ ስንሰራ ለሠላሳ ስላካፈልነው የርክበ ካህናት ኢየዐርግ ከዋለበት ወር አንድ ወር ወደፊት እንሔድናሠኔ ላይ እናርፋለን።በመሆኑም ሠኔ ዘጠኝ ቀን የዕርገት ኢየዐርግ ነው ማለት ነው።

በአጠቃላይ፡- በዓለ ዕርገት ከግንቦት 5 እስከ ሠኔ 9 ባሉት ሠላሳ አምስት ቀናት ውስጥ ሲመላለስ ይኖራል ማለት ነው።



፯.፱ የጸራቅሊጦስ ገደብ

[redacted]

ኢይወርድ

የጸራቅሊጦስን የኢይወርድ ገደብ ለመስራት የጾመ ነነዌን ኢይወርድ ስንሰራ የተጠቀምነውን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን ማለት ነው፤ መባጃ ሐመሩም 17 ነው፤ እንዲሁም የጸራቅሊጦስ ተውሳክ ደግሞ 28 ነው። ስለዚህ እሊህ ሁለቱን በመደገፍ የጸራቅሊጦስን ኢይወርድ ማግኘት እንችላለን።

የጸራቅሊጦስ መግቢያ = መባጃ ሐመር + የጸራቅሊጦስ ተውሳክ

= 17 + 28

= 45ን እናገኛለን ነገር ግን 45 ከሠላሳ በላይ ስለሆነ ለሠላሳ እናካፍለዋለን ማለት ነው። ስናካፍለውም ቀሪ 15ን እናገኛለን ማለት ነው።

ስለዚህ የዕርገት ኢይወርድ ግንቦት 5 ቀን ነው ብለን ነበር፤እናም ከግንቦት 5 ቀጥሎ የምናገነው 15 የእራሱ ግንቦት ስለሆነ ግንቦት 15 ቀን የጸራቅሊጦስ ኢይወርድ ነው ማለት ነው።

ኢየዐርግ

የጸራቅሊጦስን ኢየዐርግ ለመስራት የጾመ ነነዌን ኢየርግ ስንሰራ የተጠቀምነውን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን ማለት ነው፤መባጃ ሐመሩም 21 ነው ብለን ነበር፤እንዲሁም የጸራቅሊጦስ ተውሳክ ደግሞ 28 ነው። ስለዚህ እሊህ ሁለቱን በመደገፍ የጸራቅሊጦስን ኢየዐርግ ማግኘት እንችላለን።

የጸራቅሊጦስ መግቢያ = መባጃ ሐመር + የጸራቅሊጦስ ተውሳክ

= 21 + 28

= 49ን እናገኛለን ነገር ግን 49 ከሠላሳ በላይ ስለሆነ ለሠላሳ እናካፍለዋለን ማለት ነው። ስናካፍለውም ቀሪ 19ን እናገኛለን ማለት ነው።

ስለዚህ የዕርገት ኢየዐርግ ሠኔ 9 ቀን ነው ብለን ነበር፤እናም ከሠኔ 9 ቀጥሎ የምናገኘው 19 የእራሱ የሠኔ ስለሆነ ሠኔ 19 ቀን የጸራቅሊጦስ ኢየዐርግ ነው ማለት ነው።

በአጠቃላይ፡- በዓለ ጸራቅሊጦስ ከግንቦት 15 እስከ ሠኔ 19 ባሉት ሠላሳ አምስት ቀናት ሲመላለስ ይኖራል ማለት ነው።



፶.፲ የጾመ ድኅነት ገደብ

ኢይወርድ

የጾመ ድኅነትን ኢይወርድ ለመስራት የጾመ ነነዌን ኢይወርድ ለማግኘት የተጠቀምነውን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን ማለት ነው፤መባጃ ሐመሩም 17 ነው ብለን ነበር፤እንዲሁም የጾመ ድኅነት ተውሳክ ደግሞ 1 ነው ስለዚህ እሊህን ሁለቱን በመደገፍ የጾመ ድኅነትን ኢይወርድ ማግኘት ይቻላል።

የጾመ ድኅነት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የጾመ ድኅነት ተውሳክ

= 17 + 1

= 18ን እናገኛለን ማለት ነው።

ስለዚህ የጸራቅሊጦስ ኢይወርድ ግንቦት 15 ቀን ነው ብለን ነበር፤ስለዚህ ከግንቦት 15 ቀጥሎ የምናገኘው 18 ቀን ደግሞ የእራሱ የግንቦት ነው፤ስለዚህ ግንቦት 18 የጾመ ድኅነት ኢይወርድ ነው ማለት ነው።

ኢየዐርግ .....የጾመ ድኅነትን ኢየዐርግ ለመስራት የጾመ ነነዌን ኢየዐርግ ለማግኘት

የተጠቀምነውን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን ማለት ነው፤መባጃ ሐመሩም 21 ነው ብለን ነበር፤እንዲሁም

የጾመ ድጎነት ተውሳክ ደግሞ 1 ነው ስለዚህ እሊህን ሁለቱን በመደገፍ የጾመ ድጎነትን ኢየዐርግ ማግኘት ይቻላል።

የጾመ ድጎነት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የጾመ ድጎነት ተውሳክ

= 21 + 1

= 22ን እናገኛለን ማለት ነው።

ስለዚህ የጰራቅሊጦስ ኢየዐርግ ሠኔ 19 ቀን ነው ብለን ነበር፤ስለዚህ ከሠኔ 19 ቀጥሎ የምናገኘው 22 ቀን ደግሞ የእራሱ የሠኔ ነው፤ስለዚህ ሠኔ 22 የጾመ ድጎነት ኢየዐርግ ነው ማለት ነው።

በአጠቃላይ፡- ጾመ ድጎነት ከግንቦት 18 ቀን እስከ ሠኔ 22 ቀን ባሉት ሠላሳ አምስት ቀናት ውስጥ ዘወትር ይማላለሳል ማለት ነው።



ኢይወርድ.....የጾመ ሐዋርያትን ኢይወርድ ለመስራት የጾመ ነነዌን ኢይወርድ ስንፈልግ የተጠቀምንበትን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን ማለት ነው፤ መባጃ ሐመሩም 17 ነው ብለን

ነበር፤እንዲሁም የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ ደግሞ 6 ነው። ስለዚህ እሊህን ሁለቱን በመደገፍ የጾመ ሐዋርያትን ኢይወርድ ማግኘት ይቻላል።

የጾመ ሐዋርያት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ

= 17 + 6

= 23ን እናገኛለን ማለት ነው።

ስለዚህ የጾመ ድኅነትን ኢይወርድ ግንቦት 18 ቀን ነው ብለን ነበር ስለዚህ ከግንቦት 18 ቀጥሎ ያለው 23 ደግሞ የእራሱ ግንቦት ስለሆነ ግንቦት 23 የጾመ ሐዋርያት ኢይወርድ ነው ማለት ነው።

ኢየዐርግ

የጾመ ሐዋርያትን ኢየዐርግ ለመስራት የጾመ ነነዌን ኢየዐርግ ስንፈልግ የተጠቀምንበትን መባጃ ሐመር እንጠቀማለን ማለት ነው፤ መባጃ ሐመሩም 21 ነው ብለን ነበር፤እንዲሁም የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ ደግሞ 6 ነው። ስለዚህ እሊህን ሁለቱን በመደገፍ የጾመ ሐዋርያትን ኢይወርድ ማግኘት ይቻላል።

የጾመ ሐዋርያት መግቢያ = መባጃ ሐመር + የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ

= 21 + 6

= 27ን እናገኛለን ማለት ነው።

ስለዚህ የጾመ ድኅነትን ኢየዐርግ ሠኔ 22 ቀን ነው ብለን ነበር ስለዚህ ከሠኔ 22 ቀጥሎ ያለው 27 ደግሞ የእራሱ የሠኔ ስለሆነ ሠኔ 27 የጾመ ሐዋርያት ኢየዐርግ ነው ማለት ነው።

በአጠቃላይ፡- ጾመ ሐዋርያት ከግንቦት 23 ቀን እስከ ሠኔ 27 ቀን ባሉት ሠላሳ አምስት ቀናት ዘወትር ሲመላለስ ይሆራል እንጂ ከግንቦት 23 አይወርድም ከሠኔ 27 ቀን አይወጣም ማለት ነው።


የጾመ ሐዋርያት ገደብ
ኢይወርድ
ኢየዐርግ
ግንቦት ፳፫
ሠኔ ፳፯
አይወርድም
አይወጣም

በአጠቃላይ የአጽዋማት ኢይወርድ ምስለ ኢየዐርግ እንደሚከተለው ነው፡፡

አጽዋማት	ኢይወርድ (ጥር ፲፯ + ከነነዌ ያለው የቀን እርዝማኔ)	ኢይዓርግ (የካቲት ፳፩ + ከነነዌ ያለው የቀን እርዝማኔ)	የዙረት ቀን
ጾመ ነነዌ	ጥር ፲፯	የካ ፳፩ + አልቦ =፳፩	፴፭
ዓብይ ጾም	፴+፩= የካ ፩	፴+፭=መጋ ፭	፴፭
ደብረ ዘይት	፴+፳፰=የካ ፳፰	፴+፴+፪=ሚያ ፪	፴፭
ሆሣዕና	፴+፴+፲፱=መጋ ፲፱	፴+፴+፳፫=ሚያ ፳፫	፴፭
ስቅለት	፴+፴+፳፬=መጋ ፳፬	፴+፴+፳፰=ሚያ ፳፰	፴፭
ትንሣኤ	፴+፴+፳፮=መጋ ፳፮	፴+፴+፴=ሚያ ፴	፴፭
ርክበ ካህናት	፴+፴+፴+፳=ሚያ ፳	፴+፴+፴+፳፬=ግን ፳፬	፴፭
ዕርገት	፴+፴+፴+፴+፭=ግን ፭	፴+፴+፴+፴+፱=ሰኔ ፱	፴፭
ፆመ ጰራቅሊጦስ	፴+፴+፴+፴+፲፭=ግን ፲፭	፴+፴+፴+፴+፲፱=ሰኔ ፲፱	፴፭
ፆመ ድኅነት	፴+፴+፴+፴+፲፰=ግን ፲፰	፴+፴+፴+፴+፳፪=ሰኔ ፳፪	፴፭
ፆመ ሐዋርያት	፴+፴+፴+፴+፳፫=ግን ፳፫	፴+፴+፴+፴+፳፯=ሰኔ ፳፯	፴፭

፯.፪. ፈተና ሰባት

1ኛ. ገደብ ማለት ምን ማለት ነው?

2ኛ. የአጽዋማትን ገደብ አሳዩ?

3ኛ. የአጽዋማትን ኢይዐውግና ኢይወርድን ማወቃችን ለምን ይጠቅመናል?

ቀ ጣ ይ



ምዕራፍ ሰምንት(፰)

፰.በእንተ ጳጉሜ

ስለ ዕለተ ጳጉሜ ምን አዲስ ነገር አለ ቢሉ፡-

፰.፩ ጳጉሜ ማለት ምን ማለት ነው?
፰.፪ አመጣጡስ እንዴት ነው?
፰.፫ እንዴትስ ጳጉሜ በዘመነ ዮሐንስ ስድስት ልትሆን ቻለች?
፰.፬ ሌላውና አስደናቂው ነገር እንዴትስ ጳጉሜን ሰባት ልትሆን ቻለች የሚለው ነው?
፰.፭ ለምን በጳጉሜ ስድስት መሆን የተነሳ በታላቁ የልደት በዓል ላይ መለያየት ሊፈጠር ቻለ?

፰.፩ ጳጉሜ

ጳጉሜ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፡- ጳጉሜ ማለት ቃሉ የግሪክ ቃል ሲሆን **“ሔፓጎሜኔስ ”** ከሚለው የፅር ቃል የመጣ ነው፤ ትርጉሙም **“ዓመት በዕለት ሲለካ የተረፈ”** ማለት ነው። ስለዚህ ጳጉሜ ማለት ከዓመቱ ማለትም በዓመት ውስጥ ካሉት 365 ቀናት ውስጥ ያሉት የካልዒት፤ የሳልሲት ትርፍ ማለት ነው በማለት ቅዱሳን የአቡሽሃር ሊቃውንት ይናገራሉ ያብራራሉ ማለት ነው።

፰.፪ የጳጉሜ አመጣጥ እንዴት ነው?

እም መርሃ አዝማን(የቁጥር መጽሐፍ)

የጳጉሜ አመጣጣ እንዴት ነው ቢሉ፡- ከላይ እንዳየነው ጳጉሜ ማለት ዓመት በዕለት ሲለካ የተረፈ ማለት ነው ብለን ነበር ስለዚህ በዚህ ተንተርሰን እንሰራለን ማለት ነው።

ይህ ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚያስረዳን ከሆነ 12 ወራት ማለትም ከመስከረም እስከ ነሐሴ ያሉት የዕለታት ብዛት 360 ዕለት ነው። ከዚህም ከ360ው ዕለት አንድ ቀን ማለት፡- አንድ ቀን ማለት... 12 ስዓት፤ከ52 ካልኢት፤ከ31ሳልሲት ነው ማለት ነው። ስለዚህ የአንዱን ቀን ካወቅን የ360ውን ዕለት ለማው ይቀላል ማለት ነው። ሲቀጥል

- 52 ካልዒት ማለት 1260 ሴኮንድ ነው።(60 ካልዒት ማለት 24 ደቂቃ ማለት ነውና)።
- 31 ሳልሲት ማለት ደግሞ 12.4 ሴኮንድ ነው።

ይህንን ደግሞ ወደ ደቂቃ እንቀይር ቢባል 21 ደቂቃ ከ0.4 ሴኮንድ ይሆናል ማለት ነው።

ስለዚህ በአንድ ቀን ውስጥ 21 ደቂቃ ከ0.4 ሴኮንድ ትርፍ አለ ማለት ነው።

ማለትም

- ስድሳ ካልዒት = ሃያ አራት ደቂቃ ነው ብለን ነበር ወይም
- አንድ ካልዒት = 0.4 ደቂቃ ነው

ስለዚህ 52ቱን ከአንድ ቀን የተረፈውን ማግኘት እንችላለን ማለት ነው።

1ኛ. 60 ካልዒት = 24 ደቂቃ

52 ካልዒት = U

$U = \frac{52 \times 24 \text{ ደቂቃ}}{60}$ = 21 ደቂቃን እናገኛለን ማለት ነው።

2ኛ. 1 ካልዒት = 0.4 ደቂቃ

52 ካልዒት = $ለ$

$ለ = \frac{52 \times 0.4 \text{ ደቂቃ}}{1}$ = 21 ደቂቃን እናገኛለን ማለት ነው።

ስለዚህ በአንድ ቀን ውስጥ 21 ደቂቃ ከ0.4 ሴኮንድ ትርፍ አለ ማለት ነው።

ስለዚህ ከመስከረም እስከ ነሐሴ ያሉትን 360 ቀናት ብናሰላ በእያንዳንዳቸው ቀናት ውስጥ አንድ ቀን ማለት 12 ወር ከ52 ካዒት ከ31 ሳልሲት ወይም 12 ስዓት ከ21 ደቂቃ ከ0.4 ሴኮንድ ነው።

ስለዚህ የ360ውን ዕለት ትርፍ ለማወቅ ፡-

52 ካልዒት × 360 ዕለት = 18720 ካልዒትን እናገኛለን ማለት ነው።

ይህንንም 18720 ካልዒት ወደ ሴኮንድ ብንለውጠው 449280 ሴኮንድ ይሆናል ማለት ነው።

<u>ሲቀመር</u>

1ካልዒት = 24 ሴኮንድ

18720 ካልዒት = ?

$x = \frac{18720 \times 24 \text{ ሴኮንድ}}{1}$ = 449280 ሴኮንድን እናገኛለን ማለት ነው።

ይህንንም ያገኘነውን 449280 ሴኮንድ ወደ ደቂቃ ብንለውጠው 7488 ደቂቃ ይሆናል ማለት ነው።

ይህንንም ያገኘነውን 7488 ደቂቃ ወደ፡-

- ስዓት……..124.8 ስዓት
- ኬክሮስ…….312
- ቀን፤……..5…ዕለት …..ይሆናል ማለት ነው።

ለዚህ ነው ጳጉሜ ማለት ትርፍ ፤ ጭማሬ ማለት ነው ያልነው ፤ ስለዚህ "ሔፓጎሜኔም " ማለት ዓመት በዕለት ሲለካ የተረሳ ወይም የተረፈ ነው ማለት ከዚህ አንፃር ነው። ለዚህ ነው በእያንዳንዱ ዕለት ያሉት ጥቃቅን ሴኮንዶችና ደቂቃ ተጨምረው በዓመታት ውስጥ ያሉትን አምስት ዕለታት ትርፍ ጭማሬ እንዲወልዱ አድርገዋል። ስለዚህ የጳጉሜ አመጣጥ ከዕለታት የተረሱ ወይም የተረፉ የደቂቃና የሴኮንድ ጥርቅም ማለት ነው።

ጀ.ቮ የጳጉሜ ስድስት የመሆን ምስጢር

ጳጉሜ በዘመነ ዮሐንስ በተለየ መልኩ ስድስት ትሆናለች ብለናል ግን እንዴት ስድስት ልትሆን ቻለች ቡሉ፡- ነገሩስ እንዲህ ነው፡-

በፀሐይ አቆጣጠር አንድ ዓመት ማለት 365 ዕለት፤ከ15 ኬክሮስ፤ከ6 ካልዒት (365 ቀን፤ከ6 ስዓት፤ከ2 ደቂቃ) ነው ። ስለሆነም በአንድ ዓመት ውስጥ 15 ኬክሮስ እና 6 ካልዒት ትርፍ አለ ማለት ነው፤ ስለዚህ ይህች 15 ኬክሮስ ትርፍ በአራት ዓመት ዙረሽ አንድ ቀን ትሞላለች ማለት ነው፤ ዘመኑም ዘመነ ዮሐንስ ማለትም ጳጉሜ ስድስት የምትሆንበት ፤ ዘመኑ ዘመነ ሉቃስ ብሒል 6ኛዋ ጳጉሜ የምትፈጸምበት ዘመን ነው ማለት ነው። ስለዚህ ይህች ጳጉሜ ስድስት ቀን መገኛዋ ከአንዱ ወንጌላዊ ብቻ ሳትሆን ከ 4ቱ ወንጌላዊያን የ6 ሰዓት አስተዋፀኦ የተውጣጣች 24 ሰዓት(1 ቀን) ስትሆን በሉቃስ የምትፈፀም ከአራቱ ወንጌላዊያን አሻራ የተገኘች የአራት ዓመት ዙረሽ ውጤት ናት ማለት ነው።

ሲቀመርም፡-

1 ቀን = 60 ኬክሮስ

1 ኬክሮስ = 60 ካልዒት

1ካልዒት = 60 ሣልዒት ነው።

ስለዚህ፡- 1 ቀን = 24 ስዓት = 60 ኬክሮስ

24 ስዓት = 60 ኬክሮስ ከሆነ

υ = 15 ኬክሮስ ስንት ስዓት ይሆናል

υ = 24 ስዓት X 15 ኬክሮስ ? = 60 ኬክሮስ..... = $\frac{360 \text{ ስዓት}}{60}$

υ = 6 ስዓት

ስለዚህ 6 ስዓት = 15 ኬክሮስ ፤ በመሆኑም ዐውደ ዓመት በፀሐይ 365 ዕለት ከ6 ስዓት ነው ማለት ነው ። ወገን ልብ ልናደርገው የሚገባ 6 ስዓቷ በአንድ ዓመት ነው ወይም የአንዱ ወንጌላዊ ናት ከአራቱ ወንጌላዊም ስድስት ስድስት ስዓት ትርፍ አለ ማለት ነው እናም(ሉቃስ ስድስት ስዓት + ዮሐንስ ስድስት ስዓት + ማርቆስ ስድስት ስዓት + ማቴዎስ ስድስት ስዓት) አራተኛ ዓመት ላይ አንድ ቀን ወይም 24 ስዓት ሆና **በሉቃስ ትፈፀማች** ማለት ነው። ስለዚህ ይህች የጳጉሜ ስድስት ቀን አመጣጥ ከረጅሙ ባጭሩ ይህን ይመስላል። እናም ለዚህ እንዲህ ካልን የጳጉሜን ሰባት የመሆን ምስጢር ወደ መመርመር እንመለስ።

፰.፬ የጳጉሜ ሰባት የመሆን ምስጢር

ሌላውና አስደናቂው ነገር የጳጉሜን ሰባት የመሆን ምስጢር ነው ይህ እንዴትና መቼ ይሆናል ቢሉ፡- አቆጣጠሩ በጣም እጹብ ድንቅ ነው ነገሩ ግን ሪና መዓልት ፤ ሪና ሌሊት በማለት ያመጣዋል።

ጳጉሜ ሰባት ማለት ፡-

- ሪና መዓልት
- ሪና ሌሊት } ማለት ነው በጥንት አባቶቻችን አጠራር።

በሌላ አነጋገርም የስድስት መቶ ዓመት ዑደት ወይም ሳሮስ ሳይክል በመባል ይጠራል ማለት ነው። ስለዚህ ጳጉሜ ሰባት በስድስት መቶ ዓመት ዙረሽ በኋላ የምትገኝ ልዩ የቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ በረከት ነች ማለት ነው።

ስለዚህ አንድ ዓመት በኢትዮጵያዊያን አቆጣጠር ፡-

- ✓ 365 ዕለት፤ከ15 ኬክሮስ፤ከ6 ካልዒት ወይም
- ✓ 365 ቀን፤ከ6 ስዓት፤ከ2 ደቂቃ ነው ብለን ነበር።

በመሆኑም ይህች ትርፍ ስድስት ካልዒት (2 ደቂቃ ከ24 ሴኮንድ) በመጠራቀም ከስድስት መቶ ዓመት አንዴ አንድ ዕለት ታስገኛለች ማለት ነው ምክንያቱም ከላይ ስለ ጳጉሜ ስድስት ስናወራ የ15ቷ ኬክሮስ ትርፍ ከአራት ዓመት አንዴ ጳጉሜን ስድስት ታደርጋለች ብለን ነበር

እንደዚህም ሁሉ ስድስቷ ካልዒት ከስድሰት መቶ ዓመት አንዴ ጳጉሜን ሰባት ታደርጋለች ማለት ስለዚህ ነው።

ሲቀመርም፦

በአንድ ዓመት ወይም በ365 ዕለት ስድስቱ ካልዒት ትርፍ ካለ በአንድ ዕለት ስንት ካልዒት ትርፍ ይኖራል ብለን ማስላት ነው።

365 ዕለት = 6 ካልዒት

በ1ቀን =?

$x = \frac{1\ \text{ቀን} \times 6\ \text{ካልዒት}}{365\ \text{ዕለት}}$ = 0.16438 ካልዒት ይሆናል ማለት ነው።

ይህንን ያገኘነውን 0.16438 ካልዒት ወደ ሴኮንድ በመቀየር በአንድ ዕለት ውስጥ የሚተርፈውን የሴኮንድ ብዛት ማወቅ ይቻላል ማለት ነው።

ማለትም፦

6 ካልዒት = 2 ደቂቃ ከ24 ሴኮንድ (144 ሴኮንድ)

0.16438 ካልዒት =?

$x = \frac{144\ \text{ሴኮንድ} \times 0.16438\ \text{ካልዒት}}{6\ \text{ካልዒት}}$ = *0.4 ሴኮንድ ይሆናል ማለት ነው።*

ስለዚህ በአንድ ዕለት 0.4 ሴኮንድ ትርፍ አለች ይህችን በስድስት መቶ ዓመት ውስጥ ያላትን የዕለት ብዛት ማውጣት ነው። ስለዚህ፦

- *በአንድ ወር = 12 ሴኮንድ*
- *በአንድ ዓመት = 144 ሴኮንድ(2.4 ደቂቃ)(1ኬክሮስ)*
- *በአሰር ዓመት = 1440 ሴኮንድ(24 ደቂቃ)(60 ካልዒት)*
- *በአንድ መቶ ዓመት = 240 ደቂቃ(4ሰዓት)(10 ኬክሮስ)*
- *በሁለት መቶ ዓመት = 480 ደቂቃ(8 ሰዓት)(20 ኬክሮስ)*
- *በሦስት መቶ ዓመት = 720 ደቂቃ(12 ሰዓት)(30 ኬክሮስ)*
- *በአራት መቶ ዓመት = 960 ደቂቃ(16 ሰዓት)(40 ኬክሮስ)*
- *በአምስት መቶ ዓመት = 1200 ደቂቃ(20 ሰዓት)50ኬክሮስ)*
- *በስድስት መቶ ዓመት = 1440 ደቂቃ(24 ሰዓት)(60ኬክሮስ) = = =* ***አንድ ዕለት***

ስለዚህ ይህች ስድስት ካልዒት በስድስት መቶ ዓመት አንዴ ጳጉሜን ሰባት ታደርጋለች ማለትም በስድስት መቶ ዓመት አንዴ ሪና መዓልት፤ ሪና ሌሊት ሆኗል (ተካክሏል)

ይባላል(የሌሊቱም የመዓልቱም ስዓት እኩል ሆኗል) ማለት ነው፤ በማለት የአቡሽሃር ቀዱሳን ሊቃውንት ይናገራሉ ፤ያብራራሉ፤ያብተነትኑታል ማለት ነው።



ምዕራፍ ዘጠኝ(፱)

፱. የኢትዮጵያዊያንና የምዕራባዊያን የዕለታትና የወራት ስያሜ ልዩነት

፱.፩ የዕለታት ስያሜ ልዩነት

፱.፩. ኢትዮጵያዊያን

እሁድ

እሁድ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ እሑድ ፣ እሒዶት ከሚለው አርእስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን **አንድ፤ አንደኛ፤ መጀመሪያ** ማለት ነው።።
ስለዚህ እሁድ ማለት የመጀመሪያ ዕለት ማለት ነው።።
በዚህ ቀን ፍጥረታት መፈጠር ስለጀመሩ እሑድ ተብሏል ፤ ለዚህም አ.ዘፍ 1፤1 “በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ” እንዳለ።። ስለዚህ የሀንን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በመከተል እና አብነት በማድረግ እሁድ ብለው ጠርተዋታል።።

ሰኑይ

ሰኑይ ማለት ምን ማለት ነው **ቢሉ** “ሰኑይ፣ ሰኑዮት” ከሚለው አርእስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ሁለት፣ ሁለተኛ ሁለት አደረገ ማለት ነው ።። ለዚህም ቅዱስ እግዚአብሔር ፍጥረታትን መፍጠር የጀመረበት ሁለተኛ ዕለት ነውና ሰኞ ሊባል ችሏል ማለት ነው።።

ሠሉስ

ሠሉስ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ ሠልሶ፣ ሠልሶት ከሚለው አርእስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ሦስት ሦስተኛ ሦስት አደረገ ፤ ማግሰኞ ማለት ነው ይህም ማግስተ ሰኞ ማለት ነው።። እግዚአብሔር ፍጥረታትን የጀመረበት ሦስተኛ ዕለት ማለት ነው።።

ረቡዕ

ረቡዕ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፡- ረብዓ፣ረብዖት ከሚለው አርእስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ትርጉሙም አራት አራተኛ አራት አደረገ ማለት ነው፡፡ ይኸውም ቅዱስ እግዚአብሔር ፍጥረታትን መፍጠር የጀመረበት አራተኛ ቀን ማለት ነው፡፡

ኀሙስ

ኀሙስ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ ኀምሶ፣ኀምሶት ከሚለው አርእስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ትርጉሙም አምስት አምስተኛ ፤ አምስት አደረገ ማለት ነው፡፡ ይኸውም ቅዱስ እግዚአብሔር ፍጥረታትን መፍጠር የጀመረበት አምስተኛ ቀን ማለት ነው፡፡

ዓርብ

ዓርብ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ ዓሪብ፣ዓሪቦት ከሚለው አርእስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ትርጉሙም “**መካተቻ**” (ተካተተ) ማለት ነው፡፡ ይኸውም ፍጥረታት እሑድ መፈጠር ጀምረው ዓርብ መካተታቸውን (ተፈጥረው መፈፀማቸውን) የሚያስረዳ ነው፡፡ አንድም፡-

- “**የመና መካተቻ**”..... እስራኤላዊያን ስድስቱን ቀን ሙሉ መና ሲወርድላቸው ሰንብቶ ቅዳሜ ግን አይወርድም ነበር የቅዳሜን ትክ ግን ዓርብ ጨምሮ ይወርድላቸው ስለነበር የመና መካተቻ ብለውታል ማለት ነው፡፡ (**ኦ.ዘፍ 16፣5-22**)
- አንድም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 33 ዓመት ከ3ወር በዚህ ምድር ከኖረ በኋላ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ተሰቅሎ ድህነተ ዓለምን የፈጸመበት እና ስራውን ያካተተበት ስለሆነ “**መካተቻ**” **ብለውታል፡፡**

ቅዳሜ

ቅዳሜ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ ቀዲም፣ ቀዲሞት ፣ መቅደም ከሚለው አርእስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ሰንበተ ክርስቲያን ከሆነችው ከዕለተ እሑድ ቀድማ ስለምትገኝ ቀዳሚት ሰንበት (ቅዳሜ) ተብላለች፡፡በዚህ ዕለት እግዚአብሔር ሥራውን (ፍጥረቱን) መፍጠር ጨርሶ ያረፈበት ዕለት ነው፡፡ ኦ.ዘፍ 2፣2 የመጀመሪያዋ ወይም የቀደመችው የብሉይ ኪዳን ሰንበት ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ቀዳሚት ቀዳም፣ ቅዳሜ የቀደመች ማለት ነው ፣ ዛሬም ከሰንበተ ክርስቲያን ቀደም ቀደም ብላ የምትውል ስለሆነች ቅዱሳን ሊቃውንት ቀዳሚት ብለው ሰይመዋታል ማለት ነው፡፡

ልብበሉ

ቅዱሳን የኢትዮጵያን ሊቃውንት የዕለታትን ሰም (ስያሜ) በተገለጸላቸው ጸጋ እና እውቀት እንዲሁም ቅዱሱን መጽሐፍ ቅዱስ መሰረት በማድረግ ለዕለታት ስያሜን ሰጥተዋል እኛም የእነርሱን ፈለግ ተከትለን ለትውልድ እናስተላልፋለን ማለት ነው፡፡ ለዚህም **"ተዘከሩ መኳንቲክሙ ዘነገርክሙ ቃለ እግዚአብሔር" እንዳለ፡፡**

ስለዚህ እስከዚህ ድረስ ያለው የኢትዮጵያዊያን የዕለታት ስያሜ ነበር አሁን ደግሞ የምዕራባዊያን የዕለታት ስያሜ ወደ መመርመር እንመለስ፡፡

፱.፩.፪.ምዕራባዊያን

እሑድ

ማለት "Sun's Day ..." **የፀሐይ ቀን ማለት ነው፡፡** ምክንያቱም ለፀሐይ ይሰግዱና ፀሐይን ያመልኩ ስለነበር የፀሐይ ቀን አሉት እንጂ እንደ ኢትዮጲያዊያን የመጀመሪያ ቀን አላሉትም፡፡

ንጉስ ቆስጠንጥኖስ ስለ እሁድ ሲናገር እሁድ የዕረፍት በዓል መሆን እንዳለባትና **"sun day" የሚለውን ትቶ በላቲን ቋንቋ "Days Dominica" የጌታ ዕለት ተብሎ እንዲሰየም አድርጓል እየተባለ ይተረካል፡፡ በ321ዓ.ም.....**

ሰኞ

ማለት "Moon's Day" (በላቲን ሉናዳይ ይባላል)፡፡ ይህም ለአሲራያን ጣኢታት ሴሌን፣ሉና፣ማኒ ለተባሉ ለጨረቃ ጣኦታት ክብር የተሠየመ ስያሜ ነው፡፡ ስለዚህም Moonday" ማለት "Moon Day` የጨረቃ ቀን ማት ነው፡፡ ስለዚህ እሊህ ሰዎች ዕለቱን የሰጡት ወይም የሰየሙት ለጨረቃ ጣኦታት ስም ነው ማለት ነው፡፡

ማክሰኞ

ማለት "Tuesday`` Tiu's Day" በላቲን "Day of Mars" አንድም ቲው ለሚባለው የጦርነትና የሰማይ (የጠፈር) አምላክ (ባለ አንድ እጅ አምላክ) ለሚባለው የወጣ ስም ነው፡፡

ረቡዕ :- **ማለት** "Wensday" (Woden' s day) ብለው ሰይመውታል፣ ይህም "Weden" ማለት የወደን ቀን ፤ ወደን (የአደን አምላክ) የሚሉት የጀርመን ጣኦት ስም ሲሆን ዕለቱም በእርሱ

ተሰይሟል። በተለይም በኢንግላንድና በአንግሎ አክሶን እስከ 7ተኛው ክፍለ ዘመን የታወቀ ጣኦት ነበር።

ኀሙስ

ማለት “Thursday” “Thor’s Day” ፤ ይህ ቃል በጥንት እንግሊዘኛ “Pinor” ሲባል በአሁኑ ዘመን ግን መጠሪያው “Thursday” ተብሏል ወይም የቶር ቀን ይህም በጀርመን ጣኦት አምላኪዎች ዘንድ **“የመብረቅ አምላክ”** በመባል የሚጠራ የጣኦት ስም ነው።

ዓርብ

ማለት “Friday” ….” Freya’s Day” የፍረያ ቀን፣ ፍረያ (የፍትወትና የውበት አምላክ) ለሚሉት ጣዖት **የተሠጠ ስም ነው ዕለቱም በጣዖቱ ስም ተሰይሟል ማለት ነው።**

ቅዳሜ

ማለት “Saturday” በላቲን “Day saturiny” “Saturn’s Day” - የሳተርን ቀን፣ ሳተርን፤የእርሻ አምላክ ወይም **“የሰብል አምላክ”** በመባል ይመለክ የነበር የጣኦት ስም ሲሆን ለእርሱ ክብር በማለት ይህችን ቀን ሰይመዋታል ማለት ነው።

ልብበሉ

ምዕራባዊያን የቀናትን ስያሜ ሲሠጡና ሲሠይሙ መጽሐፍ ቅዱስን መሰረት አድርገው ሳይሆን እራሳቸው ለሚያመልኳቸው ጣኦታት ስያሜ ሲሰጡ ቅዱሳን አባቶቻችን ግን ከምዕራባዊያን በላቀና በማይገናኝ መልኩ የቀናትን ስያሜ ሰጥተዋል ማለት ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያዊያንና የምዕራባዊያን የቀናት ስያሜ በትልቁ ልዩነት እንዳለው በጥብቅ መገንዘብ እና መረዳት አለብን ማለት ነው።

እስከዚህ ድረስ የዕለታት ስያሜ ልዩነት ነው አሁን ደግሞ ወደ ወራት ልዩነት ወደ መመርመር እንሔዳለን ማለት ነው።

፱.፪ የወራት ስያሜ ልዩነት

፱.፪.፩. ኢትዮጵያዊያን

1ኛ. መስከረም

መስከረም ማለት የግእዝ ቃል ሲሆን "ከሪም፤ ከሪሞት"፣ መክረም ከሚለው አርዕስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን "መስ" የሚለው ቃል ከመሴ መጥቶ "ከሪም" ከሚለው ቃል ላይ ወድቆበታል፡፡ ስለዚህ መስከረም ማለት መሴከሪም ወይም ምሴተ ክረምት ፤ የክረምት መምሻ ፤ የክረምት ጫፍ፣ የክረምት መካተቻ ፣ የመፀው መባቻ ማለት ነው፡፡

እንግዲህ በቋንቋ ጥናቶች (ሊንጉስቲክ ስተዲይ) ከሆነ "ዝ" ና "ስ" በጸሐፊ ስህተት ይወራረሳሉና መስከረም ተባለ እንጂ በጥንት ጊዜ "መዝከረም" ይባል ነበር ፡፡ ለምሳሌ ብንመለከት ፡- ሀበዘ ብሎ ህቡዝ ወይም ህብስት .... ህብዞት ማለት ሲገባው ህብስት ይላል ይን ስንመለከት እንግዲህ "ዝ" ና "ስ" እንደሚወራረሱ ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ "መስከረም" የሚለውም ቃል "ዝ" ለ "ስ" ተለውጦ መስከረም ተባለ ይላሉ የቋንቋው ሊቃውንት፡፡ ስለዚህ መስከረም ማለት የዓመት ማሠቢያ ፤ መታሠቢያ ወይም አውደ ዓመት ማለት ነው፡፡ እናም ቅዱሳን የኢትዮጵያ ሊቃውንት የመጀመሪያውን ወር በዚህ መሰረት መስከረም ብለውታል፡፡

2ኛ. ጥቅምት

ጥቅምት ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ ጠቂም፣ ጠቂሞት ወይም መጥቀም ከሚለው አርዕስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ትርጉሙም በዘይቤ አፈታቱ "የተሠራች ስር" ማለት ነው፡፡ በምስጢር ሲታይ ግን ወርኃ ግብር፣ ጥንተ ግብር፤ የስራ ወር፣ የስራ መጀመሪያ ይኸውም ጥንተ ፍጥረት እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው በዚሁ ወር እንደሆነ ይነግረናል ማለት ነው፡፡

በተለይ ግን እንደ ወራቱ ሲፈታ ግን በተለይ ጽጌውን አበባውን መደብ አድርጎ ከተፈታ ደግሞ ጥቅምት ማለት ፍሬ፣ ወርኃ ፍሬ፣ የፍሬ ወር ፣ የሰብል ወር ማለት ነው። ይህንን አስመልክቶ አባቶቻችን በምሳሌያዊ አነጋገር ሲናገሩ እንዲህ ይላሉ፡- ልጅን በጡት ካልቀጡት እህልን በጥቅምት ካልጠበቁት ፣ ካልቆጠቡት ከንቱ ነው በማለት ይናገራሉ ማለት ነው። ስለዚህ ወሩን ጥቅምት ብለውታል ።

3ኛ. **ህዳር**

ህዳር ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፡-

- በእብራይስጥ - አደር
- በቅብጥ- አቶር የሚለውን ትርጉም ይሰጠዋል ማለት ነው።

ይኸውም ህዳር ማለት ሀዲር፤ ሀዲሮት ከሚለው አርዕስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ትርጉሙም የአዘመራ ወራት ስለሆነ ጠባቂዎች በዱር የሚያድሩበት(የሚያርፉበት) ወር ማለት ነው።

4ኛ. **ታኅሣሥ**

ታኅሣሥ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፡- ኀሲስ፤ ኀሲሶት ከሚለው አርዕስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ምረመራ፣ ፍለጋ ፤ ምርምር ማለት ነው።ይኸውም እንደሚታወቀው ክብር ይግበውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ወር ታህሳስ 29 ቀን ነው ጌታችን በተወለደበት ስዓትም ሦስቱ ነገስታት "አይቱ ህለወ ዘተወልደ ንጉሠ አይሁድ" የተወለሰው የአይሁድ ንጉስ ወደየት ነው እያሉ እየመረመሩ ፣ እየፈለጉ እስከ ቤተ ልሔም ድረስ መጥተዋል ስለዚህ ሊቃውንት ታኅሣሥ ብለውታል፤ ማለትም የፍለጋ፤የምረምራ ወራት ማለት ነው።

5ኛ. **ጥር**

ጥር ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፡- ጠይሮ፣ ጠይሮት ከሚለው አርዕስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ትርጉሙም በምስጢር ሲፈታ ምጥቀት፤ርዝመት ማለት ነው። ይኸውም በዚህ ወር "በሰናኦር አካባቢ አርባ ዓመታትን የፈጀ ቁመቱ 5432 ክንድ ከሁለት ስንዝር የሆነ እጅግ ምጡቅ ህንጻን ፈጽመው ያንንም ህንጻ ስላሴ በዚህ ወር "ንዑ ንረድ" የከለዳዊያንን ቋንቋ

እንደባልቀው ብለው ቋንቋቸውን ደባልቀው ሕንፃቸው እንዲፈርስ አድርገዋልና ቅዱሳን ሊቃውንት ምጥቀት ፤ ርዝመት ያለው ህንፃ የፈረሰበት ሲሉ ጥር ብለው ሰይመውታል።(ዘፍ 11፤1-7፣ ኩፋ 10፤12-13)

6ኛ. የካቲት

የካቲት ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፡-"ከቲት፤ከቲቶት" ከሚለው አርዕስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ትርጉሙም "ማስገባት" ማለት ነው። ይኸውም "የመከር መካተቻ፤ የበልግ መባቻ" ማለት ነው።

7ኛ. መጋቢት

መጋቢት ማለት "መግቦ፣ መግቦት"ከሚለው አርዕስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ትርጉሙም የሌሊቱም የመዓልቱም እኩል የሚሆንበት ማለት ነው። ለምሳሌ፡- መስከረምና መጋቢት ቀኑ አሥራ ሁለት ስዓት ፤ ሌሊቱም 12 ስዓት ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ ቀንና ሌሊት የሚተካከልበት ሲሉ መጋቢት ብለው ሰይመውታል።

8ኛ. ሚያዝያ

ሚያዝያ ማለት "ምሕዝ፣ ምህዞት፤ መቅረብ፤ ማጀብ፤ ማክበር" ወይም ሙሽራ ሙሽሪትን መክበብ ተብሎ መመዝገብ ከሚባለው አርዕስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ትርጉሙም "የሚዛዝርት/የሚዚዎች/" ወራት ፤ የሙሽሮች ወራት "መኑ መኑ" ማን ማን የሚበባሉበት ማለት ነው። በኢትዮጵያዊያን ልማድ በግንቦት ወር ከጥንት ምንም አይነት ሠርግ አይከናወንም ነበር ስለዚህ ይህ ወር ሠርግ የሚደረግበት ፣ ሚዚዎች በዝተው የሚታዩበት ነውና ሚያዝያ ነው።

ምሳሌ

ሚዜና ሚያዝያ የሚሉት ተመሳሳይ ቃል ይሰጠናል በደንብ ስናስተውለው፡-

ሚዜ፡- ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፡- ቃሉ የግዕዝ ቃል ነው "አርከ መርዓዊ" ወይም ግልገል ሙሽራ የሙሽራው አሳሳች ከቀኙ የቆመ እኩያው አምሳያው ነው። ስለዚህ ከማሳሳቱ የተነሣ ልብሱም ከሙሽራው ጋር ከመመሳሰሉ የተነሣ የሙሽሪት ዘመዶች "መኑ ዝንቱ" ይህ ማነው ይህ ማነው እያሉ ያደንቁታል ይጠይቁታል ስለዚህ "መኑ ዝንቱ" የሚሉት ነውና ሚዜ ተብሏል።

ሚያዝያ፡- ማለት ደግሞ በዚህ ወቅት ሚዜዎች የሚታዩበት ተጋቢዎች የሚጋቡበት ነውና "የሚዛዝርት" ወራት ሲሉ ሊቃውንት ሚያዝያ የሚል ስያሜን ሠጥተውታል።

9ኛ. ግንቦት

ግንቦት ማለት “ገንቦ፤ ገንቦት”፤ መገንባት፤ መናስ፤ ወይም ማፍረስ ፤መቆፈር ከሚለው አርዕስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ትርጉሙም “ገቦ ክረምት፤ ጎረ ክረምት” የክረምት አቅራቢያ በክረምት ጎን ያለ የክረምት አጎራባች ማለት ነው፡፡ ግን በግንብ ዘይቤ ከተፈታ ግን እጅግ ድንቅ ምስጢርን ይሰጠናል፤ ይኸውም “”ወርኃ ስራሔ፤ ወርኃ ህንጻት” ወይም የግንባታ፤ የህንፃ ወር ማለት ነው ፡፡ እንደሚታወቀው (2ኛ ዜና 6፤1)(ዕዝ 3፤8-13) የባቢሎን ግንብ ሁለቱ መቅደሶች በግንቦት ተመስርተዋል፤ ስለዚህ ሊቃውንት የግንባታ ወራት ሲሉ መጽሐፍ ቅዱሱን አይተው ግንቦት ብለው ሰይመውታል፡፡

10ኛ. ሠኔ

ሠኔ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፡-

- በቅብጥ…..ኘዋኒ
- በእብራይስጥ….ሴዋን ተብሏል፡፡

ስለዚህ ሠኔ ማለት “ሠኒ ሠኒዎት” ማማር፤ መወበት፤መቆንጀት ከሚለው አርዕስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ትርጉሙም የወጣ ሲሆን ትርጉሙም በቁመ፡ “ሠናየ ዘርዕ” የመልካም ዘር ወር፤ ዘረ መልካም ሲሉ ሠኔ ብለውታል፡፡

11ኛ. ሐምሌ

ሐምሌ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፡-“ሐሚል፤ ሐሚሎት” መለምለም ፤ቅጠላማ መሆን ከሚለው አርዕስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ትርጉሙም በቁመ፡ “ወርኃ በቅል፤ ወርኃ ሠርፅ” የመለምለም ፤ የመረንጎድ፤ አረንጓዴ የመሆን የሚል ፍች በቅዱሳን ሊቃውንት ተሰጥቶታል፡፡

12ኛ. ነሐሴ

ነሐሴ ማለት “ንሒስ፣ ንሒሶት” ወይም መገንባት ከሚለው አርዕስት ጥሬ ዘር ስም ንዑስ አንቀጽ አባት ዘር የወጣ ሲሆን ትርጉሙም በዘይቤ ከተፈታ ጥብቀት፤ “ቅናተ ክረምት” ወይም የክረምት ጎን መታጠቂያ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ወር አዝዕርት ስር የሚሰዱበት ፤ ቅንጣት አንን የሚያወጡበት፤ በቁመት የሚመነደጉበት፤በስራቸው ብዙ ዝርያዎችን የሚያፈሩበት ወር ማለት ነው፡፡

ስለዚህ “ጥብቀት ዕናት ” ማለት ነው። ማለትም ከሠኔ 25 ቀን ጀምሮ በሚዘንበው ዝናብ መራቱ እየጠበቀ የቡቃያው ስር ወደ ታች እየጠበቀ ቁመቱ ወደ ላይ እየመጠቀ የሚታይበት ወር ስለሆነ ነሐሴ ብለው የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሊሰጥሙት ችለዋል። ከዚህ በመቀጠል የኢትዮጵያዊያን ፀጋ እና ሀብት የሆነችው አሥራ ሦስተኛዋ ወር “ጳጉሜ” ናት ምዕራፍ ስምንት ላይ በይፋ ስለተገለጸ መመልከት ይቻላል።

፱.፪.፪. ምዕራባዊያን

1ኛ. January (ጥር)

“ጃንዋሪ” ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፤ “ጃኑስ” የሚባል የሮማዊያን ጣኦት ማለትም የሮማዊያን የበር ጠባቂ ጣኦት እየተባለ ይመለክ ይሰገድለት የነበረ የአንድ የእንጨት ጣኦት ስም ነው ፤ ለጣኦቱ ማስታወሻ ሲሉ ወራቱን መእርሱ ሰይመውታል ማለት ነው።

2ኛ. February (የካቲት)

“ፌብርዋሪ” ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፡-በነጠላ “ፌብርዋ” ሲባል በብዙ “ፌብሩ” ይባላል፤ ይህም የሮማዊያን አጠራር ሲሆን “መንፃት” ማለት ነው። ማለትም የሮማዊያን “የመንፃት” በዓል በዚህ ወር ይከበራል በተለይ ይህ ወራቸው ለአዲስ ዓመትና ለአዲስ የአዝመራ ወቅት የሚዘጋጁበት ስለሆነ “አማልእክቶቻችን ከተደሰቱ ብዙ ምርት እናገኛለን ከተቆጡ ግን ምንም ምርት አናገኝም” ስለሚሉ በዚህ ወቅት ኃጢአታቸውን ለጣኦታቱ እየተናዘዙ ንስሐ ይገቡበታል ስለዚህ “የመንፃት” ወር “ፌብርዋሪ” ብለው በጣኦታቱ ስም ሰይመውታል ማለት ነው።

3ኛ. March (መጋቢት)

“ማርች” ማለት “ማርስ” ከሚለው የፕላኔት ስም የወጣ ሲሆን ይህም “የጦር አምላክ” ተብሎ ይሠገድለት የነበረ የጣኦት ስያሜ ነው። ይህም ጣኦት አዝመራችንን የጠብቅልናል ብለው ጣኦት አምላኪዎች ይሠግዱለት ነበር። ስለዚህ “የማርስ” ወር ሲሉ “ማርች” ብለው መጽሐፍ ቅዱስን መሰረት ሳያደርጉ ምዕራባዊያን ሠይመውታል ማለት ነው።

4ኛ. April (ሚያዝያ)

ይህ የምዕራባዊያን አራተኛ ወር ስያሜውን ያገኘው “አፕሪልስ” ወይም “አፍሮ ዳይት” ከምትባለ የፍቅርና የቁንጅና አምላክ ተብላ ትመለክ ከነበረች አንዲት ጣኦት ስም የወጣ ነው። ይኸውም “አፕሮል” በላቲን “መክፈት” ማለት ሲሆን በዚህ ወራት አበቦች የሚያበቡበት ወር ሲሆን በርካታ የእርሻ በዓላት

ይደረጋሉ ፤ በዚህ በዓላቸው ሴቶቹ የአበባ ጉንጉን እራሳቸው ላይ በማድረግ ሰውነታቸውን በመታጠብ ለዚች ጣኦት ማለትም “ለአፍሮ ዳይት” መስዋዕት ያቀርቡ ነበር፡፡ ስለዚህ የእርሷ ወር ሲሉ “አፕሪል” ብለው ሠይመውታል፤ የአፍሮ ዳዊት ወር ማለት ነው፡፡

5ኛ. May (ግንቦት)

ይህ ወራቸው ስያሜውን ያገኘው “ማያ” ከምትባል “የስጦታ አምላክ” ከምትባል የጣኦት ስም ሲሆን “የሜርኩሪ እናት” በመባል ትመለክ የነበረች ጣኦት ስም ነው፡፡ ትርጉሙም “የማያ” ወር ማለት ነው፡፡

6ኛ. June (ሠኔ)

“ጁን” ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፡- “ጁኖፕ” በምትባል ሴት ጣኦት የተሰየመ ነው፡፡ ይህችም ጣኦት “የጁፒተር ሚስትና እህት” ተብላ ይሠገድላት የነበረች ጣኦት ናት ፤ በተለይ “የጋብቻ አምላክ፤ የሴቶችን ውበት የምትጠብቅ” ተብላ የምትመለክ ጣኦት ስትሆን ወሩ በእርሷ ተሰይሟል ማለት ነው፡፡

7ኛ. Jully (ሐምሌ)

“ጁላይ” ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ በጥንት ስሙ “ኩንቲኒስ” በላቲን አምስተኛ ማለት ነው፡፡ በዘመኑ ግን “ለጁሊየስ ቄሳር” ክብር ሲሉ ዕለቱን ለውጠው “ጁላይ” ብለው “ለጁሊየስ ቄሳር” ስም ሠይመውታል ማለት ነው፡፡

8ኛ. August (ነሐሴ)

“ኦገሥት” ማለት ምን ማለት ነው ቢል በጥንት ስሙ “ሴክስቲልስ” ይባል ነበር በላቲን ስድስተኛ ማለት ነው፡፡ ኋላ ግን “ለአውግስጦስ ቄሳር” ክብር ሲባል ወራቱ “ኦገስት” ተብሎ በእርሱ ስም እንዲሰየም ተደርጓል ማለት ነው፡፡

9ኛ. September (መስከረም)

“ሴፕቴምበር” ማለት በላቲን “ሴፕቲፒርስ” “ሰባተኛ ” ማለት ነው፡፡

10ኛ. October (ጥቅምት)

“ኦክቶበር” ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፤ “ኦክቶብሪስ” ማለት ሲሆን፤ በላቲን ስምንተኛ ማለት ነው፡፡

11ኛ. Novmeber (ህዳር)

“ኖቬምበር” ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፤ “ኖቬምብሪስ” ማለት ሲሆን በላቲን ዘጠነኛ ማለት ነው፡፡

12ኛ. December (ታኅሣሥ)

“ዲሴምበር” ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ፤ “ዲሴምብሪስ” ማለት ሲሆን በላቲን አሥረኛ ማለት ነው።

እናስተውል

እንግዲህ የአውሮፓዊያንን የወራት ስያሜ ስንመረምር ፡-

አምስት ወራቶቻቸው ብቻ የቀን አቆጣጠርን ስያሜ ሲይዝ ማለትም፡-

- ኦገሥት
- ሴፕቴምበር
- ኦክቶበር
- ኖቬምበር
- ዲሴምበር

ሁለቱ ወራቶቻቸው የነገሥታቶቻቸውን ስም ይዟል ። እነርሱም፡-

- ጁን
- ጁላይ

ቀሪዎች ወራት ግን የጣኦታቶቻቸውን ስምና ዝና ይዘዋል ማለት ነው። ማለትም፡-

- ጃንዋሪ
- ፌብርዋሪ
- ማርች
- አፕሪል
- ሜይ

ስለዚህ እስከዚህ ድረስ የኢትዮጵያዊያንና የምዕራባዊያን እጅግና ግሩም የቀንና የወራት ስያሜ ነው ። አሁን ደግሞ የስድስቱ ዕለታት ሥነ-ፍጥረትን ወደ መመርመር እንመለሳለን ።



ምዕራፍ አስር(፲)

፲. ሥነ-ፍጥረት

የሥነ ፍጥረት ነገር እንዴት ነው ቢሉ ፍጥረታት በፈጣሪያቸው በቅዱስ እግዚአብሔር መፈጠር ማለት ነው፤ ፍጥረት ከእሑድ እስከ ዓርብ ለስድስት ዕለታት ተፈጥረዋል።

የስድስቱ ቀን ሥነ ፍጥረት አፈጣጠር እንዴት ነው ቢሉ ሥላሴ እንቅድመ ዓለም በአንድነት በሦስትነት ሳሉ አንድነታቸው ሦስትነታቸውን ሳይጠቀልለው ሦስትነታቸው አንድነታቸውን ሳይከፍለው በአንድነት በሦስትነት ሲሠለሱ ሲቀደሱ ሲመሰገኑ ይኖሩ ነበር። ኋላ ግን ዓለምን እንፍጠር ብለው አሰቡ፤ አስበውም አልቀሩ፡-

1ኛ. "ዘአምጽአ ኩሎ በቃለ ኃይሉ እምኀበ ኢሀሎ ኀበ ሀሎ" ይህንን ዓለም እምኀበ አልቦ ኀበቦ... ካለ መኖር ወደ መኖር አምጥተው ፈጠሩት።

2ኛ. እስመ ውእቱ ይቤ ወኮነ ወውእቱ አዘዘ ወተፈጥሩ፤ እርሱ ብሏልና ሆኑም እርሱም አዝዟልና ተፈጠሩም። እንዳለ ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት(መዝ 148፤5-6)

ቅድስት ሥላሴ ይህንን ዓለም ካለ መኖር ወደ መኖር አምጥተው መፍጠራቸው ጉዳይ ኖሯቸው ጉዳይ ሊሞላላቸው አይደለም ፤ አንድነታቸው ሦስትነታቸው ጌትነታቸው ባለጸግነታቸው በዓለም እንዲታወቅ ብለው ነው እንጂ።

፲.፩ የእሑድ ፍጥረታት

ለእግዚአብሔር ጥንት አስገኝ የለውም ፤ በአንድነት በሦስትነቱ ጌትነት ሳለ ዓለምን ልፍጠር ብሎ አሰበ አስቦም አልቀረም ቅዳሜ ማታ ለእሁድ አጥቢያ ሰማይንና ምድርን፣ እሳትንና ነፋስን፣ ውሃንና ጨለማን፣ መላእክትንና ብርሃንን ፈጠረ።

“በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ” እምዳለ ቅዱስ ሙሴ በኦሪት ።።

እሑድ ማለት ለፍጥረት አንደኛ ለቀመር ስድስተኛ ለፀሐይ አምስተኛ ዕለት ማለት ነው።። የአሥራ ሁለቱ ስዓተ መዓልት የአስራ ሁለቱ ስዓተ ሌሊት የሀያ አራቱ ግዚያት ስምንት ፍጥረት ይህ ነው።። ይህም የተፈጸመው በምን ቀን ነው ቢሉ መጋቢት ሃያ ዘጠኝ ቀን ነው።።

፲.፪ የሰኞ ፍጥረታት

ወይቤ እግዚአብሔር ለይኩን ጠፈር ማዕከለ ማይ ከመ ይፍልጥ ማእከለ ማይ ወማይ ወኮነ ከማሁ፤ ዘፍ 1፡6-9

ቅዱስ እግዚአብሔር በሁለተኛው ዕለት ምን ፍጥረትን ፈጠረ ቢሉ ከዚህ ገቦምሮ እስከ ብሩህ ሰማይ ውሃ መልቶ ፈጥሯል፤ እሑድ በጊዜ ሠርክ ለሰኞ አጥቢያ “ለይትጋባዕ ማይ ውስተ ምዕላዲሁ ወያስተርኢ የብስ” ውሃው በአንድ ቦታ ይሰብሰብ ደረቁም ይገለጥ ብሎ ውሃውን ሰበሰበ።። ያን ከአራት ከፍሎ በየቦታው አዘጋጀው።።

- **አንደኛው ይህ የምናየው ሰማይ ነው**
- **ሁለተኛው ከጠፈር በላይ ወስኖታል “ሐኖስ” ይባላል፤ ይኸውም ኃያል ተሐዋኪ ማለት ነው ።። “ወማይ ዘመልዕልተ ሰማይ ተባዕታይ ውእቱ” ከጠፈር በላይ ያለው ውሃ ተባዕት ነው እንዳለ ቅዱስ ሔኖክ(13፡32)።። ማይኒ ለመልዕልተ ሰማያት፤ከሰማይ በላይ ያለው ውሃ እንዳለ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት(መዝ 148)**
- **ሦስተኛው በአድማስና በናጌብ መካከል ዙሪያውን አጎድጉዶ ወስኖታል አስፍሮታል እርሱም “ወቅያኖስ” ይባላል።። ጠፈርን ከእብነ አድማስ ጋር አያይዞታል፤ “ወአስተጣበቅዋ ዲበ እብነ ኮክሕ እንዳለ ቅዱስ እዮብ።። ከጠፈር በዙሪያዋ 12 እልፍ(120000) ደጃፎችን አወጣ፤ ከቅዱስ ሚካኤል ሰራዊትም 24 እልፍ(240000) መላእክትን አምጥቶ በእያንዳንዱ ደጃፍ ሁለት ሁለት ጠባቂዎችን ሾመ።። “ወሄመ ክልኤተ ክልኤተ ርኡሳነ ለእለ አሐዱ አንቀጽ እንዲል።። ጠባቂዎችም ከሥላሴ ማህተም ያለበት ደብዳቤ ያልያዘውን አያስወጡም አያስወርዱም።።**

በምድር በዙሪያዋ ሁለት ተራራዎችን አስገኘ የወዲያኛውን አድማስ አለው ከዚያም 12 መስኮት በምስራቅ፣ 12 መስኮት በምዕራብ አወጣለት ነፍሳት የሚወጡበት ነው።። የወዲህኛውን ናጌብ አለው፤ ዐረፍተ ሣህል ማለት ነው።። ለዚህም 6 መስኮት በምስራቅ፣ ስድስት መስኮት በምዕራብ አወጣለት፤ ይኸውም የብርሃናት መመላለሻ ነው።።

- **አራተኛውን እጅ ውሃ ከምድር በታች አጽንቶታል።። “ዘአጽንዓ ለምድር ዲበ ማይ እንዳለ ክቡር ዳዊት”(መዝ 23፤2)።። ነገር ግን ከምድር ጋር ተራርቃለች።። “ወሰቀላ ለምድር ዲበ ወኢምንት ዕራቃ” እንዳለ እዮብ(26፤7) ይህም ምድሪቱን በታችዋ አንዳች አልባ አንጠለጠላት ማለት ነው።።**

ሰኑይ ማለት ሁለት ሁለተኛ ማለት ነው፤ ሰኞ ለፍጥረት ሁለተኛ ለቀመር ሰባተኛ ለፀሐይ ሦስተኛ ማለት ነው። ሁለት ዕለት ዘጠኝ ፍጥረት ይህ ነው ። ይህስ የተፈጸመው መቼ ነው ቢሉ መጋቢት ሠላሳ ቀን ነው።

፲.፫ የማግሰኞ ፍጥረታት

ወይቤ እግዚአብሔር ለታብቁል ምድር ሐመላማለ ዘርእ ዘይዘራእ በበዘርኡ ወበበዘመዱ ዘፍ 1፤11-13፤ እግዚአብሔር ሰኞ ማታ ለማስከኞ አጥቢያ በጊዜ ሠርክ በዕለተ ሠሉስ ምንና ምን ፍጥረት ፈጠረ ቢሉ ሦስት ፍጥረትን ፈጠረ ።

- በምሳር የሚቆረጡ
- በማጭድ የሚታጨዱ አዝርዕትን
- በጥፍር የሚለቀሙ አትክልትን ዕፅዋትን ፈጠረ

አንድም፡-

ምድር ሁለተናዋ ጭቃ ነበርና ሰኞ ማታ ለማስከኞ አጥቢያ ከእግረ አድማስ ነፋሳትን አውጥቶ ሲያስማማት አደረ። እንደ ሠኔ እርሻ ስትሆን "ለታብቁል ምድር ሐመላማለ ዘርእ ዘይዘራእ በበዘርኡ ወበበፅጌሁ ወበበፍሬሁ" ምድር በየዘሩና በየአበባው በየፍሬውም የሚያፈራ ዘርንና ልምላሜን ታውጣ ብሎ ባዘዘ ጊዜ በመጥረቢያ የሚቆረጡ ዕጽዋት፤ በማጭድ የሚታጨዱ አዝርእት፤ በጥፍር የሚለቀሙ አትክልት ሦስት ፍጥረታት ተገኝተዋል።

"ወበሠሉስ ዕለት ገብረ እግዚአብሔር ዕፀወ ዐቢይተ ወንኢሳነ" እግዚአብሔር በሦስተኛው ዕለት ታላላቆችንና ታናናሾችን ዛፎች ፈጠረ እንዳለ ኤጲፋንዮስ አክሲማሮስ። የዕፀ ሕይወትም ተፈጥሮ በዚሁ በሦስተኛው ቀን ነው።ከዚህም ዕፀ ሕይወት ውስጥ አራት አፍላጋት(ወንዞች) ይወጣሉ። እነርሱም ፡-

- ኤፌሶን
- ግዮን
- ጤግሮስ
- ኤፍራጥስ ናቸው።

እስከዚህ ድረስ የዕለተ ሠሉስ ፍጥረት ነው። ሠሉስ ማለት ሦስት ሦስተኛ ለፍጥረት ሦስተኛ ለቀመር አንደኛ፤ ለፀሐይ ሰባተኛ ማለት ነው። ሦስት ዕለት አሥራ ሁለት ፍጥረት ይህ ነው። ይህስ የተፈጸመው በምን ቀን ነው ቢሉ ሚያዝያ አንድ ቀን ነው።

፲.፩ የረቡዕ ፍጥረታት

“ወገብረ እግዚአብሔር ብርሃናተ ዓበይተ ዘየዓቢ ከመይመልክ መዓልተ ፤ ወዘይንእስ ብርሃን ከመ ይመልክ ሌሊተ ምስለ ከዋክብት። ዘፍ 1፤12”

እግዚአብሔር በዕለተ ረቡዕ ማግሰኞ ማታ በጊዜ ሠርክ ለረቡዕ አጥቢያ ምን ምን ፍጥረትን ፈጠረ ቢሉ ፡-

- ፀሐይን
- ጨረቃን
- ከዋክብትን ፈጠረ።

አንድም፡-

ማግሰኞ ማታ ለረቡዕ አጥቢያ “ለይኩን ብርሃናት ለጠፈረ ሰማይ” ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ላይ ይሁኑ ባለ ጊዜ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት ተገኝተዋል።

አፈጣጠራቸው

ጨረቃን ሲፈጥር ስሌደዋን ከንፋስና ከውሃ የወደደውን ያህል ነስቶ ብርሃን ሥሎባታል። ቅርፅዋም በሰው አምሳል አድርጓታል። “በዕሥራ ወርቀ ሌሊት ታስተርኢ ወርኃ በአርአያ ብእሲ ሌሊተ ወመዓልተ በሰማይ” በሃያኛው ሠርቀ ሌሊት ጨረቃ በሌሊትና በመዓልት ከሰው አምሳል በሰማይ ትታያለች እንዳለ ሔኖክ።

ፀሐይንም ሲፈጥር ስሌዳዋን ከእሳትና ከነፋስ የወደደውን ያህል ነሥቶ ብርሃን ሥሎባታል። ቅርፁም እንደ ጨረቃ ነው፤ የሁለቱም መጠናቸው እኩል ነው።

ከዋክብትን ሲፈጥር የሠሌዳቸው መጠን ግን ይነስም ይብዛም አልተጻፈም ፤ በብርሃን እንዲበላለጡ ግን ኮከብ እም ኮከብ ይኔይስ ክብሩ፤ ኮከብ ከኮከብ በክብር ይበልጣል በማለት ቅዱስ ጳውሎስ ተናግሯል ማለት ነው።

ረቡዕ ማለት ማለት አራት አራተኛ ለፍጥረት አራተኛ ለቀመር ሁለተኛ ለፀሐይ አንደኛ ማለት ነው። ረቡዕ ማለት አራት ዕለት ማለት ነው። አራት ዕለት አሥራ አምስት ፍጥረት ይህ ነው። ይህስ የተፈጸመው በምን ቀን ነው ያሉ እንደሆን ሚያዚያ ሁለት ቀን ነው።

፲.፭ የሐሙስ ፍጥረታት

“ወይቤ እግዚአብሔር ለታውፅዖ ማይ ዘይትሐወስ ዘቦ መንፈሰ ሕይወት ወአዕዋፍ ዘይሠርሩ መልዕልተ ምድር ወመትሕተ ሰማይ ወኮነ ከማሁ”። ዘፍ ፩፤፳-፳፩

እግዚአብሔር በዕለተ ሐሙስ ረቡዕ ማታ ለሐሙስ አጥቢያ በጊዜ ሠርክ ምንና ምን ፍጥረት ፈጠረ ቢሉ ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ ብሎ ቢያዝዝ በእግራቸው የሚሽከረከሩ፤ በክንፋቸው የሚበሩ፤ በልባቸው የሚሳቡ በየወገናቸው በየዘመዳቸው ሰፍር ቁጥር የሌላቸው ሦስት ፍጥረታት ተፈጠሩ። ዘፍ 1፤20-21

አንድም ፡-

“ለታውጽእ ባሕር ዘመድ ዓሣት ወኩሎ ዘይትሐወስ ዘቦ መንፈሰ ሕይወት”፤ ባሕር የዓሣትን ወገንና የሕይወት መንፈስ ያለው የሚንቀሳቀሰውንም ሁሉ ታውጣ ብሎ እግዚአብሔር በተናገረ ጊዜ ፡-

- በልባቸው የሚሳቡ
- በእግራቸው የሚሽከረከሩ
- በክንፋቸው የሚበሩ ሦስት ፍጥረታት ተፈጥረዋል።

ከእነዚሁም ውስጥ የሚበሉም፤ የማይበሉም አሉ። “ኢትብላዕ ኩሎ ዘአልቦ ክንፈ ወቅጣረ ዘውስተ ማይ”፤ በውሀ ውስጥ ካለው ክንፍና ቅርፊት የሌለውን ሁሉ አትብላ ብሎ ሊቀ ነቢያት ሙሴ እንደተናገረ።(ዘሌ 11፤10-12)

ሐሙስ ማለት አምስት አምስተኛ ማለት ነው። ዕለተ ሐሙስ ለፍጥረት አምስተኛ፤ ለቀመር ሦስተኛ፤ ለፀሐይ ሁለተኛ ማለት ነው። አምስት ዕለት አሥራ ስምንት ፍጥረት ይህ ነው። ይህስ የተፈጸመው በምን ቀን ነው ቢባል ሚያዝያ ሦስት ቀን ነው።

፲.፭ የዓርብ ፍጥረታት

“ወእመ አዘዛ እግዚአብሔር ለይእቲ የብስ አውዕአት ኩሎ እንስሳተ ወአራዊተ ወአዕዋፈ ዓበይተ ወደቃይቀ ዘአልቦን ጎልቋ”። ዘፍ ፩፤፳፬-፳፭

እግዚአብሔር በዕለተ ዓርብ ሐሙስ ማታ በጊዜ ሠርክ ለዓርብ አጥቢያ(ጽባሕ) ምን ምን ፍጥረትን ፈጠረ ቢሉ ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደ ወገኑ ታውጣ ብሎ ቢያዝዝ ሦስት ፍጥረታትን ፈጠረ። “እንስሳት ፣ አራዊት፣ አዕዋፍት በየወገኖቸው በየዘመዳቸው ተፈጠሩ። ዘፍ 1፤24-25

አንድም፡-

“ለታውዕእ የብስ ዘመደ እንስሳት”፤ ምድር የእንስሳትን ወገን ታውጣ ብሎ እግዚአብሔር በተናገረ ጊዜ ፡-

- በልባቸው የሚሳቡ
- በእግራቸው የሚሽከረከሩ
- በክንፋቸው የሚበሩ ሦስት ፍጥረታት ተገኝተዋል።

ከእነዚህም ውስጥ የሚበሉም የማይበሉም አሉ። “ብልዑ ኩሎ እንስሳ ዘንፍቅ ሰኮናሁ ወስጡቅ ጽፍሩ” ፤ ሠኮናው የተከፈለ ጥፍሩ የተሰነጠቀ የሚያመስኳም እንስሳ ሁሉ ብሉ ብሎ ሙሴ እንደተናገረ። (ዘሌ 11፤1-3) ፤ እስከዚህ ድረስ ሃያ አንድ(፳፩) ፍጥረት ነው።

እነዚህንስ ለምን ፈጠራቸው ቢሉ ለሰው መማሪያ፤ ማወቅያ መመርመሪያ ሊሆኑ ፈጥሯቸዋል። “ወኩሉ ዘተፈጥረ ለመፍቅደ ነባብያን ቦ እምኔሆሙ ለምህሮ ወቦ እምኔሆሙ ለተዘክሮ”፤ ከተፈጠረውም መካከል ለትምህርት ለተዘክሮ የሚሆኑ አሉ ብሎ አረጋዊ መንፈሳዊ እንደተናገረ። “ወለእመ ፈቀድከ ታእምር ዘንተ እምአፍአ ብከ መምህር ወሰማዕት ካልዕ ዘይመርሐከ ኀበ አንክሮተ እግዚአብሔር” ፤ ይህን ታውቅ ዘንድ ብትሻ እግዚአብሔርን ወደ ማድነቅ የሚመራህ መምህር ሌላም ምስክር ከውጭ አለልህ ብሎ ማር ይስሐቅ እንደተናገረ። “ወዘያስተርኢ እግዚአብሔር እምፍጥረተ ዓለም ይትዐውቅ በፍጥረቱ ለፍጥረቱ”፤ ከፍጥረተ ዓለም ገቦምሮ የማይታይ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ለፍጥረቱ ይታወቃል ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረ።(ሮሜ 1፤20) ፤ አንድም “እንዘ ኢየኀድግ ርእሶ ዘእንበለ ሰማዕት” ፤ ራሱን ያለ ምስክር አልተወም ተብሎ እንደተጻፈ።(ሐዋ 14፤15-17)

ትኩረት፡- ረቡዕ ማታ በጊዜ ሠርክ ለሐሙስ አጥቢያ እንስሳት፤አራዊት፤አዕዋፍ ተፈጠሩ ካልን እነዚህ አንድ አይሆኑም በምን ይለያያሉ ቢሉ በግብራቸው ይለያያሉ። ከባሕር የተፈጠሩት ወደ የብስ ወጥተው ቢውሉ ቢያድሩ ዋዕየ ፀሐይ/የፀሐይ ቃጠሎ/ ሲያቃጥላቸው ይሞታሉ ያልቃሉም። ከየብስ የተፈጠሩትም ከባሕር ገብተው ቢውሉ ቢያድሩ ውርጭ ወይም ቅዝቃዜ ሲጸናባቸው ይሞታሉ ያልቃሉና በግብራቸው ይለያያሉ ማለታችን ለዚህ ነው።

፲.፭.፩. የአዳምና የሔዋን ተፈጥሮ

የአዳምና የሔዋን አፈጣጠር/ተፈጥሮ/ እንዴት ነው ቢሉ፡- ከዚህ በፊት ሥላሴ ፍጥረታትን ሁሉ በሠርክ በሠርክ ሲፈጥሩ ሰንብተው ዓርብ በነግህ “ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ። ዘፍ ፩፤፳፮-፳፯

እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር ብለው ቢያዝዙ አዳም ተፈጠረ። ዘፍ 1፤26-27

“ወነሥአ እግዚአብሔር ነፋሰ ወእሳተ ማየ ወመሬተ ወገብሮ ከእንለ እምሕያው በዘዚአሁ አርአያ ወአምሳል” ፤ አዳምንስ ከምን ከምን ፈጥረውታል ቢሉ ከመሬትና ከውኃ፣ ከእሳትና ከነፋስ እንደ ዘንግ መልምለው እንደ እሾት ፈልፍለው በእርሳቸው አርአያ በእርሳቸው አምሳል ፈጠሩት። አንድም ቅድስት ሥላሴ “ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ብለው ቢያዝዙ አራቱ ባሕርያተ ሥጋ ሦስቱ ግብራተ ነፍስ አንድ ሆነው ተዋህደው የሠላሳ ዓመት ጎልማሳ ሆኖ አንድ ጊዜ ተገኝቷል። “ሔዋንንም” በሳምንቱ ፈጥረዋታል። ማለትም፡-

የመጀመሪያው ሰው አዳም ከተፈጠረ በኋላ አራዊትን ሁሉ ሴትና ወንድ እየሆኑ ሲወጡ ሲወርዱ አየና ሥላሴ ከመላእክት በቀር ፍጥረታትን ሁሉ ሲፈጥሩ ሴትና ወንድ እያደረጉ ፈጥረዋቸዋል፤ ለምን ይሆን እኔን ብቻዮን የፈጠሩኝ ብሎ አሰበ ፤ ሥላሴም የአዳምን አሳብ “ጸሎት” አድርገው ሰምተውለት፤

“ኢይደልዎ ለእጓለ እምሕያው ይንበር ባሕቲቶ አላ ንግበር ሎቱ ቢጸ ዘትረድኦ”። ዘፍ ፪፤፲፰-፲፱ ፤እጓለ እምሕያው ብቻውን መኖር አይገባውምና ባለእንጀራ እንፍጠርለት አሉ። ዘፍ 2፤18-19 ፤ “እጓለ እምሕያው ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ አዳም ከሕያው እግዚአብሔር አባት ፤ ከሕያው መንፈስ ቅዱስ እናት የተገኘ የተፈጠረ ልጅ ማለት ነው። አንድም “እጓል” የተባለ አዳም ፤ “እም” የተባለች ምድር ፤ “ሕያው” የተባለ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ከሕያው እግዚአብሔር አባት፤ ከጎቱም ምድር እናት የተገኘ የተፈጠረ ልጅ ሲል “እጓለ እምሕያው” አለው።

“ወእምዝ ነሥአ እግዚአብሔር አዳደ ዓፅመ እም ዓፅመ ገቦሁ ለአዳም ወመልዓ መካና ለይእቲ ዓፅም ሥጋ ወነደቃ ብእሲተ ”። ዘፍ ፪፤፳፩-፳፪ ፤ ከዚህም በኋላ በአዳም ላይ ድካም ንዋም/እንቅልፍ/ መጣበት ፤ አዳምም እጅግ ሳይተኛ እጅግም ሳይነቃ በመንቃትና በመተኛት መካከል ሳለ ከግራ ጎኑ አንድ አጥንት አንሥቶ ሔዋንን እርሱን አስመስሎ እርሱን አሳክሎ በአርአያ በአምሳል፣ በአካል በብርሃን የአሥራ አምስት ሴት አድርጎ ፈጠራት። ዘፍ 2፤ 21-23፤ “ኦ ዝመንክር ነሥአ አዳደ ዓፅመ እምገቦሁ ለአዳም ወለሐኮ እምኔሁ ብእሲተ ወኩሉ ፍጥረተ እጓለ እምሕያው”፤ ከአዳም ጎን አንዲት ዓፅም መንሳት ምን ይደንቅ ከእርሱ ሴትን ፈጠረ የሰው ፍጥረትንም ሁሉ ፈጠረ እንዳለ ቅዱስ ኤፍሬም ዘሐሙስ። ከዚህም በኋላ ቅድሥት ሥላሴ አዳምን በአርባ(፵) ቀኑ፤ ሔዋንን በሰማንያ(፹) ቀኗ በመንፈስ ቅዱስ አክብሮ ሰባቱ ሐብታትን አሳድሮ ብርሃን አልብሶ፤ ብርሃን አጎናጽፎ ገነት አስገብቷቸዋል።

ሰባት ሐብታት የተባሉትም፡- ኃይል፣ ኩነኔ፣ መንግሥት፣ ንዕሕና፣ ክህነት፣ ትንቢትና አሚን ናቸው።

ቅድስት ሥላሴ እሑድ ጀምረው እስከ ዓርብ ድረስ የፈጠሯቸው ፍጥረታት እያንዳንዱ ቢቆጠር ፍጡር ተናግሮ ባልፈፀመውም ነበር ነገር ግን እየወገኑ ብዙውን አንድ ብዙውን አንድ እያሉ ቢቆጥሩ ግን ከእሑድ እስከ ዓርብ ድረስ የተፈጠረው ፈጥረት ሃያ ሁለት(፷፪) ነው። “ወኮነ ኩሉ እስራ ወክልዔተ ዘመደ” እንዳለ(ኩፋ 3፤2)። በሰባተኛው ቀን ግን ከመፍጠር አርፈውበታል ይኸውም ቅዳሜ ነው።

“ወአመ ሳብዕት ዕለት አዕረፈ እግዚአብሔር እምኩሉ ግብሩ ዘአንዘ ይግበር”። ዘፍ ፪፤፪-፫፤ እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በስድስተኛው ቀን ፈፀመ። በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ አረፈ።(ዘፍ 2፤2-3)

እስከዚህ ድረስ የዕለተ ዓርብ ሥነ ፍጥረት ነው ዓርብ ማለት ስድስት ስድስተኛ ማለት ነው። ዓርብ ለፍጥረት ስድስተኛ ፤ ለቀመር አራተኛ፤ ለፀሐይ ሦስተኛ ቀን ማለት ነው። ስድስት ዕለት ሃያ ሁለት ሥነ ፍጥረት ይህ ነው። ይህስ የተፈጸመው በምን ቀን ነው ቢሉ ሚያዝያ

አራት ቀን ነው። እስከዚህ ድረስ ከረጅሙ በአጭሩ ከስድስቱ ዕለታት የተፈጠሩ ፍጥረታትን የሚያወሳ ነው።

ምስጋና ለስላሴ

ማን ፈጠረን

ማን-ፈጠረን? --------ስላሴ
ስላሴ ስንት ናቸው?-------ሶስት

ስማቸው ማን ማን ነው?------አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ

አብ ማለት ምን ማለት ነው?-----አባት

የማን አባት?--------የወልድ

ወልድ ማለት ምን ማለት ነው?------- ልጅ

ከማን የተወለደ?----------ከአብ

መንፈስ ቅዱስ ማለት ምን ማለት ነው?-------ሰራጺ

ከማን የሰረጸ?---------ከአብ

ሰረጸ ማለት ምን ማለት ነው ?------አብን አህሎ ወልድን መስሎ ከአብ የወጣ የተገኘ ማለት ነው ። ዘሰረጸ እምአብ እንዳሉ ሊቃውንት።

አብ ወላዲ አስራጺ ፣ ወልድ ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስ ሰራጺ ምንም ላጠይቆ አካላት ሶስት ስላልን አንድ አምላክ ብለን እናምናለን ስላሴ አንድ ሲሆኑ ሶስት ይሆናሉ ሶስት ሲሆኑ አንድ ይሆናሉ።

ሶስት የሚሆኑበት ነገር በምን በምን ነው ቢሉ ---በስም ፣ በአካል ፣ በግብር ፣ በገጽ ፣ በመልክ በእኒህ በአምስት ነገሮች ሶስት ይሆናሉ።

የስም ሶስትነታቸው አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ መባላቸው ነው

በግብርም እየብቻ ናቸው ።

የአብ ግብሩ መውለድ ማስረጽ ነው እንጅ እንደ ወልድ አይወለድም እንደ መንፈስ ቅዱስ አይሰርጽም ፥ የወልድም ግብሩ መወለድ ነው እንጅ እንደ አብ አይወልድም አያሰርጽም እንደ መንፈስ ቅዱስም አይሰርጽም ፥ የመንፈስ ቅዱስም ግብሩ መስረጽ ነው እንጅ እንደ አብ አይወልድም አያሰርጽም እንደ ወልድም አይወለድም ::

በዚህም ግብራቸው አባት ክልጅ እንዲቀድም ልጅ ከአባት እንዲከተል መቅደም መቀዳደም መከተል መከታተል የለባቸውም::

በአካልም እየብቻ ናቸው::

የአብ አካሉ የብቻው ነው ፥ የወልድም አካሉ የብቻው ነው ፥ የመንፈስ ቅዱስም አካሉ የብቻው ነው ::

ይህም አካላቸው ገጽ ያለው ነው::

የአብ ገጹ የብቻው ነው ፥ የወልድም ገጹ የብቻው ነው ፥ የመንፍፈስ ቅዱስም ገጹ የብቻው ነው::

ይህም ገጻቸው መልክ ያለው ነው::

የአብ መልኩ የብቻው ነው ፥ የወልድም መልኩ የብቻ ነው ፥ የመንፈስ ቅዱስም መልኩ የብቻው ነው::

<<አብኒ በአካሉ ወበገጹ ወበመልኩ ፍጹም ውእቱ ፥ ወልድኒ በአካሉ ወበገጹ ወበመልኩ ፍጹም ውእቱ፥መንፈስ ቅዱስኒ በአካሉ ወበገጹ ወበመልኩ ፍጹም ውእቱ >> እንዳለ ሊቁ አትናትዮስ::

የአንድነታቸውስ ነገር በምን በምን ነው ቢሉ በእግዜብሔርነት በአምላክነት በፈጣሪነት በባሕርይ በፈቃድ በመንግስት በስልጣን በክብር በመለኮት በብርሐን በሕይወት በሕልውና ከዚሕ በሚበዛ ነገር አንድ ይሆናሉ::

 <<አንሰ ሶበ እቤ እብል በይንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዳለ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ>>

ሰው ማለት ምን ማለ ነው ቢሉ

ሰባቱ ነገራት ያሉበት ማለት ነው::

ሰባቱ ነገራት ማን ማናቸው ቢሉ ------አራቱ ባሕርያተ ስጋ እና ሶስቱ ግብራተ ነፍስ ናቸው::

አራቱ ባሕርያተ ስጋ ማን ማናቸው ቢሉ -----ነፋስ ፥እሳት፥ውሃ ፥መሬት ናቸው::

ሶስቱ ግብራተ ነፍስ ማን ማናቸው ቢሉ------ለባዊነት ፥ነባቢነት ፥ሕያዊነት ናቸው::

ለሰው ከዚሕ የወጣ ተፈጥሮ የለውም::

የስላሴን አንድነት ሶስትነት ምልአት ስፍሀት ርቀት

የወልድንም ከሰማኣየ ሰማያት መውረዱን

ከስጋዋ ስጋ ከነፍሷ ነፍስ ንስቶ ከሁለት አካል አንድ አካል ፥ ከሁለት ግብር አንድ ግብር ፥ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በኩነተ ተዋሕዶ በቅብዓተ መንፈስ ቅዱስ መክበሩን ፥ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን ፥ ወልደ አብ ወልደ ማርያምነቱን ፥ በሰላሳ ዘመኑ በእደ ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ መጠመቁን ፥ አርባ መአልት አርባ ሌሊት በገዳመ ቆሮንቶስ መጾሙን ፥ ሶስት አመት ከሶስት ወር በዚህ አለም ህገ ወንጌል ማስተማሩን እናምናለን።

ለአርዓያ ለቤዛ ብሎ በእለተ አርብ 13ቱን ህማማተ መስቀል መቀበሉን እናምናለን

እሊህስ 13ቱ ሕማማተ መስቀል ማን ማን ናቸው ቢሉ

1.ተአስሮ ድሕሪት.....ወደኋላ መታሰር

2. ተስሕቦ በሐብል.....በገመድ መሳብ

3. ወዲቅ ውስተ ምድር.....በምድር ላይ መውደቅ

4. ተከይዶ በእግረ አይሁድ.....በእግረ አይሁድ መረገጥ

5. ተገፍዖ ማዕከለ አምድ.....ከምሰሶ ጋር መላተም

6. ተጽፍዖ ምልታሕት.....በጥፊ መመታት

7. ተቀሰፎ ዘባን.....ጀርባን በጅራፍ መገረፍ

8.ተኮርዖተ ርዕስ.....ራስን በዱላ መመታት

9.አክሊለ ሶክ.....የእሾህ አክሊል መድፋት

10. ጸዊረ መስቀል.....መስቀል መሸከም

11. ተቀንዎ በቅንዋት.....በችንካር መቸንከር

12. ተሰቅሎ በዕጽ.....በመስቀል (በእንጨት) መሰቀል

13. ሰሪበ ሐሞት.....መራራ ሐሞትን መጠጣት

ስጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ለቤዛ አለም መስጠቱን እናምናለን።

ሶስት መአልት ሶስት ሌሊት በከርሰ መቃብር አድሮ መቃብር ክፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል መነሳቱን እናምናለን

እኛም እርሱን ተከትለን እርሱን በኩር አርገን ከሞት በኋላ መነሳታችንን እናምናለን። ኋላም ይህን አለም ለማሳለፍ ሐሴት ለጻድቃን ፍድሃ ለኃጥአን ለመስጠት ዳግም ምጽአቱን እናምናለን።

ይህን ለአደረገ አምላክችን 10ቱን ቃላተ ኦሪት 6ቱን ቃላተ ወንጌል 7ቱን ጊዜአት 7ቱን አጽዋማት ሕጉን ስርአቱን ለመጠበቅ ያብቃን አሜን!!!

ተፈጸመ ፡ አንቀጸ ፡ ባሕረ-ሐሳብ ፡ ወ ፡ ሥነ-ፍጥረት።።

“በአንዲት መለኮታዊት ሥልጣን ለሦስቱ አካላት ምስጋና ይገባል አሜን ይቆየን!!!”

ዋቢ መጽሐፍት

1ኛ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ ፷፪ ዓ.ም

2ኛ. መጽሐፈ አቡሽሃር(የቀን መቁጠሪያ) ሐምሌ ፴/፲፱፻፹፪ ዓ.ም አዲስ አበባ

3ኛ. መጽሐፈ አክሲማሮስ ንባቡና ትርጓሜ ዘስድስቱ ዕለታት ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ

4ኛ. የቀመርና የሥነ ፈለክ ምርምር ከአለቃ ያሬድ ፈንታ ወልደ ዮሐንስ ፲፯/፰/፳፻፩ ዓ.ም

5ኛ. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ፲፱፻፸፰ ዓ.ም

6ኛ. ወልደ አብ ቀደምት በምስባከ ቅዱሳን ቆጋ ኪዳነ ምሕረት አፀደ ኤምስጣቴምስ አንድነት ገዳም አሳታሚነት

7ኛ. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አዲስ አበባ

ተፈፀመ!!!

ወልደ ሚካኤል ጎንቻ(0919473584)